

# ፈለገ ጥበብ

፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩ ጥር - መጋቢት ፲፱፻፺፩ ዓ/ም







* በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?
* ሰው የሌላውን ሕይወት የማጥፋት መብት የለውም
* የማይ... ሁለት ነገሮች
* ... የትንቢት ቀጠሮ
* ቅዱስ ላሊበላና ቅድስት መስቀል ክብራ
* የጽኛ መቶ ክፍለ ዘመን ሰውና ጥያቄው
* ኃጢአትን የምናሸንፈው ሕግን በመጠበቅ ነው
* ታቦት (ጽላት) እንዲቀረፅ ማን ፈቀደ?




ሚካኤል እምባ (ትግራይ)



ቤተ መድኃኔ ዓለም (ላሊበላ)



ቤተ ጊዮርጊስ (ላሊበላ)



ቤተ ማርያም (ላሊበላ)

© Safeguarding Religious Treasures of the Ethiopia Orthodox Church

ዋጋ ብር 3.00

www.ethiopianorthodox.org

# እስትጉቡእ

(ኦስትጉቡእ - ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማስተ ነው)

## ጾመ ነቢያት
## (የነቢያት ጾም)

መምህር ቀለመወርቅ ወርቁ

የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ

«ስለዚህም ነገር ጾምን፡ ወደ እግዚአብሔርም ለመንን፡ እርሱም ተለመነን።» (ዕዝ.፰፥፳፫)

በዚህ ርእስ መነሣት ከሚገባቸው ጥያቄዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣

፩. ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

፪. የነቢያት ጾም በማን፡ መቼ እና እንዴት ተጀመረ?

፫. የነቢያትን ጾም ለምን እንጾማለን? የሚሉት ናቸው።

፩. ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

ጾም ማለት በፊደላዊ ትርጉሙ «ጾመ» ጾመ፡ ተወ፡ ታቀበ፡ ታረመ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተመሠረተ ሲሆን መተው፡ መከልከል፡ እና መጠበቅ ማለት ነው።

ይህም ከክፉ ሥራ እና ለክፉ ሥራ ከሚያነሣሡ የምግብ እና የመጠጥ ዓይነቶች በቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጻሕፍት እስከ ተወሰነልን ጊዜ መታቀብ ማለት ነው። በምሥጢራዊ (በአንድምታ) ትርጉሙ ጾም ማለት፡

ሀ. የሥጋ ግብር (ጻባሕተ ሥጋ) ማለት ነው።

ይህም ማለት የሥጋ ፈቃድን ለነፍስ ፈቃድ ማስገዛት ማለት ነው። ኃጢአት የእግዚአብሔርን ስጦታ የሚያሳጣ ክፉ ሥራ ሁሉ የሥጋ ፈቃድ ድል ነው። በተቃራኒው ጾም ማለት የነፍስ ፈቃድ ድል ነው።

ለ. ጾም ማለት «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ.፬፥፬) ሲል መድኀን ክርስቶስ በነገረን ቃለ ወንጌል መሠረት እንጀራ ለሰው እንጂ ሰው ለእንጀራ የተፈጠረ አለመሆኑን መረዳት፡ የሰው ሕይወት ያለ እንጀራ የሚኖርበት ዓለም የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳለ በማመን ሰው በእግዚአብሔር መንግሥት ለሚኖረው ኑሮ ልምምድ ማድረግ ነው።



ሐ. ጾም ማለት ለጥፋታችን ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቅጣት መቀበል ነው። (መዝ.፴፭፥፲)

፪. ነቢያት እነማን ናቸው? ጾማቸውስ?

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለሕዝቡ የሚያስተላልፉ እና በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላቸው የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ አስቀድመው የሚናገሩ ነቢያት ይባላሉ። (፩ሳሙ.፱፥፺፡ ፪ጴጥ. ፪፥፪፡ አሞ.፩፥፫)

### የነቢያት ጾም ስያሜና አጀማመር

ይህ ጾም እንደ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አተረጓጎም በርካታ ስያሜዎች አሉት ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ:-

፩. ጾመ ነቢያት (የነቢያት ጾም ይባላል)

ነቢይነት የሚጀምረው ደረጃው የተለያየ ይሁን እንጂ ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ነው (ዘፍ.፪፥፳፫) በመሆኑም ጾሙም የሚጀምረው ከአዳም እንደ ሆነ እና...«ነገር ግን መልካምን እና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱም በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ» (ዘፍ.፪፥፲፯) የሚለው የእግዚአብሔር ቃል የመጀመሪያው የጾም ትእዛዝ እንደ ሆነ ስለሚታመን ጾሙ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ልደት በተለያየ ጊዜ የነበሩ ነቢያት የጾሙት ጾም ስለሆነ የነቢያት ጾም (ጾመ ነቢያት) ይባላል።

የነቢያት ጾም ከሰባቱ አጽዋማት የመጀመሪያው ጾም ነው። የጾሙን አጀማመር ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕግ በተቀበለ ጊዜ ከጾመው ጾም ጋር የሚያያይዙት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አሉ (ዘጸግ.፴፥፴) ይልቁንም ለዘመነ ሥጋዌ ይቀርቡ የነበሩት እነ ኢሳይያስ እና ኤርምያስ፡ እነ ዳንኤል እና ሌሎችም በዘመናቸው የነበሩ ነቢያት መጾም ብቻ ሳይሆን የእውነተኛ ጾም አፈፃፀም እንዴት መሆን እንዳለበት የተናገሩበት ጾም ስለሆነ በጾመ ነቢያት ስም ተሰይሟል። (ኢ.ሳ.፶፰፥፩)

፪. ጾመ ስብከት

ነቢያት የእግዚአብሔርን ልጅ ሰው መሆን ያስተማሩበት ጾም ስለ ሆነ ጾመ ስብከት ይባላል።

፫. ጾመ ልደት

የጾሙ መጨረሻ (ፋሲካው) የእግዚአብሔር ልጅ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደበት ቀን ስለሆነ ጾመ ልደት ይባላል።

፬. ጾመ ማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን ከመውለዷ በፊት ስለ ጾመችው ጾመ ማርያም ይባላል።

ጾመ ነቢያት በየዓመቱ ኅዳር አሥራ አምስት ቀን ይጀመራል። በአጀማመሩ በኩል በርካታ አከራካሪ ነጥቦች የነበሩ ሲሆን የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት በየ ዓመቱ ኅዳር አሥራ አምስት ተጀምሮ ፋሲካው መጨረሻው በሦስቱ ዘመናት ማለት በዘመነ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ሉቃስ ጨርሶ ዮሐንስ በሚረከብበት (በዘመነ ዮሐንስ) ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ነው።

፫. የነቢያትን ጾም ለምን እንጾማለን?

ይህ ጥያቄ ለነቢያት ጾም ብቻ ሳይሆን በጾም ትምህርት ሁሉ ከሚነሡ አጨቃጫቂ የጾም ጥያቄዎች አንዱ ነው።

ይህ ማለት ማንኛውም ጾም ለምን እንጾማለን? ማለት ነው። በፊደሉ አነጋገር የጾም ጥቅሙ ምንድን ነው? ማለት ነው።

ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመቀበል እንደ ጾመ (ዘጸ.፴፥፴) ነቢያት በጾም እና በጸሎት ይጠብቁት የነበረውን የእግዚአብሔርን ልጅ ልደት በጾምና በጸሎት መጠበቅ እንዳለብን በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ታዘዝን ነው። (ፍትሐ ነገ.ፍ.መ አንቀጽ ፲፭)።

ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org


# ሐመረ ጥበብ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ ማስተባበርያ መምሪያ በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፲፩ - ጥር - መጋቢት ፲፱፻፺፬ ዓ.ም


## ማውጫ


በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን? . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪

ቃለ በረከት

ሰው የሌላውን ሕይወት የማጥፋት መብት የለውም . . . . . . . . . . . . ፫

«አሮን እጉከ ይኩንከ አፈ» የምንለው ልዑክ አይኖረንም . . . . . . . . . . ፭

አቀድም አእኵቶቶ ለእግዚአብሔር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፯

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

ትምህርተ ሕፃናት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፩

ትምህርተ ሃይማኖት

የማይለያዩ ሁለት ነገሮች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬

የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የትንቢት ቀጠሮ . . . . . . . . . . . ፲፯

ቅዱስ ላሊበላና ቅድስት መስቀል ክብራ . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፩

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

የ፳ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ሰውና ጥያቄው . . . . . . . . . . . . . . . ፳፬

ልማት በቤተ ክርስቲያን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፮

ከወጣቱ ለወጣቱ

ኃጢአትን የምናሸንፈው ሕግን በመጠበቅ ነው . . . . . . . . . . . . . ፳፱

ዜና መጽሔት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፩

መድፍነ ፀር

ታቦት (ጽላት) እንዲቀረፅ ማን ፈቀደ? . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፪

እስትጉቡእ

ጾመ ነቢያት (የነቢያት ጾም) . . . . . . . . . . . . . . የፊት ለፊት ሽፋን ውስጥ

ዘመነ ቅበላ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፫



### አርታዕያን (ኤዲተሮች)

መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ቀሲስ በላይ ተገኝ

### አዘጋጆች:-

ዋና አዘጋጅ መምህር ዕንቁባሕርይ ተከሥተ

ም/ዋና አዘጋጅ መልአከ ሰላም ኃ/ኢየሱስ ከበደ

☎ 562652፤ 550098፤ 550099 Ex. 46

✉ 81286 – አዲስ አበባ

## ርእሰ አንቀጽ

# በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?

«ወይቤሎ መንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ ሑር ወትልዎ ለዝ ሠረገላ ወሮጸ ፊልጶስ ወበጽሐ ወሰምዖ ያነብብ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነቢይ ወይቤሎ ፊልጶስ ተአምርኑ እንከ ዘታነብብ። ወይቤሎ ኀፅው በአይቴ አእምር ለእመአልቦ ዘመሀረኒ»።

«መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ይህን ሠረገላ ሂድና ተከተለው አለው። ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማውና በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህ? አለው ጃንደረባውም የሚያስተምረኝ ሳይኖር ይህ እንዴት አውቀዋለሁ አለው።» (የሐዋ.ሥራ ም.፰፡፳፱–፴፪)

እኛም ሆነ ሌላው የክርስትና ዓለም እንደሚያውቀው ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀች ሀገር እንደሆነች ብዙ ነቢያት በትንቢታቸው ደጋግመው አንስተዋታል። በጽሑፋቸውም በብዕራቸው ደጋግመውናቀልመውታል።

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ፵፫ ጊዜ በላይ ስምዋ የተጠቀሰ ሲሆን ከክርስትና እምነት በፊት ማለትም በብሉይ ኪዳን ዘመን በአንድ አምላክ ታምን እንደ ነበረ በብዙ ቦታ ተጠቅሳለች።

በተለይ ከ፩ ሺህ ፲፫–፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረችው የኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ (ንግሥተ ሳባ) የሰሎሞንን ጥበብና ዜና ለማየት በዘመኑ የነበረው የኢትዮጵያን ሥልጣኔ ለማስተዋወቅ የብሉይ ኪዳንንም እምነትና ሥርዓትን ትምህርቱን ከመሠረቱ ለመረዳት ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መሄድዋን በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ምዕ.፲ ቁ.፩–፲፪። በዜና መዋዕል ካልእ. ምዕ.፱ ቁ.፩–፲፪ ተመዝግቦ ስለሚገኝ የታሪክ እውነትነቱን ያረጋግጧል። ንጉሥ ሰሎሞንም ለኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ የወደደችውን ሁሉ እንደሰጣት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል።

ከእነዚህም ስጦታዎች አንዱ በምድረ ጋዛ የጎዝ ማሳረፊያ ቦታ ነው። ይህ ቦታ በርስትነት እንደ ሰጣት በታሪክ መጻሕፍት ታትቷል። ከዚህ በላይ ለመግለጽ የተገደድነው (የተሞከረው) ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ያላት ድርሻ ለመግለጽ ነው።

ኢትዮጵያ ከ፪ ሺ፱ ፩፻፵፩ እስከ ፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ልቦና ከ፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እስከ ፴፬ ዓ.ም በሕገ ኦሪት፣ እየተመራች አምልኮተ እግዚአብሔርን ስትፈጽም ኖራ በ፴፬ ዓ.ም ወደ ክርስትናው እምነት ተሻግራለች።

ኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት የተቀበለችው በመጀመሪያው ምእተ ዓመት በ፴፬ ዓ.ም በጎጽዋ ለህንዳኬ (ጃንደረባ) አማካይነት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ታዞ (ተመርቶ) የኢትዮጵያ ንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረው ጃንደረባው በበዓለ ሐምሳ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሥርዓተ አምልኮቱን ፈጽሞ በምድረ ጋዛ በሠረገላ ተቀምጦ እየሄደ መጽሐፈ ኢሳይያስ ምዕ.፶፫ ቁ.፯ ያለውን እያነበበ እያለ «የምታነበውን ታስተውለዋለህን?» ብሎ ጠየቀው። ጃንደረባውም «የሚያስተምረኝ ሳይኖር ይህ እንዴት አውቀዋለሁ?» አለው።

ከዚህ በኋላ ጃንደረባውና ቅዱስ ፊልጶስ ሁለቱ በሠረገላው ተቀመጡ። ፊልጶስም «አፉን ከፈተ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ሰበከለት። በመንገድም ሲሄዱ ውሃ ወደ አለበት ቦታ ደረሱ ጃንደረባውም «እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው?» አለው።

ፊልጶስም «በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው። መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ። ሠረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ። ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም ከውኃው ከወጣ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም ደስ ብሎት መንገዱን ሄደ» (የሐዋ.ሥራ ም.፰፡፳፮–፵)።

ይህ በግብረ መንፈስ ቅዱስ የተመሠረተው አስደናቂና እውነተኛ ታሪክ ኢትዮጵያ ከዓለም ሕዝብ በፊት ከአይሁድ ቀጥላ እምነተ ክርስትናን በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መቀበልዋን ያረጋግጣል።

ጃንደረባው በሐዋርያት ዘመን ወንጌልን ለኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ማስተማሩ ታምኗል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስ ኀፅው (ጃንደረባው) ከተጠመቀ በኋላ ወንጌልን ማስተማሩ መስክሯል።

ከጃንደረባው ቀጥሎም ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን መስበኩ በጥንት የቤተ ክርስቲያን ጸሐፊዎች በእነሩፊኖስና ሶቅራጥስ ተመሥክሮአል። በጃንደረባው የተሰበከው ሃይማኖት በ፫፻፴ ዓ.ም በከሣቴ ብርሃን ሰላማ ዘመን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ።

በዚህም መሠረት በጃንደረባው የተቀጣጠለው የእምነት ችቦ እስከ አሁን ድረስ በምድረ አፍሪካ እያበራ ይገኛል። ኢትዮጵያንም የክርስትና ደሴት ከማስባሉ በላይ ሕዝቡም ሕዝበ እግዚአብሔር አሠኝቷል።

ከላይ እንደተገለጸው ዛሬ በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን የምናከብረው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት ጃንደረባው በተለመልን መልካም ጎዳና መሆኑን ልብ ማለት ይገባል።

ታሪካችንን፣ ክብራችንን፣ ሃይማኖታችንን የምንወድ ያህል የራሳችን ቅዱሳን የምንወድ ስንቶቻችን ነን?

እንደዚህ ለማለት ያበቃን ጃንደረባው ባኮስ (መልከ ጼዴቅ) ለገዛ ወገኖቹ ኢትዮጵያውያን የክርስትና ጀማሪ መሆኑ እየታወቀ አንድም በስሙ መታሰቢያ ሳይደረግለት፤ ቤተ ክርስቲያን ሳይታነጽለት መቅረቱ በጣም የሚያስገርም ስለሆነ ነው።

ደግነቱ የጃንደረባው ባኮስ (መልከ ጼዴቅ) ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአልና ሰው መታሰቢያ ሠራለት አልሠራለት ትርጉሙ የዚያን ያህል ነው።

ይህ ተግባር የተለመደ ይመስላል ለምሳሌ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ያሬድ የበለጠ ሐዋርያና ባለውለታ የለም።

ነገር ግን ቅዱስ ያሬድ በልበ ሊቃውንት ከመታሰቡ በቀር ከ፴፪.፳፻፴፯ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በስሙ የታነጸለት ከ፪ አብያተ ክርስቲያናት አይበልጡም።

ይህ የሚያስገነዝበን የራሳችን ወገኖች ለሆኑ ቅዱሳን ያለን አመለካከትና አፍቅሮት ከአፍ ያላለፈ በተግባር ያልተተረጎመ ራእይ መሆኑን ይገልጻል።

ለወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እና ምእመናን ስለዚህ ጉዳይ በጥልቀትና በስፋት ሊያስቡበት ይገባል እንላለን። እንግዲህ ዘወትር የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀትን ስናከብር ርስታችን ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን እንደምናስብ ሁሉ፣ የኢትዮጵያዊ ጃንደረባ መጠመቅና ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ማምጣቱን ስናበሥር ከዚሁ ጋር በኢየሩሳሌም (እስራኤል) ያለው ምድራዊ ርስታችንን ለማስከበር ከአባታችን ጋር አብረን መሰለፍ ይኖርብናል። ✣

## ቃለ በረከት

# ሰው የሌላውን ሕይወት የማጥፋት መብት የለውም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በዓለም የንግድ ማዕከልና በፔንታጎን በደረሰው ጥቃት ሕይወታቸው ላለፈው ንፁሐን አሜሪካውያንና የሌላ አህጉር ዜጎች በተካሔደው የመታሰቢያ ሥርዓተ ጸሎት ላይ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ያስተላለፉት መልእክት



ክቡር ሚስተር ቲቦር ናጂ

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር

ክቡራትና ክቡራን

የእግዚአብሔር ቤተሰቦች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ሁላችሁም በዛሬው ዕለት ከቅርብ ጊዜ በፊት በዓለም የንግድ ማዕከልና በፔንታጎን በደረሰው አሳዛኝ ጥቃት ሕይወታቸው ላለፈው ንፁሐን አሜሪካውያንና የሌላ አህጉር ዜጎች በምናደርገው መታሰቢያ ሥርዓተ ጸሎት ላይ ለመገኘት እንኳን ደህና መጣችሁ። እግዚአብ ሔር አምላክ ለሰው ልጅ የሰጠው ሕይወት የተቀደሰ ነው። ፈጣሪያችን «አትግደል» የሚል ትእዛዝ ሰጥቶናል (ዘዳ.፭፡፲፫)።

በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረና ለባዊት ነፍስና አስተዋይ አእምሮ የተሰጠው የሰው ልጅ ማስተዋል፣ ፍትር፣ ርኅራኄ፣ ትሕግስትና ጥበብ ኖሮት እግዚአብሔር እንዳዘዘው ቅዱስ ይሆን ዘንድ ሊጥር ይገ ባል። ስለዚህ ማንም ሰው የሌላውን ሕይወት የማጥፋት መብት የለውም። ሁላችንንም እግዚአብ ሔር አምላክ በሰላምና በስምምነት እንኖር ዘንድ ፈጥሮናል። ስለዚህ የባሕል፣ የታሪክና የእምነት ልዩነት ሳይገድበን በሰላም አብሮ መኖርን ተግባራዊ ልናደርገው ይገባል። ለምድራዊ ኑሮአችን እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ሦስት ነገሮች አሉ። እነዚህም፦

፩. በሰላም አብሮ መኖር

፪. በሰላም አብሮ መኖር

፫. በሰላም አብሮ መኖር ናቸው።

የዓለም መንግሥታት ሁሉ በሰላም አብሮ መኖርን በምድር ለማስፈን በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ ፊት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። የሰው ልጅ ሁሉ በየትኛውም ስፍራ ባለ ሕዝብ ላይ የሚቃጣ የሽብር ድርጊት ፍጹም ስህተትና በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል። ማንኛውም ስሚታዊ አመለካከት ሽብርን ከቶውንም ቅዱስ ሊያደርገው አይችልም። ስለዚህ የሰው ልጅ ሽብርን ሊያወግዝና ከሥሩም ነቅሎ ለማጥፋት በአንድነት ሊቆም ይገባል። ምክንያቱም ሽብር የሁላችን ፈጣሪ፣ ቅዱስ፣ ሕይወት ሰጭ፣ ዘለዓለማዊና የርኅራኄ ምንጭ በሆነው በእግዚአብሔር ዘንድ የተነቀፈ ነው።

ክቡር ሆይ፤

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች፤

በአሜሪካ ሕዝብና መንግሥት ላይ የደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት በጥልቅ ኃዘን በምናስበበት በተለይም ሕይወታቸውን ያጡትን በሺህ የሚቈጠሩ ንጹሐን ዜጎች ጸሎት በምናደርግበት ወቅት ለቤተሰቦቻቸው ጥልቅ ኃዘናችንን እንገልፃለን። በሙሉ ልብም የኃዘናቸው ተካፋይ ነን። የኃዘን ድባብ ባጠላበት በዚህ ሰዓት ቸርና ሩኅሩኅ እግዚአ ብሔር መጽናናቱን ሁሉ እንዲሰጣቸው እንመኛለን። በምድር ያሉትን ሕዝብና መንግሥታት ሁሉ ልናስብ ይገባል። አሜሪካ ግን ከመላው ዓለም አያሌ ሰዎች ከነልጆቻቸው መጠለያ፣ ጥበቃና የተሻለ ሕይወት ፍለጋ የሚጎዙበት ነው።

የሙታንን ነፍሳት እግዚአብሔር በሰላም ያሳርፍ፤

የኃዘንተኞችን ልብ እግዚአብሔር ያጽናናልን፤

ለአሜሪካ መንግሥትና ሕዝብ ጥንካሬውንና መጽናናትን ይስጥልን፤

ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ሰላም በዓለም ላይ ይስፈን፤

እግዚአብሔር አምላክ ዓለማችንን ይባርክ፤



www.ethiopianorthodox.org

## Message of His Holiness Abune Paulos Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum and Echegue of the See of St. Teklehaimanot delivered at the memorial service for the thousands of Americans and other innocent victims who lost their lives as a result of the the attack on the World Trade Center and the Pentagon.

*Holy Trinity Cathedral, September 20/2001, Meskerem 10/1994 E.C*

Your Excellency Mr. Tibor P. Nagy,

Ambassador of the U.S.A. to Ethiopia

Excellencies and Children of God

On behalf of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, I welcome all of you to this solemn memorial prayer service in honor of those innocent Americans and other nationalities who lost their dear lives in the tragic attack at the World Trade Center and the Pentagon.

Life bestowed by God to men and women is most sacred and holy. God our creator has commanded us all "thou shall not kill" (Ex 20:13). Men and women created in the image and likeness of God and endowed with a gift of rational soul and mind must act rationally, lovingly, mercifully, patiently and with wisdom and try to be holy as God has commanded them to be.

In light of this Divine gift and Commandment no single creature has the right to take the life of another. We are all created by the Lord God to live in peace and harmony in this world. Therefore, inspite of our cultural, historical, and confessional differences we all have to exercise peaceful co-existence. In fact, in our world there are three unavoidable important factors for our earthly existence. These are:- 1. Peaceful Co-existence 2. Peaceful Co-existence 3. Peaceful Co-existence.

The nations of the world have the prime responsibility before to see to it that peaceful co-existence prevails on earth.

Mankind must be fully aware that terror against people anywhere is utterly wrong and evil in the eyes of God. No reason or rhetoric, however passionate and emotion-loaded can make terror holy. Henceforth mankind should condemn terrorism and must stand together to uproot it. In the eyes of God Almighty, creator of us all, who is Holy, life-giving, eternal and the boundless source of mercy terrorism is repulsive.

Your excellency

Dear Children of God

As we reflect with profound sorrow about the great tragedy which befell the Americans as a nation, people and Government and especially the thousands of innocent lives who are either dead or unaccounted for, we would like to express our deep heartfelt condolences to their families and loved ones. We fully share their grief and sorrow. May the merciful God console and uplift their hearts at this dark hour of deep and poignant distress. We ought to be concerned about all nations on earth but America is the home where people from the entire world flock to seeking shelter, protection and btter life.

May God rest in peace the souls of the dead

May God console the hearts of the sorrowful

May God give strength and comfort to the American Nation and its people

May the eternal peace of God reign on earth

May the merciful God bless our world.



# አሮን እጉከ ይኩንከ አፈ የምንለው ልዑክ አይኖረንም

ከብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የጅማ የከፋ ሸካ ቤንችና ማጂ አኅጉረ ስብከት ጳጳስ ለ፳ኛው አጠቃላይ መንፈሳዊ ሰ!!ካ ጉባኤ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ



በሚቀጥል ልዩ ዓውደ ጥናት እንድንማማር ለፈቀደልን ቸሩ ፈጣሪያችን ክብርና ምስጋና ይግባው እላለሁ።

ይህ ዐውደ ጥናት ለ፬ ቀናት ባካሄድነው ሀገር አቀፍ የሰበካ ጉባኤ ከዋናው ማዕከላችን ጠቅላይ ቤተ ክህነትና ከየሀገረ ስብከቱ የቀረቡ የ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ዓመታዊ የሥራ ውጤት መግለጫ ሪፖርቶችን ገምግመን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ባየን በት ማግስት ለ፭ ቀናት ቅዳሜና እሑድ እንዲቀጥል የተደረገበት ዓላማ ጥንካሬውን አጎልብተን ድክመቶቻችንን አርመን ቤተ ክርስቲያናችንን በምጣኔ ሀብት የበለጠ ለማሳደግና የቤተ ክርስቲያናችንን ሐዋርያዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ ለማጠናከር በቃለ አዋዲው በአንቀጽ ፫ እና ፯ የተደነገገውን ዓላማና ተግባር በጥራት ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚያስችል ዝግጅት ለማድረግ እንደ ሆነ ልንገነዘብ ይገባል።

በዚህ ዓላማ መሠረትም የቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ ተልዕኮን በሚገባ ለመወጣት የተለያዩ የሥራ ክፍሎችንና መዋቅሮችን በየደረጃው የበለጠ እንዲጠናከሩ ማድረግ ተቀዳሚ የተልዕኳችን አካል እንደ ሆነ ለማስታወስ እወዳለሁ።

የምንፈልገውን የቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት ማረጋገጥ የምንችለው ሁላችንም በየተልዕኮአችን በስፋት ስንንቀሳቀስና በርትተን ተልዕኮአችንን ስንወጣ እንደ ሆነ የሚጠራጠር አይኖርም።

ከዚህ ቀደም እንደሚታወቀው ሰበካ ጉባኤን በየደረጃው ለማዋቀርና ለማጠናከር ብሎም አሁን በሚታየው ደረጃ ለማቈየት ሰፊ ጥረት መደረጉንና ጥረቱን ውጤታማ ለማድረግም በዓመት ሁለት ጊዜያት የሰበካ ጉባኤያት የስምሪት መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ በየሀገረ ስብከቱ እስከ ጠረፍ ቤተ ክርስቲያን ድረስ ያዳረሰ የቅስቀሳና የትምህርት ፕሮግራም በስፋት ተዘርግቶ ሲካሄድ በነበረበት ጊዜ የበለጠ ክርስቲያናዊ መነሳሳትን የፈጠረ ውጤታማ እንቅስቃሴ እንደ ነበረን የሚታወቅ ነው።

ይሁን እንጂ በዓመት ሁለት ጊዜ ሲካሄድ የነበረው የትምህርት ሥርጭትና የሥራ ግምገማ ስምሪት ከ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ለ፲ ዓመታት ተቋርጦ በመቈየቱ በአሁኑ ፳ኛው ሀገር አቀፍ ጉባኤያችን የገመገምነው ውጤት በዚህ ዕድሜ ማየት ከነበረብን ዕድገት በታች እንደ ሆነ መገመት አያዳግትም።

ሳይቋረጥ መቀጠል የነበረበት የሥራ ስምሪት እንዲቆም የተደረገ

## የዐውደ ጥናቱ ዓላማና ይዘት

«አስተጋብአሙ እምበሐውርት፤ እምጽባሕ ወእምዓረብ ወመስዕ ወባሕር» (መዝ.፲፡፫) «ከምሥራቅና ከምዕራብ፤ ከሰሜንና ከደቡብ ከየሀገሩ አሰባሰባቸው» በማለት ነቢዩ ዳዊት እንደ ተናገረው ሁሉ ከሁሉ በፊት በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ቦታ ከምትወሳው ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአራቱ መዓዘናት የየመንበረ ጵጵስና አህጉረ ስብከትና ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኙት አህጉረ ስብከት በሰላም አሰባስቦ በዚህ ብሔራዊ ዓመታዊ ጉባኤ በቤተ ክርስቲያናችን ልማትና ዕድገት ለ፬ ቀናት ስንወያይ ሰንበትን በተ ጨማሪ ለ፪ ቀናት



www.ethiopianorthodox.org

ውም ሲላኩ ከነበሩት ልዑካን መካከል የአንዳንዶቹ የችሎታ ብቃት ማነስና አንዳንድ ሀገረ ስብከቶች ድክመታቸው በስምሪቱ እንዳይታይባቸው ሲሉ ለስምሪቱ መቀጠል ተገቢ ድጋፍ ባለማሳየታቸው ምክንያት እንደ ነበረ ታውቋል።

አሁን ግን ተፈላጊ ያልሆኑ ድክመቶችን እያረሙ የተሻለ ብቃት አላቸው በሚባሉ ልዑካን ስምሪቱ እንዲቀጥል ስለ ተወሰነና የመጀመሪያ ዙር ስምሪት ፲፩ ቤቅርቡ ስለሚደረግ ለዚሁ ስምሪት የተመረጡ የመንበረ ፓትርያርክ ልዑካን ግንዛቤ እንዲሰንቁ የዚህ ዐውደ ጥናት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ተደርጓል።

ስለሆነም ልዑካኑም ሆናችሁ የየሀገረ ስብከቱ የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ለዚህች ታላቅና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ላላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኛ ሆኖ መሄድ በጣት የያዙት ወርቅ ሳይሆን እጅግ በጣም ከፍተኛ ክብር ያለው ስለሆነ ከብዙ ነገር መቈጠብንና ከተራ ቦታ ያለመገኘትን ይጠይቃል።

ነገር ግን በስም ብቻ መኖር፣ በታሪክ ብቻ መክበር ስለማይቻል ይህችን ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ለማስቻል እያንዳንዱ ልዑክ በተሰለፈበት የሥራ መስክ ቅኑት እንደ ገብሬ ፅሙድ እንደ በሬ ሆኖ መሥራት ይጠበቅበታል።

የስምሪቱን የትምህርት ስርጭትና የተልዕኮውን ዓላማ በተገቢው መልክ መግለጽ እንዲያስችለው ለስምሪት ልዑካን በሚመረጠው በእያንዳንዱ የትምህርት ርእስ የተሟላ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልገዋል።

«ኵሉ አመክሩ ወሠናየ ግበሩ» እንደ ተባለው ሁሉ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ያጋጠመውን ሁሉ ገምግሞ አግራጩን የመጠቀም መብቱ በተሰፋበት በአሁኑ ወቅት ሰሚ ሳይሆን የሚናገርና የሚከራከር፣ የሚማር ሳይሆን የሚያስትምርና የሚያመሠጥር፣ በተለያየ መልኩ በሚገለጽበት በአሁኑ ጊዜ በዚህ ዓይነቱ የሥራ ዕድል ለመሠማራት አጥብቆ መታጠቅና አሟልቶ መሠነቅ አስፈላጊና ተገቢ ይሆናል።

«አሮን እኁከ ይኩንከ አፈ»
የምንለው ልዑክ የለንም።»

ነገር ግን በስም ብቻ መኖር፣ በታሪክ ብቻ መክበር ስለማይቻል ይህችን ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ለማስቻል እያንዳንዱ ልዑክ በተሰለፈበት የሥራ መስክ ቅኑት እንደ ገበሬ ፅሙድ እንደ በሬ ሆኖ መሥራት ይጠበቅበታል።

እንዲኖረንም አንፈልግም ገበሬ የታረሰው መሬት ሁሉ ስንዴ ያበቅላል ብሎ አይዘራም የሚዘራውን ዘርና የሚቀበለውን አፈር ለይቶና ተረድቶ ነው የሚዘራው በመሆኑም እያንዳንዱ ዘር ፴ እና ፷ ከዚያም በላይ የእጥፍ እጥፍ እያፈራ ዓለሙን ሲመግበው ይኖራል።

እያንዳንዱ ልዑክ በቂ የሆነ ተሳታፊ የሚቀበለው ቅድመ ዝግጅት እንዲኖርው ሆኖ በየሀገረ ስብከቱም በሚደረገው የስምሪት አውደ ጥናት የተገኙትና የትምህርት እድሉን ለመሳተፍ ጊዜና ቦታ የገጠማቸው ካህናት፣ ምእመናንና ወጣቶች በሚተላለፈው ጥልቀትና ምጥቀት ያለው የትምህርት ስርጭት ረክተውና ስሜታቸው ተማርከ «ምንተ ንግበር» መምህር ሆይ ምን እናድርግ? የሚል ጥያቄ እስከሚያቀርቡ ድረስ የሚጋብዛቸው መሆን ይኖርበታል።

ቤተ ክርስቲያናችን የመጻሕፍት እጥረት የለባትም የምሁራን ድህም አይደለችም። ሳይማሩ ተምረናል፣ ሳያውቁ እናውቃለን፣ ሳይላኩ ተልከናል የሚሉ አፈጮሌዎች የሉባትም ማለት ግን አይቻልም።

ይሁን እንጂ ከአሁን በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት የተልዕኮውን ዓላማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም በቂ ችሎታና የትምህርት ዝግጅት ሳይኖረን በስምሪቱ መርሐ ግብር በመሳተፍ አቀራረባችን ያልተስተካከለና የትምህርት ዝግጅታችን ያልተሟላ ሆኖ በመገኘቱ በስምሪቱ ዐውደ ጥናት ተሳታፊዎች በሚፈጠረው ቅሬታ ከአሁን ቀደም ስምሪቱ እንዲቆም ያስገደዱ ምክንያቶች ዳግም እንዲፈጠሩ አንፈልግም።

«አሮን እኁከ ይኩንከ አፈ» የምንለው ልዑክ አይኖረንም፣ እንዲኖረንም አንፈልግም ለማለት የተገደድነውም ሥምሪቱን ያለ ምክንያት መፈጸምና ማስፈጸም የሁላችሁም የጋራ ጥረት እንደሆነ መግለጽ ስለ አለበት ነው።

ስለዚህ ከላይ እንደ ተገለጸው ቤተ ክርስቲያናችን የመጻሕፍት መድበል ስለ ሆነችና የምሁራንም እጥረት ስለሌለብን ማንበብና መጠየቅ ለዝገጅታችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው እየገለጽኩ የነቢያትን ትንቢትና የሐዋርያትን ስብከት የተቀበለ አምላክ ተልእኮአችን እንዲያቃናልን በጸሎት እንጠይቃለን።

«ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን
ጋር ይሁን»




# «አቀድም አእኵቶቶ ለእግዚአብሔር...» (ሮሜ.፩፥፰)

ከአባ ገሪማ

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና

የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ስለ በዓለ ጥምቀቱ የቀረበ ትምህርት



ለ፳፻፲፩ ዓ.ም ሁላችንንም በሕይወትና በጤንነት አድርሶ በዓለ ጥምቀቱን ለማክበር ላበቃን አምላክ በቅድሚያ ምስጋና እናቀርባለን።

የዛሬ ፲፫ ቀን፣ የ፳፻፲፩ ዓ.ም በዓለ ልደቱን በያለንበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት አክብረናል።

አሁንም የ፳፻፲፩ ዓ.ም በዓለ ጥምቀቱን በየዓመቱ እንደሚደረገው ሁሉ በታላቅ ሥነ ሥርዓት በማክበር ላይ እንገኛለን።

አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን እንደ ተፈጸመ ዓለምን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ አምላክ ሰው ሁኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ብርሃን ልደቱን የገለጠው እንደ እኛ አቈጣጠር ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ስለ ሆነ፤ ይህ ዕለት በሁላችንም ዘንድ ሲከበር የሚኖር ታላቅ በዓል ነው። ስለ ምሥጢረ ሥጋዌው ተናጋሪ ቢናገር፤ ሰሚውም ቢሰማ ሁሉም አለኝታውና ተስፋው የላቀ ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያናችን ከበዓለ ልደቱ ቀጥላ ከቅፅረ ቤተ ክርስቲያን ወጥታ በዱር፣ በሜዳ፣ በወንዝ ዳርቻ በጥር ፲ና ፲፩ ቀን በየዓመቱ በታላቅ ሥነ ሥርዓት የምታከብረው በዓለ ጥምቀቱን ነው። ይህም በሌላ ዘይቤ ኤጲፋንያ ተብሎ ይጠራል፤ ኤጲፋንያም መገለጥ ማለት ነው።

«ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከናዝሬት ገሊላ መጥምቁ ዮሐንስ ወደ አለበት ወደ ዮርዳኖስ መጣ» ተብሎ በወንጌል ተጽፏል። (ማቴ.፫፥፲፫)

የዮርዳኖስ ወራጅ ውሀ ከላይ ከሔርሞን ወይንም ከሰሎሞን ተራራ መንጭቶ ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚጎርፍ፤ በመጨረሻም ወደ ባሕረ ሉጥ፣ ወይንም ሙት ባሕር ወይንም ጨው ባሕር ገብቶ፤ ተውጦ የሚቀር ነው። ከዚህ በመነሣት ዮሐንስ መጥምቅ ከሙት ባሕር፤ ጨው ባሕር፤ ባሕረ ሉጥ መዳረሻ አንሥቶ በሰማርያ አንፃር እስከሚገኘው በሳሌም አቅራቢያ ሄኖን እስከሚባለው በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ሲያስተምርና ሲያጠምቅ የነበረበት አካባቢ ነበር። (ዮሐ.፫፥፳፫)

ሳሌምና ሄኖንም ተቀራርበው የሚገኙ በምድረ ሰማርያ፣ ሴኬም ካለ ከአዘቅተ ያዕቆብ ወደ ምሥራቅ ሲልም በዮርዳኖስ ማዶ ቢታንያና ቤተ ራባ ይገኛሉ። (ዮሐ.፩፥፳፰)

ዮሐንስ መጥምቅ በዚያን ወቅት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች እየታየ በፈለገ ዮርዳኖስ የንስሐ ጥምቀትን ያጠምቅ ስለ ነበር እስራኤላውያን በብዛት ወደ እርሱ እየመጡ ይጠመቁ ነበር።

መጥምቁ ዮሐንስ ከመነሣቱ በፊት ለተወሰነ ጊዜ በቤተ እስራኤል ነቢይ ባለመገኘቱ እስራኤላውያን ትንቢት የሚናገርላቸው፣ ተአምራት የሚያሳያቸው ነቢይ እጥተውናረው ነበርና መጥምቁ ዮሐንስ በነቢይነት ሲነሣ ዝናውን የሰሙ ሁሉ ትምህርቱን ለመስማትና የንስሐ ጥምቀትን ለመጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ ይጓዙ ነበር።

ከላይ እንደ ተገለጸው እስራኤላውያን የነቢዩ የሚልክያስን ድምፅ ከሰሙ አምስት መቶ ዘመን በመሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል ከነቢይ አንደበት ለመስማት ይጓጉ ነበር።

መቃብያን ከቤተ እስራኤል ጠላቶች ጋር ከተዋጉ ሁለት መቶ ዘመን አልፏል።

በጊዜውም የሮሜ መንግሥት ወታደሮች የአማልክት ስሞች የተጻፉባቸውን ባንዲራዎች በማውለብለብ ከቤተ መቅደሱ አጠገብ ወደሚገኘው ሠፈራቸው በኢየሩሳሌም ቅድስት ከተማ አውራ ጎዳናዎች ሲያመሩ ይታዩ ነበር።

ይህ ሁሉ በሆነበት ጊዜ ነው ቤተ እስራኤልን ከሮም መንግሥት የአገዛዝ ቀንበር ነፃ የሚያወጣ ማን ይሆን የሚለው ጥያቄ በሁሉም ቤተ እስራኤል አእምሮ የሚጉላላ ሐሳብ ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የታወቁት ቴዎዳስና ሀገሩ ገሊላ የሆነው ይሁዳ በሮማውያን



www.ethiopianorthodox.org

አገዛዝ ላይ አምፀው በመነሣት ሀገራቸውን ከርማውያን አገዛዝ ነፃ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገው ነበር። ይሁንና ጊዜው ሳያመች ቀርቶ ቴዎዳስና ይሁዳ ተማርከው (ተይዘው) ሲገደሉ ተከታዮቻቸውም በያሉ በት ተበታትነው ቀርተዋል። (የሐዋ.ሥራ ፭፥፴፮–፴፯)

ከዚህ ሁሉ በኋላ አንድ ሌላ ሰው የቤተ እስራኤል ዓርበኞች መናሐሪያ በሆነው በዮርዳኖስ በረሀ መነሣቱ ይነገራል።

መንገዱን ለማዘጋጀትና ቃል ኪዳኑን ለማወጅ እግዚአብሔር አስቀድሞ መልእክተኛውን ይልካል ብሎ ነቢዩ ሚልክያስ በተናገረው መሠረት (ሚልክያስ ፬፥፩–፮) ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ትንቢቱን ለመፈጸም መጥምቁ ዮሐንስ በጊዜው ጊዜ መጥቶ (ማቴ.፲፩፥፲፬፤ ማር.፩፥፪፤ ሉቃ.፪፥፲፯) የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም ሥራውን ጀመረ።

ይህ ሰው ቀደም ሲል ከተነሡት ነፃ አውጭ አርበኞች ሁሉ የተለየ አቋምና ጠባይ እንደ ነበረው ተነግሯል።

ይህ ሰው ልብሱ የግመል ጠጉር፣ ኑሮው እንደ ባሕታዊ የሆነ በዮርዳኖስ በረሃ አካባቢ እየተዘዋወረ «እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» በማለት የሚሰብክ እንጂ ተነሡ፣ እንነሣ፣ በማለት አመፅ እንዲካሔድ የሚያስተባብር ሰው አልነበረም።

በሐረገ ትውልዳቸው ይመኩና ራሳቸውን እንደ ልዩ ፍጥረት አድርገው ይቈጥሩ የነበሩትን ጸሐፍት ፈሪሳውያን ሊቃነ ካህናትን እናንተ የእፉኝት ልጆች በማለት ይገስፃቸው ነበር።

እነሆ ይህ በበረሃ እንዲህ እያለ የሚጮህ ሰው ድምፅ ነው።

- የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጥርጊያውንም አቅኑ፣
- አባጣ ጎባጣው ይስተካከል፣
- ጎድጓዳው ይሞላ፣
- ተራራው ኮረፍታው ዝቅ ይበል፣
- ጠማማው ይቅና፣
- ሸካራው ይለስልስ፣ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ፣ ይመልከት፣
- ሁለት ልብስ ያለው አንዱን አንድ ለሌለው ይስጥ፣
- ምግብ ያለውም ለሌለው ያካፍል፣
- ቀራጮች በሕግ ከታዘዘው በላይ አብልጠው እንዳይወስዱ (እንዳይቀርጡ)
- ወታደሮችም በማንም ሰው ላይ ግፍ እንዳይሠሩና ማንንም በሐሰት እንዳይከሱ፣ ለመኖርም ደመወዛቸው በቂ ነውና፣
- ተራው ሕዝብም ምንም እንኳ ድሀ ቢሆን ከዚያው ካለው ለሌለው እንዲያካፍል፣ ሁሉችም በጽድቅ ጎዳና እንዲመላለሱ የንስሐ ጥሪውን በማስማትና ኃጢአታቸውን በማናዘዝ ብዙዎችን በዮርዳኖስ ወንዝ የንስሐ ጥምቀትን ያጠምቅ ነበር።

ዮሐንስ መጥምቅ የኤልያስ መንፈስ አድሮበት ከሰው ተለይቶ በዮርዳኖስ በረሃ የተቀመጠ፣ በሐዲስ ኪዳን መነሻ በብሉይ ኪዳን መዳረሻ ስለ መንግሥተ እግዚአብሔር መቅረብ ማስተማር የጀመረ አምላክ ሰው ሁኖ መምጣቱን ለቤተ እስራኤል ያስተማረ፣ እስራኤላውያን ንስሐ በመግባት ጽድቅን መሥራት ይችሉ ዘንድ ያወጀ ነበር።

ይህም ሰው «ከሴቶች ልጆች የሚበልጠው የለም» ተብሎ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረለት ዮሐንስ መጥምቅ ነበር። (ማቴ.፲፩፥፲፩)

መጥምቁ ዮሐንስ እንደ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቃል በስተርጅና ከዘካርያስና ከኤልሳቤጥ የተወለደ፣ ናዝራዊ በመሆን በምድረ በዳ ያደገ፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሁኖ ሕዝበ እስራኤልን ለንስሐ ያዘጋጀ፣ ነቢየ ልዑል የእግዚአብሔር መንገድ ጠራጊና አዋጅ ነጋሪ ተባለ። ያም ጊዜ አምላክ ሰው ሁኖ በሥጋ ተገልጦ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን የሚያመለክት ነበር።

ያ ዘመን ሙሴ በእሪት የጻፈለት፣ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት፣ ሱባኤ የተቈጠረለት፣ ተስፋ የተያዘለት፣ ቃል ኪዳን የተገባለት ጊዜው ደርሶ በጊዜው ጊዜ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሁኖ በዳዊት ከተማ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ ተወልዶ በጥበብና በመንፈስ አድጎ ትምህርቱንና ተአምራቱን ለመጀመር ጊዜው እንደ ደረሰ አውቆ በሠላሳ ዘመኑ በሠላሳ ዓመተ ምሕረት በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ብለው የጻፉት ወንጌላውያን ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ናቸው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በዮሐንስ እጅ የተጠመቀበትን መሠረት በማድረግ በየዓመቱ ጥር አሥር ለአሥራ አንድ ቀን አጥቢያ ታቦታተ ሕጉ በካህናት ተይዘው ወደ ሚዳ፣ ወንዝ ዳር በመሔድ በቅዳሴ፣ በውዳሴ፣ በዝማሬ፣ በሆታ፣ በዕልልታ፣ በከበሮ በጸናጽል፣ በእምቢልታ፣ በመሰንቆ፣ በአጀብ በዓለ ጥምቀቱን በታላቅ ሥነ ሥርዓት እናከብራለን።

ፈጣሪ በፍጡሩ እጅ ሊጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፣ ሰማያዊው በመሬታዊው ዮሐንስ መጥምቅ እጅ ተጠመቀ ማለት ሰሚውንና አንባቢውን ለጥያቄ የሚያነሣሣ መሆኑ ግልፅ ነው። ይሁንና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ፣ በፈለገ ዮርዳኖስ ሊጠመቅ የመጣው:-

- በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም፣
- ውሀውን ለመቀደስ፣
- ለጥምቀት ኃይልን ለመስጠት፣
- ለእኛም አርአያና ምሳሌ ለመሆን ነው እንጂ የንስሐ ጥምቀትን በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ አይደለም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የማስጠንቀቂያ ምሳሌነትን ይነግረናል።

«ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ፣ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፣ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፣ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፣ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበር። እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፣ በምድረ በዳ ወድቀዋልና» ይላል (፩ኛቆሮ.፲፥፩–፭)

ከዚህም ጋር በሐዋ.ሥራ ፩፥፭ ዮሐንስ በውሀ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» ይላል። ሙሴ እስራኤላውያንን በደመና በባሕር አጠመቃቸው። ዮሐንስም በውሀ አጠመቀ። በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቅ ግን ለሙሴና ለዮሐንስ ጌታ ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን እንረዳለን።

እስራኤላውያን በምድረ ግብፅ አራት መቶ ሠላሳ ዘመን በፈርዖኖች የጸና አገዛዝ ከወደቁ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በመልአኩ ተራዳኢነት፣ በታላቁ ሙሴ መሪነት፣ በብዙ ትዕምርትና ተአምራት ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ነፃ ወጥተው፣ ጠላቶቻቸው ሰጥመው በማየታቸው በባሕሩ ዳርቻ የነፃነት አደባባይ ሁነው «ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ሰቡሐ ዘተሰብሐ ፈረሰ ወመስተፅዕነ ወረወ ውስተ ባሕር» «ፈረሱንና ፈረሰኛውን አሽቀንጥሮ ወደ ባሕር የጣለ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን» በማለት የምስጋና ዝማሬን ለእግዚአብሔር አቅርበዋል። (ዘጸ.፲፭፥፩)

ከዝማሬውም በኋላ እስራኤላውያን በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ባደረጉት ሮሮ የአርባ ቀናቱ ጉዞ ወደ ዓርባ ዘመን ተለውጦ ዓርባ ዘመን ሙሉ በቃዴስ በረሀ የውጣ ውረድ ጉዞ ደከሙ።

በአራት መቶ ሠላሳ ዘመን የባርነት ኑሮአቸውም ሆነ በዓርባ ዘመኑ የበረሀ አድካሚ ጉዞ ከአባቶቻቸውና እናቶቻቸው የወረሱትን ሃይማኖት «የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ አድነን፣ ፍረድልን» ከማለት የተቈጠቡበት ጊዜ ባለመኖሩ እግዚአብሔር አምላካቸው፣ ጽኑ እምነታቸውን አይቶና ተመልክቶ በበረሀው ጉዞ እንዳሉ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ለመሪያቸው ለሙሴ ተገልጦ አሠርቱ ሕግጋትንና ትእዛዛትን የያዙ ሁለት የዕብነ በረድ ሠሌዳዎችን (ጽላትን) እንደ ሰጠውና ሙሴም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለእነዚህ ጽላት ማኅደር የሚሆን ታቦት በቦታው ማስቀመጡን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። (ዘጸ.፳፬፥፲፪–፲፰፣ ፳፭፥፲–፳፪)

በመሠረቱ ከዘመነ መሳፍንት ከሙሴና ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ይማጠኑባት፣ ከጠላትም ኃይል ይጠበቁባት የነበረችው የሕጉ ማደሪያ፣ የስሙ መጸፊያ የሆነችው ጽላተ ሙሴ ናት።

ሙሴ ከእግዚአብሔር ተጠርቶ ወደ ሲና ተራራ ወጥቶ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ከሰው ተለይቶ ከእህልና ውኃም ርቆ ከጾመ በኋላ ታቦተ ሕጉን ከእግዚአብሔር እጅ በመቀበል ሕጉን ለቤተ እስራኤል ሊያስተምር ችሏል። (ዘጸ.፱፥፳፪)

ጽላተ ሙሴ በዘመነ ሐዲስ ላለነው ክርስቲያናት መማፀኛ የሆነችው የመቢታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌዋ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ በረቂቅ ጥበቡ ቀደም ብሎ ጊዜው ሳይደርስ ያዘጋጃት ነበረች።

ምሳሌነቷም ጽላተ ሙሴ በማናቸውም ሁኔታ ሁሉ በጠበብት ያልተዘጋጀች፣ ቃሉም በግብር አምላካዊ ተጽፎ የተገኘ ነው። ቃሉ ያለ ጸሐፊ እጅ ተጽፎባት እንደ ተገኘ ሁሉ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ያለ ዘርዓ ብእሲ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በመዋሐድ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ያስረዳል።

ታቦት ከቤተ እስራኤል የነፃነትና የአምልኮት ታሪክ ጋር ተያይዞ የመጣ፣ አሠርቱ ቃላተ እሪት የተጻፈባቸው የሁለቱ ጽላት ማደሪያ የሆነ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጸንቶ ለሚኖረው ሕያው ቃል ኪዳን ምስክር ነው። (ዘጸ.፳፭፥፩–፳፪፣ ፵፥፳)

ከሲና ተራራ ጀምሮ እስራኤላውያን በሕይወታቸው ሁሉ ታቦት እሲዘው ሲጓዙ በሕይወት የኖሩ፣ ኃጢአት ሠርተው ሲያስቈጡትም፣ በረሃብ፣ በቸነፈር፣ በጦር ሜዳ በጠላት እጅ በመጣል ይቀጣቸው ነበር። ንስሐ ገብተው ሲለምኑትም ምሕረቱን፣ ቸርነቱን ያደርግላቸው እንደ ነበር የሙሴ መጻሕፍት ይነግሩናል።

ይኸውና እኛም ኢትዮጵያውያን ከሙሴ መጻሕፍት ባገኘነው ትውፊት መሠረት ታቦተ ሕጉን የእግዚአብሔርን ስም በመሸከም ስሙን በመጥራት በቅዳሴ፣ በውዳሴ፣ በዝማሬ በሆታ፣ በልልታ፣ በታላቅ ሥነ ሥርዓትና አጀብ መንፈሳውያን በዓላትን እናከብራለን። ለዚህም መታወቂያው ይህ የዛሬው የበዓላችን አከባበር ነው።

ከዚህም ጋር የሀገርን ድንበር የሚጥስ፣ የሚያፈርስ፣ ወገንን የሚያጠፋ ጠላት ሲመጣ እስራኤላውያን እንዳረጉትና እንደሚያደርጉት ሁሉ እኛም ኢትዮጵያውያን ደቂቀ እስራኤል ነንና አድርገናል፣ እናደርጋለንም። ለዚህም በቂ ጉሉህ መረጃ የሚሆነው በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም ባንድ ጀንበር ያበቃለት ታዋቂው የአድዋው ጦርነት ነው።

ሙሴ ከዓርባ ዓመታት የውጣ ውረድ ጉዞ በኋላ ስለ እግዚአብሔር አምላክነት የተቀኘውን መዝሙር ከዘመረና የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ ከባረከ በኋላ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስትምሥራቅ በሚገኘው በሞአብ ምድር ሞተ ተቀበረ ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። (ዘዳግ.፴፩፥፭–፮)

ኢያሱም በሙሴ እግር ተተክቶ የቤተ እስራኤል መሪ ሆነ። ይሁንና በዘመነ አበው ፍጻሜና በዘመነ መሳፍንት መነሻ አካባቢ በነበረው የሽግግር መንግሥት አስተዳደር ወቅት ሙሴና ኢያሱ ቤተ እስራኤልን በመምራት ተመዝነው ክብደትንና ክብርን ያገኙበት ጊዜ ነበር።

ኢያሱ መስፍነ እስራኤል የሙሴ ተከታይ ወይንም ምትክ ሁኖ ከቤተ እስራኤል ጋር የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሮ በተስፋ የተሰጠውን ምድር ለመውረስ ሲገባ የጥምቀትን ምሳሌ እንደሠራ፣ ማለት ሕዝቡን እንደገዘረ፣ ባዲስ ዕዓልም የፋሲካን በዓል እንዳከበረ፣ መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አምስት ከቁጥር አንድ እስከ አሥራ ሦስት ያለው ይነግረናል።

እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት እንደ እግዚአብሔር ቸርነት በታቦተ ጽዮን ተአምራት ሠሪነት ዮርዳኖስን ተሻግርው ምድረ ርስት ገብተው የኢያሪኮን ግንብ አፍርሰው ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን እንደ ገና አድሰዋል። (ኢያሱ.፳፬፥፲፭–፲፱)።

ስለ ጥምቀተ ክርስቶስ በሕግና በነቢያት የተነገሩ ትንቢቶችና የተገለጡ ምሳሌዎች አሉ። ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ከሙሴ ቀጥሎ በተነሣው በቤተ እስራኤል መሪ በኢያሱ ዘመን ምስፍና ሕዝበ እስራኤል ምድረ ርስትን ለመውረስ በጉዞ ላይ ሳሉ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ገብተው በወንዙ ማዕከል ሲቆሙ ከዳር እስከ ዳር መልቶ የነበረው ውሀ ከመውረድ ተቋርጦ ጥርጊያ መንገድ ተከፈተላቸው። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስትን ወርሰዋል።

እንደዚሁም ንዕማን የተባለ የሶርያ መኮንን በዮርዳኖስ ውሀ ተጠምቆ ካደረበት የለምፅ በሽታ ሲነፃ፣ ጻድቁ ኢዮብም በዚህ ወንዝ ውሀ በመጠመቅ ከደዌ ሥጋ ፈውስን አግኝቷል። ነቢዩ ኤልያስም ይህኑ ወንዝ በሰበኑ መትቶ ከሁለት በመክፈል በደረቅ መሬት ከተሻገረ በኋላ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ አርጓል።

ትንቢትንም በተመለከተ:-
«ቃለ እግዚአብሔር ላዕለ ማያት፣
አምላክ ስብሐት እንጐድጐደ፣
እግዚአብሔር ላዕለ ማያት ብዙኅ»
«የእግዚአብሔር ቃል በውሀዎች ላይ ነው
የተመሰገነ አምላክ ድምፁን አሰማ፣



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በብዙ ውሆች ላይ ነው»
(መዝ.፳፰፥፫-፬)

«ርእዩከ ማያት እግዚኦ፤
ርእዩከ ማያት ወፈርሁ፤
ደንገፁ ቀላያተ ማያት ወደምፀ ማያቲሆሙ»
«አቤቱ ውሆች አዩህ፤
ውሆች አዩህና ፈሩህ
የውሆች ጥልቆች ደነገጡ
ማዕበላቸውም ተሰማ»
(መዝ.፸፯)

«በእንተዝ እዜከረከ እግዚኦ፤
በምድረ ዮርዳኖስ በአርሞንኤም በደብር ንዑስ፤
ቀላይ ለቀላይ ትጼውእ በቃለ አስራቢከ»
«አቤቱ ስለዚህ አስብሀለሁ፤
በዮርዳኖስ ምድር በአርሞንኤም በታናሹ ኮረፍታ፤
በሹዋ ሹዋቱ ድምፅ ቀላይ ቀላይን ትጠራለት»
(መዝ.፵፩)

«ባሕርኒ ርእየት ወጐየት
ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ
አድባር አንፈርዐፁ ከመ ሐራጊት»
«ምንተ ኮንኪ ባሕር ዘጐየይኪ
ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባእከ ድኅሬከ
አድባር ዘአንፈራዐፅክሙ ከመ ሐራጊት»
ባሕር አየች፤ ሸሸችም
ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ
ተራሮች እንደ ኮርማዎች ዘለሉ፤
አንቺ ባሕር የሸሸሽ፤

አንተም ዮርዳኖስ ወደኋላ የተመለስህ ምን ሆናችኋል እናንትም ተራሮች እንደኮርማዎች፤ ኮረብቶችስ እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ? ሲል ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ተናግሯል።

በካህናቱና በዲያቆናቱ በውሀው ዙሪያ ሲዘምሩ የሰማናቸው እነዚህኑ ትንቢቶች መሠረት በማድረግ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ከውሀው ሲወጣ:-

«ወናሁ ተርኅወ ሰማይ፤ ወርእየ መንፈሰ እግዚአብሔር እንዘ ይወርድ ከመርግብ ወነበረ ላዕሌሁ»

ሰማይ ተከፍቶ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት መጥምቁ ዮሐንስ አየ።

«ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱ ሠመርኩ:-» ለተዋሕዶ የመረጥሁት በእርሱ ሕልው ሁኜ ልመለከበት የወደድሁት ልጄ ይህ ነው የሚል ቃልም ከወደ ሰማይ ተሰማ።

መንጌላውያኑ በዚህ ቃል ምሥጢረ ሥላሴን በግልፅ አስተምረውናል። አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ከውሀው ሲወጣ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ሲያርፍ፤ የባሕርይ አባቱ አብም የወደድሁት ልጄ ይህ ነው በማለት በእርሱ ሕልው መሆኑን መስክሯል።

በዚህም የባሕርይ አምላክነቱን፤ የባህርይ ልጅነቱን ከአብ፤ ከመንፈስ ቅዱስ አስመስክሮበታል።

ምሥጢረ ሥጋዌ ከሦስቱ አካላት ሁለተኛው አካል ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ የመገለጡ አምላክ ሰው፤ ሰው አምላክ የመሆኑ ምሥጢር ነው፤ «ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» ይላል ሐዋርያው ዮሐንስ። (ዮሐ.፩፥፲፬) ስለዚህ በምሥጢረ ሥጋዌ የሚገለጠው ትምህርት ክርስቶስን ቃለ አብ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ድንግል ማርያምን በእማን ወላዲተ ቃል ብሎ ማመን ነው። (ቁርሉስ ሃይ.አ)

ከዚህ ታሪክ አንፃር ቀደም ሲል እንደ ተባለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በእደ ዮሐንስ መጠመቁን ለማዘከር ታቦተ ሕጉን ተሸክመን ወደ ወንዝ ዳር በመሔድ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት እግዚአብሔርን በማመስገን በዓሉን በታላቅ ሥነ ሥርዓት በማክበር ዕለቱን እናዘክራለን።

ስለዚህ ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት በየዓመቱ የምናዘክረው ስለ ጥምቀት በትንቢት የተነገረውን፤ በምሳሌ የተገለጸውን ከ[ግቢ]ን ጋር የአብ፤ የወልድ፤ የመንፈስ ቅዱስ አንድነትና ሦስትነት የታወቀበት ዕለት መሆኑንም በመገንዘብ እምነታችንን አጽንተን እንድንይዝ ያስተምረናል። የጥምቀተ ክርስቶስ በዓል አከባበር ዋናው ምሥጢርም ይህ ነውና።

በመጨረሻም ለማሳሰብ የምወደው ይህን በዓል በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን የምናከብርበት ዋናው ምክንያት ቀደም ሲል እንደ ተባለው:-

- በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም፤
- ውሀውን ለመቀደስ፤
- ለጥምቀት ኃይልን ለመስጠት፤
- ለእኛም አርአያና ምሳሌ ለመሆን፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በዮሐንስ እጅ በፈለገ ዮርዳኖስ የተጠመቀውን ጥምቀት በኅብረት በማክበርና በማዘከር በረከትን ለማግኘት እንጂ ሌላ ዘይቤ የለውም።

ሙሴ የመሰከረለት፤ ነቢያት የጮሁለት፤ ዮሐንስ መንገዱን የጠረገለት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ጥምቀት በየዓመቱ የምናከብርው ከዚህ አንፃር መሆኑን ሁሉም ማወቅና መረዳት ይኖርበታል።

## የፈለገ ጥበብ መጽሔት ደንበኛ ይሁኑ

### መልእክት ለአንባብያን

የፈለገ ጥበብ መጽሔት ቋሚ ደንበኛ ለመሆን ለምትፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚከተለውን የክፍያ መጠን በመፈጸም መጽሔቱን በየ3 ወሩ ማግኘት የምትችሉ መሆናችሁን እየገለጽን፤

ደንበኞች ክፍያውን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሂሳብ ቁጥር1955 ገቢ በማድረግ የከፈላችሁበት ደረሰኝና ሙሉ ስማችሁ ከነ አድራሻችሁ በፖስታ ሳጥን ቁጠር 81286 መላክ የምትችሉ መሆናችሁን የምናረጋግጠው በደስታ ነው።

| ቦታ | የሁለት እትም የግማሽ ዓመት | የአራት እትም የዓመት |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ በተራ መልእክት | 6.80 | 13.60 |
| ክፍለ ሀገርና አዲስ አበባ በአደራ መልእክት | 9.10 | 18.20 |
| ክፍለ ሀገር በተራ መልእክት | 7.00 | 14.00 |
| አፍሪካ በአደራ መልእክት | 4 ዶላር | 8 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ በአደራ መልእክት | 5 ዶላር | 10 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ በአደራ መልእክት | 6 ዶላር | 12 ዶላር |

በተጨማሪ በደርዘን ለመውሰድ የሚፈልጉ ደምበኞቻችን በቅናሽ ዋጋ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በሚገኘው የመጽሔት ማከፋፈያ ሱቃችን ብቅ ቢሉ የፈለጉትን ያገኛሉ።

በአዲስ አበባም ሆነው መመዝገብ የሚፈልጉም በአካል ቀርበው መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።



# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

## ክፍል ፩

### ትምህርተ ሕፃናት

### ከሥርዓተ–ቤተ–ክርስቲያን

እርሱም:-

፩. ስለ ቤተ–ክርስቲያን ማለት ስለ ቤተ–ጸሎት ምንነት
፪. ቤተ–ክርስቲያን ለመግባት ስላለው ዝግጅት
፫. ስለ ሥርዓተ–ዓቲብ
፬. ለቤተ ክርስቲያን የሚቀርብ እጅ መንሻ
፭. ስለ ሥርዓተ–ስግደት
፮. ለቅዱሳን የሚቀርብ እማኄና የሚቀርብበት ምክንያት
፯. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰሩት የማይገባ ስራና ሊናገሩት የማይገባ ነገር ነው።

### ትምህርቱ ሲሰጥ ፩. ስለ ቤተ–ክርስቲያን ምንነት ቤተ ክርስቲያን ምንድር ናት ቢባል

ሀ. ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት (ማር.፲፩፥፲፯። ግብ ሐዋ.፳፪፥፲፯)
ለ. ቤተ ክርስቲያን የስግደት ቤት ናት። ለእግዚአብሔር ይሰገድበታል (መዝ.፳፰፥፪። መዝ.፭፥፯)
ሐ. ቤተ ክርስቲያን ንስሐ መቅረቢያና የኃጢአት ይቅርታ መቀበያ ናት (ሉቃ.፲፰፥፲፱)
መ. ቤተ ክርስቲያን መሥዋዕት ያቀርቡበታል፤ የቍርባን ቤት ናት። ክርስቲያን ምእመናን መሥዋዕት ያቀርቡበታል፤ ቍርባን ይቆርቡበታል።
ሠ. ቤተ ክርስቲያን የንጽሕና እና የቅድስና ቤት ናት። ንጹህ እና ቅዱስ ሁነው ነው የሚገቡባት፤ (ዘጸ.፳፱፥፵፬፤ ዘጸ.፫፥፭፤ ኢያ.፭፥፲፭) ምእመናን የመንፈስ ንጽህና እና ቅድስና ያገኙበታል።
ረ. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት (መዝ.፲፪፥፩፤ መክ.፭፥፩ን ተመልከቱ) ስሙ ይጠራባታል፤ እግዚአብሔር ያድርባታል፤ ተአምራቱን ያሳይበታልና፤
ሰ. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መገናኛ ናት ክርስቲያን ምእመናን ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኙባታልና። (ዘጸ.፳፱፥፵፪–፵፫)
በ. ቤተ ክርስቲያን የበረከት ቤት ናት እግዚአብሔር ሕዝቡን ይባርክባታልና (ዘጸ.፳፥፳፬)
ተ. ቤተ ክርስቲያን በሰማይ ያለች የኢየሩሳሌም ምሳሌ ናት። (ራእ.፳፩፥፪ ቁ.፲–፳፯)

ከመጽሐፈ–ሰዓታት «ቤተ ክርስቲያን ትትሜሰል በጽርሐ አርያም ዘላዕሉ» ማለት «ቤተ ክርስቲያን ግን በላይኛው ጽርሐ አርያም ትመሰላለች» እንዲሉ፤

## ክፍል ፪

### ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የሚደረግ ዝግጅት

ልጆች ተማሪዎች ለጸሎት፤ ለስግደት፤ ለቅዳሴና ለቍርባን፤ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይኬዳል፤ እና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት በቅድሚያ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፤ ዝግጅቱም ምንድር ነው? ቢባል፤

ሀ. ቤተ ክርስቲያን መኼድ ያስቀየሙት ሰውካለ ይቅርታን ጠይቆ፤ የተቀየሙት ሰው ካለ ይቅርታን አውርዶ፤ ታርቆ፤ ነው። (ማቴ.፭፥፳፫–፳፬ ተመልከቱ) ቂምና ጥላቻን ይዞ ቤተ ክርስቲያን መኼድ ግን አይጠቅምም፤ ይጎዳል እንጂ።
ለ. ቤተ ክርስቲያን መኼድ በስርቆት፤ በቅሚያ፤ በማታለል፤ የወሰዱት የሰው ከብት (ገንዘብ) ቢኖር ለባለቤቱ መልሶ ነው፤
ሐ. ቤተ ክርስቲያን መሄድ ዋሽቶ መስከሮ እንደሆን ንስሐ ገብቶ ነው።
መ. ጥንቆላ እያስጠነቈሉ፤ ሟርት እያሟረቱ ቤተ ክርስቲያን መኼድ አይጠቅምም (ራእ.፳፪፥፲፭። ከዚህም ሌላ ቅዳሴ ዘአትናቴዎስ የመጀመሪያውን ክፍል ተመልከቱ)
ሠ. መጠጥ ጠጥቶ ሰክሮ ቤተ ክርስቲያን መግባት ክልክል ነው። (ዘሌ.፲፥፰–፲)
ረ. ቤተ ክርስቲያን በሚገቡበት ዕለት ባልና ሚስት (ወንድና ሴት) የመኝታ ግንኙነት አድርጎ ማደር ክልክል ነው (ዘጸ.፲፱፥፲፭)
ሰ. በቤተ ክርስቲያን የሚለበስ ልብስ መለየት ያስፈልጋል።
ቀ. ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ የሚለብሱት ልብስ የታጠበ ንጹህ ሊሆን ይገባል (ዘጸ.፲፱፥፲–፲፩)
በ. ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ሰውነትን መታጠብና መጸዳዳት ይገባል።
ተ. ሴቶች ደመ–ትክቶ (የወር አበባ) ሲመጣባቸው ቤተ ክርስቲያን መግባት አይገባቸውም፤ ሊያቋርጥላቸው ይገባሉ።
ቸ. የሚያኸር ቁስል፤ የሚያነፈርቅ ጉንፋን እና ሳል ይዞ ቤተ ክርስቲያን መግባት አይገባም።
ኀ. ጫማ አድርጎ (ጫማን እንደተጫሙ) ቤተ ክርስቲያን መግባት ክልክል ነው (ዘጸ.፫፥፭፤ ኢያ.፭፥፲፭)።
ነ. ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ አደግድጎ ማለትም ልብስን መስቀለኛ አድርጎ ተለብሶ ነው።
ኘ. ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ እያማተቡ ነው።

## ክፍል ፫

### ሥርዓተ ዓቲብ ማለት የማማተብ ሥርዓት

ማማተብ ማለት ፊትንና ግንባርን መባረክ፤ የመስቀል ገጽታ ማመልከት ማለት ነው።

ማማተብ ጣትን አመስቅሎ ነው (መስቀለኛ አድርጎ ማለት ነው)

አሠራሩ ከአውራ ጣት ቀጥሎ ያለውን ጣት ቀጥ አድርጎ ማቆም

መካከለኛውን ጣት እና ቀጥለው ያሉትን ጣቶች አጠፍ፤ አጠፍ፤ ተደርገው እንደ ቀኝና እንደ ግራ የመስቀል ክንፍ ይሆኑና ቀጥ ብሎ ከቆመው ጣት ጋር በመጋጠም የመስቀልን ገጽታ ያሳዩአል።

ሲያማትቡ

እንዲህ ጣትን መስቀለኛ አድርጎ «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ» ብሎ ስመ ሥላሴን በመጥራት አዓትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል» እያሉ ከራስ ግንባር እስከ ደረት (እስከ ልብ አፍ)

ሀ. ከላይ ወደ ታች፤
ለ. ከቀኝ ወደ ግራ ጎን፤
ሐ. ከግራ ወደ ቀኝ ጎን፤ ገጽንና ሁለንተናን ያማትቧል (ይባርኳል)

የማማተብ ሥርዓተ ወይም አሠራሩ እንዲህ ነው ማለትም አሁን እንደ ተመለከተው ነው።

ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ፤ የትም ቦታ ሆኖ ጸሎት ሲጀምሩ እንዲህ አማትቦ ነው።

ምሥጢሩ:- ጣትን አመስቅሎ ገጽን ማማተብ ለምንድር ነው? ቢባል፤

ክፉ ሐሊናን ከልብ ለማራቅ ነው፤ ወይም የሰይጣንን መንፈስ ለማራቅ ነው፤ (ለማባረር ነው) ሰይጣናት በእግዚአብሔር ጣት ይባረራሉና (ሉቃ.፲፩፥ ቁ.፳ን ተመልከቱ)





www.ethiopianorthodox.org



## ክፍል ፩

### ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ እማኄ

ቤተ–ክርስቲያን ሲገቡ እመጀመሪያው ደጅ አፍ (እቅኑ መዓልቱ መግቢያ) ቆም ብሎ «ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ–ክርስቲያን ማኅደረ –መለኮት፡ ምስአል፡ ወምስጋድ፡ ወምስት ስራየ–ኃጢአት» በማለት ወይም «ሰላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት፡ አምሳለ– ኢየሩሳሌም ሰማያዊት» በማለት ለቤተ ክርስ ቲያን እማኄ ይሰጣል። ወይም ይሰግዷል።

ምሳሌ:- ቀድሞ እነ አብርሃም፡ የእግዚአ ብሔር ቤተ መቅደስ ለሚሠራባትና አምልኮቱ ለሚፈጸምባት ለተስፋ አገራቸው ለምድረ ከነዓን ሰላምታ (እማኄ) እንደሰጡ ነው፤ (ዕብ.፲፩፡፲፫)

ቅዱስ ያሬድም በሀበልዋ ተሳለምዋ... ለቤተ ክርስቲያን ሲል አስተምሯል። (መጽ ሐፈ መዝሙር ወይም ድጓ)

ዋና ምክንያቱ ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ እግዚአብሔር ስለሆነች ነው።

## ክፍል ፫

### ሥርዓተ– ስግደት ባማርኛ የስግደት ሥርዓት

ት ም ህ ር ቱ መቸም ስግደት የሚስ ገድ ለእግዚአብሔር ነው። ማቴ.፬ ቁ.፲ን፤ ራእ.፲፱ ቁ.፲ን፡ ራእ. ፳፪ ቁ.፱ን፡ ኢሳ.፶፫ ቁ.፳፫ን፡ መዝ.፺ ቁ.፱ን እንብቡና ተረዱ።

ስግደት የሚሰገድ ለምንድር ነው? ቢባል:- ስግደት የአምልኮ፡ የተገ ዥነት፡ መግለጫ ነው፤ ማረኝታም ነው።

ሥርዓቱ ቤተ ክር ስቲያን ሲገቡ በቅ ድሚያ የሚደረስ (የሚሰገድ) የተወሰነ ስግደት አለ፤ ይኸ ውም እንዲህ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ እመጀመሪያው በር (መግቢያ) ለቤተ ክርስ ቲያን እማኄ አቅርበ ያልፏል። (የእማኄ ውን አቀራረብ ባለ ፈው ክፍል አይተ ናል፡ ወይም አሳይተናል።

ቀጥሎ ሀ. ቅኔ መዓልቱን አልፎ እኹ ለተኛው ክፍል (እቅ ድስቱ) መግቢያ ላይ ቆም ብሎ ያማትቡና «እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ብሎ አንድ ጊዜ ይሰግሳል።

ለ. ቅድስቱን ክፍል (ኹለተኛውን ክፍል) አልፎ እመቅደሱ በር ዓላሙ ላይ (ድርገት መውረጃው) ቆም ብሎ በማማተብ «እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያሉ ኹለት ጊዜ ይሰግዷል።

እዚህ ላይ ስግደት ሦስት ይኾናል። ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጸሎት ከመጀመሩ በፊት ለእ ግዚአብሔር የሚቀርብ የስግደት ውሳኔ ይህ ነው።

ምሥጢሩ ባንድ ጊዜ ሦስት ስግደት መስ ገድ (ማቅረብ) ለምንድር ነው ቢሉ እግዚአ ብሔር ሀ. በነፍስ ለ. በሥጋ፡ ሐ. በመንፈስ፡ ማምለካችንን እና ለእግዚአብሔር፡ በነፍስ፡ በሥጋ፡ በመንፈስ፡ መገዛታችንን ለመግለጽ ነው፤

እነዚሆንም ሦስቱ ሕዋሳት፡ ወይም እነ ዚህን ረቂቅና ግዙፍ ሕዋሳት፡ ጳውሎስ ሐዋርያ በትምህርት ጠቅሷቸዋል (ጠቁሟ ቸዋል)። ፩ተሰ. ም.፭ ቁ.፳፫ን እንብቡ።

እግዚአብሔርም በመንፈስ እንድን ሰግድለት ይሻል (ዮሐ.፬፡፳፫–፳፬) ሕዋሳትን ሁሉ የሚያዝዝ መንፈስ ነውና።

ማሳሰቢያ:- እላይ በተጠቀሱት ሁለት ክፍሎች ሆኖ መስገድ ባያመች፡ ወይም ሁለት ክፍል (ቅኔ መዓልትና ቅድስት) በሌለበት ቤተ ክርስቲያን ግን ሦስቱን ስግደት ባንድ ሥፍራ ባንድ ክፍል ሆኖ ይሰግዷል።

ይህም ሦስት ስግደት በእሑድ በቅዳሜ በዓልና በሌሎች ዓበይት በዓላት የማይከለከል የየእለትና የየሰዓቱ አምልኮተ እግዚአብሔር መግለጫ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቀዳሚውን ስግ ደት እንዲህ ካደረሱ (ካቀረቡ) በኋላ ተገቢውን ቦታ ይዞ ቆሞ የዘወትሩንና የዕለቱን ጸሎት መጸለይ ነው።

የግል ከኾነ ጸሎት በግል መጸለይ፡ የማኅ በር ከኾነ ከማኅበር ጋር ጸሎቱን ማድረስ ነው።

በጸሎቱ ውስጥ ሰጊድ በሚወሳበት ቃል ጸሎቱን እየተናገሩ ይሰግዷል።

ለምሳሌ:- ነአኵተከ እግዚእ...በሚለው ጸሎት ውስጥ «ንሰግድ ለከ እ ዘለከ ይሰግድ፡ ኵሉ ብርክ» ሲባል፤

«ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡» በሚለው ውስጥ «ንሰግድ ለከ ክርስቶስ፡ ምስለ–አቡ ከኄር ሰማያዊ ወመንፈስከ ቅዱስ ማኅየዊ» ሲባልና «ንሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐተ ስግደተ» ሲባል እየሰገዱ ይነበባል ጸሎቱ።

ጸሎቱን ጸልየው አብቅተው ወደ ቤት በሚመለሱበት ጊዜ አንድ ጊዜ ሰግዶ ይመለ ሳል፤ ይኸም አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብለን ማምለካችንን ማሳየት ነው።

እንደ መጀመሪያው ሦስት ጊዜም ሰግዶ ቢመለሱ ይኾናል።

የክፍሉ ትምህርት መደምደሚያ:- ለፈጣሪ ለእግዚአብሔር የአምልኮን ስግደት ካቀረቡ በኋላ፡ በቤተ – ክርስቲያናችን ሥርዓት

### ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም፤

ለመስቀለ–ክርስቶስ፡ ለእግዚአብሔር መላእክት፡ ለታቦተ –ምሰዋእ፡ ለቅዱሳን ሰዎች፡ ለጻድቃን፡ ሰማዕታት እማኄ ማቅረብ፡ ወይም የአክብሮት ስግደት ማቅረብ አለ።

## ክፍል ፬

### ለቅዱሳን የሚቀርብ እማኄ ወይም ስግደትና የሚቀርብበት ምክንያት

መግለጫ – ቅዱሳን የተባሉት ከዚህ ርእስ በላይ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ጀምሮ በእየስማቸው የተጠቀሱት ናቸው።

ቅድስናቸው የእግዚአብሔር መላእክት ንጽሐ–ጠባይዕ (የባሕርይ ንጽህና) ያላደፈ ባቸው ቅዱሳን ናቸው፤ (ሉቃ.፲፭፡፺ን አጥኑ)

ከሰው ዘር ድንግል ማርያም ንጽሀ– ጠባይዕ ያላደፈባት ቅድስት ናት (ሉቃ. ፩፡፳፰ን እና ፵፪ን እንብቡና ልብ አድርጉት)

ቅዱሳን ሰዎችም በተጋድሎና በትዕግ ሥት፡ ፍጹማን ጻድቃን ናቸው።

እነዚህ ሁሉም ቅዱሳን ስለ ኾኑ በእግዚ አብሔር ፊት ሞገስና ክብር አላቸው፡ ጸሎ ታቸውና ልመናቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ቅቡል ነው፡ (ተቀባይነት ያለው ነው) ለተማ ጸነባቸው ልመናቸው ይረዳል፡ (ያዕ.፭፡፲፯)

ለምሳሌ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም እማኄ እንዴ ቀረበ እናገኛለን።

ጥቅስ:- «ሰላም ለኪ እ ማርያም ድንግል እንተ–ወለድኪ እንዘ ኢይትነሰት መሠረ ተ–ማህጸንኪ። ሰላም ለኪ እ ማርያም ድንግል እንተ–ወለድኪ እንዘ–ኢይትርኃው ወእንዘ– ኢይትቄለጥ ማኅተመ–ድንግልናኪ፤ ወተሰ መይኪ እመ ወእመተ በልደተ– መድኃኒነ ቅዱስ። ሰላም ለኪ እ ማርያም ድንግል እንተ–ረከብኪ ሞገሰ እግዚአብሔር ምስሌኪ» ብሏል። (ሃይ.አበ.የዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን ክፍል ፳፭)።

ከዚህም ሌላ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ– ክርስቲያናችን ለቅዱሳን እማኄ ለማቅረቧና በጸሎታቸው ለመማጸኗ ከልዩ ልዩ የጸሎት ክፍሎች ጠቅሰን ማስረጃ እናቀርባለን።

ሀ. ከቅዱስ፡ ቅዱስ...ንሰግድ ለእግዝ እትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ፤ ንሰግድ ለመስቀለ–እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ...

ለ. ካጼ ናእድ ተማኅጸኖ ሰላም ለኪ እንዘ – ንሰግድ ንብለኪ፡ ማርያም እመነ ናስተበቍዐኪ...

ሐ. ከማኅሌት ንግሥት – «ሰላም ለከመ ማኅበረ – መላእክት ትጉኃን፤ ሰላም ለከመ ማኅበረ – ነቢያት ቅዱሳን፤ ሰላም ለከመ ማኅበረ – ሰማዕት ወጻድቃን፤ ሰላም ለከመ ማኅበረ – ሥላሴ ጉቡእን፤ ሰላም ለከመ ማኅበረ – ሐዋርያት ፍንዋን፤ ወሰላም ለማር ያም ዘእሳት ክዳን» እያለች ቤተ ክርስ ቲያናችን ለቅዱሳን የአክብሮት እማኄ ታቀርባለች።

ማስገንዘቢያ ለቅዱሳን የምናቀርበው ስግ ደት፡ የአፍቅሮት፡ የአክብሮት፡ መግለጫ፡ ነው።

ለመስቀል፡ እና ለታቦትም ስግደት የምና ቀርብ፡ የእግዚአብሔር ኃይል ስለሚገለጽ ባቸው ነው (እግዚአብሔር ኃይሉን ስለሚገል ጽባቸው ነው)።

### ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን የነበረው ጽላተ –ሕግ

ሀ. እግዚአብሔር ቃሉን ያሰማበት ነበር (ዘጸ.፳፭፡፳፩–፳፪)

ለ. በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ፤

ሐ. በኢያሪኮ ግንብ ላይ፤

መ. የፍልስጥኤማውያን አምላክ በነበረው በዳጎን ላይ፤ የእግዚአብሔር ኃይል ተገልጾበታል።

በለ የተጠቀሰው (ኢያ.፫፡፲፬–፲፯)

በሐ የተጠቀሰው (ኢያ.፮፡፩–፳)

በመ. የተጠቀሰው (፩ሳሙ.፭፡፩–፬) ይገኛል እንብቡ።

ዛሬም በአብያተ ክርስቲያናችን የሚገ ኘው ታቦተ መሥዋዕ ታቦተ–እግዚ አብሔር፤ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል (ይገኝበታል)

ለቁርባን የምናቀርበው ኅብስትና ወይን የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ሆኖ ይከብርበታል፤

እንደ ጌታ እንደኢየሱስ ክርስቶስ አካልም አድርገን እናስበዋለን ታቦተ መሥዋዕን።

እንዲህም በመኾኑ፡ ታቦተ–መሥዋዕ ሰምህላ፡ ለዑደት ወደውጪ ወጥቶ በቤተ–መቅደስ ዙሪያ በሚታወድበት ጊዜ

በአካባቢውና በአንጻሩ (በትይዩ) የሚገኝ ቦታ ባራት መአዝን ይባረካል

ደዌያት ይጠፋሉ (ይበርዳሉ)

አጋንንት ይሸሻሉ።

ማስረጃ በግእዝ

«ወአንቲኒ ታቦት እምኅበኒ መጻእኪ ወኅበኒ ተሐውረ መድኃኒተ ኮኒ፡» ባማርኛ አንቺም ታቦት ከመጣሽበትም ቦታ፡ ከምትኼ ድበትም ቦታ መድኀኒት ኾኚ» መጽሐፈ መዝ ሙር ዘያሬድ (ድጓ)

ይህ እንደሚደረግ እናምናለንና በአክ ብሮት እንሰግድበታለን ስግደቱ የሚቀበለን ራሱ እግዚአብሔር ነው።

## ክፍል ፭

### በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሠሩት የማይ ገባ ተግባርና ሊናገሩት የማይገባ ነገር

፩. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አጸያፊ ነገር መናገር፡ ዓለማዊ ጨዋታ መጫወት፡ ተረት መተረት፡ ቀልድ መቀለድ፡ ሳቅ መሳሳቅ፡ ክልክል ነው። ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት እንጂ የዓለም ነገር መነጋገሪያ አይደ ለችምና።

፪. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙግት፡ ጭቅጭቅ፡ ንትርክ፡ አይገባም፡

፫. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብር ይዞ፡ እቃ ይዞ፡ ገብቶ መሻሻጥ (ገበያ መገብየት) አይገባም፡ (ማር.፲፩፡፲፭–፲፯)

፬. ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲገቡ፡ ገብቶም ከቦታ ወደ ቦታ ሲንቀሳቀሱ፡ እየሮጡ እንድቅ፡ እንድቅ፡ እያሉ መኼድ አይገባም።

፭. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደርሰው ጸሎት ፈውስ ለማግኘት፡ ቍርባን ለመ ቀበል ታዝሎ የመጣ ሕመምተኛ ካል ኾነ በቀር ተጋድሞ መተኛት ክልክል ነው። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት



እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አገላለጽ የማይለያዩ ሁለት ነገሮች የተባሉት እምነትና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ናቸው።

## ሀ. እምነት ወይም ሃይማኖት

እምነት ማለት በፍጹም ልባችን እግዚአብሔርን ዓለም ሳይፍጠር የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ዓለሙንም አሳልፎ የሚኖር፣ የሚታየውንና የማይታየውንም የፈጠረ ወይም ያስገኘ መሆኑን ማመን ነው።

ሁሉን ቻይነቱን፣ በዓለም ሙሉነቱን፣ ዘለዓለማዊነቱን፣ ኃያልነቱን፣ ሁሉን አዋቂነቱን፣ ቅዱስነቱን እና የመሳሰለውን ሁሉ ማመን እምነት ወይም ሃይማኖት ይባላል።

ከዚህም ጋር የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ያለእናት ከአብ፣ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ መወለዱን ማመን ሃይማኖት ወይም እምነት ይባላል።

የሰውን ልጅ ከጠፋበት ለመፈለግ፣ ከኃጢአት ቍራኝነት፣ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በመስቀል ተሰቅሎ፣ ሥጋውን ቆርሶ፣ ደሙን አፍሶ፣ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከሙታን ተለይቶ መነሳቱን ማመን ሃይማኖት ይባላል።

«እምነት ማለት በተስፋ የምንጠባበቃቸውን ነገሮች እንደምናገኝ የሚያረጋግጥ፣ የማናያቸው ነገሮች መኖራቸውንም የሚያስረዳ ነው። የቀድሞ ሰዎች የተመሰገኑት በእምነት ምክንያት ነው። ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም» (ዕብ. ፲፩፥፩–፫፥፮)

በጠቅላላው ከአባቶቻችን የተቀበልነውን፣ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የተማርነውን እና የተቀበልነውን እምነት እስከ መጨረሻው ጠብቆ ማቈየት ሃይማኖት ይባላል።

ሁላችንም እንደምናውቀው ገበሬ በእምነት ይዘራል፤ እንደ እምነቱም ወቅቱን ጠብቆ ሰብሉን ይሰበስባል። አማኝም እንደ እምነቱና እንደ ሥራው ዘለዓለማዊ ዋጋ ማግኘቱ አያጠራጥርም። «እስመ ሀለዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው ይምጻእ በስብሐተ አቡሁ ምስለ መላእክቲሁ፤ ወአሜሃ የዐስዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ» የሰው ልጅ በመላእክት ታጅቦ በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ዋጋውን ይሰጠዋል ተብሏልና ነው። (ማቴ.፲፮፥፳፯)

## የማይለያዩ ሁለት ነገሮች

## ለ. የእምነት ኃይል

የፀና እምነት ካለን ታላላቅ ግዳጆችን እንፈጽማለን። እንደ ተራራ ያበጡ ችግሮችን እናስወግዳለን፤ በእምነት ብንጸልይ ጸሎታችን ይሰማል፤ ግዳጅም ይፈጽማል። ጌታ በወንጌል «በእውነት እላችኋለሁ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወዲያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁ ነገር አይኖርም» (ማቴ.፲፯፥፳) በማለት ያስተማረውን ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህም ጋር «ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤ የሚፈልግ ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል» ተብሏልና (ማቴ.፯፥፯–፰)።

ማንኛውም ሰው እምነቱን ማሳረፍ የሚገባው ሁሉን ማድረግ በሚችለው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው እንጂ እንደ እርሱ ፍጡራን በሆኑት ላይ እምነቱን ጥሎ ማሟረት ከእግዚአብሔር የሚያርቅና የእግዚአብሔር ልጅነትንም የሚያሳጣ ነው።

ሰው ከሃይማኖትና ከምግባር ውጪ ሆኖ እንደ ፈቀደው ይኖር ዘንድ ከእግዚአብሔር ነፃነት አልተሰጠውም።

ሃይማኖት ወጪ የሌለው፣ ኪሳራም የማያስከትል ዘለዓለማዊ ትርፍ ነው። ከሃይማኖት እወጣለሁ ብሎ የሚጓዘውን የሚያጋጥመው ነገር ቢኖር የጨለማ ገደል ነው።

በዚህ መሠረት ሃይማኖትን አክብሮ እና ጠብቆ መያዝ የምግባር ተቀዳሚ ተግባር ስለ ሆነ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ ማመንና በጎ ምግባርን መያዝ ለሰው ልጅ ክብር የሕይወት መሠረት ነው። ሃይማኖትንና መልካም ሥነ ምግባርን ካልተመረኮዘ ወይም ካልተደገፉ የሚሄዱበት መንገድ ሁሉ አይቀናም። ሚዳው ገደል፤ ቀኑ ጨለማ ይሆናል። ማንኛውም ሰው እምነቱን የማያከብር፣ ሥነ ምግባሩን የማያሳምር ከሆነ ራሱን የሚያምነው፣ የሚያከብረው አይኖርም።

አበው፡- «መኖር ዋዛ አይደለም» እንደሚሉት በዚህ ዓለም ሲኖር እንደ ዓሣ ምግብ በብልሃት እና በእምነት መኖር ይገባል።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በሰው ገጸ–ምግባር ላይ ያለውን ጉድፍ (መስታወት) አድርጎ ማሳየትና ለዚህ የሚሆነውን ጥንቃቄ ገልጾ ማሳየት ነው።

አረም የበቀለበት አዝመራ ከነአረሙ ቢተውት ፍሬ ቢስ ሆኖ መቅረቱ የታወቀ ነው። ክፉ አመል ያለበትም ፍጥረት ያንኑ ክፉ አመሉን በቃለ እግዚአብሔር፣ ካላረሙለት ከታላቅ ጉዳት ላይ መድረሱ አይቀሬ ነው።

ክፉ አመልንም ማረም ልብን ጠልቆ በሚሰማ በእግዚአብሔር ቃል እንጂ ቢተው ይተው፣ ባይተው ግን ለራሱ ይባሰው በማለት በግብር ይውጣ መሆን የሌለበት ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው።

«ሰዎች ተመከሩ ከሕግ አትለፉ፣
ከሕግ አልፎ መሄድ መዋረድ ነው ትርፉ፣
ሕግን ካፈረሱ ከሕግ ከወጡ፣
እነማን አያችሁ ከውርደት ሲያመልጡ፣
አብሮ ያድጋልና አመልና ልማድ
ጠባዩን ያሳምር ያዲስ ዘመን ትውልድ።

ተብሎ የተገጠመውን ከዚህ ላይ መጥቀስ እንወዳለን።

## ሐ. የእምነት መሠረትነት

እምነት (ሃይማኖት) መሠረት ናት። ምግባር ግን ግድግዳና ጣራ፣ ማገርና ወጋግራ ነው። ምግባር ያለሃይማኖት መሠረትነት በምንም ላይ ጸንቶ ሊኖር አይችልም።

ለቤት ድጋፍና ጽናት ከመሠረት እስከ ጉልላት ያሉ ነገሮች እንደሚያስፈልጉት ለሰውም ሕይወት ከሃይማኖት እስከ ምግባር ያሉት፣ ከደግ ምግባር የሚገኙ ጠባዓት ያስፈልጉታል። እምነትን የሚከተለው ምግባር ስለ ሆነ ምግባርን ከእምነት እምነትን ከምግባር ለያይቶ ማስቀረት ሃይማኖታዊ ሥርዓት አይደለም።

እያንዳንዱ አማኝ (ሰው) ነፋስ እንደሚወዘውዘው ዛፍ በእምነቱ ወዲያና ወዲህ የሚዋልል ሳይሆን ፀጥ ያለ፣ ቀጥ ያለም አቋም ሊኖረው ይገባል። በሰላም ወቅት አምኖበት በቆየው እምነቱ ችግርና መከራ በደረሰበት ጊዜ በዚያው ምጽናት እንጂ መናወጽ አይገባውም።

ያልተገበረበት ርስት እንደማይጸና እያንዳንዱ ሰው የእምነትና የምግባር ግብር ለእግዚአብሔር የመክፈል ግዴታ አለበት። እምነትና ምግባር የእግዚአብሔር የወግ ዕቃዎች ናቸው። ምእመናንም የእግዚአብሔር የወግ ዕቃ ቤቶች መሆናቸው የታወቀ ነው። ከእነዚህ ከሁለቱ ዕቃዎች ከምግባርና ከሃይማኖት አንድ እንኳ ቢጠፉ ሰዎች በኃላፊነት መጠየቃቸው አይቀርም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከዝሙት ራቁ፤ ሰው የሚያደርገው ሌላው ኃጢአት ሁሉ ከሰውነቱ ውጪ የሚደረግ ነው፤ ዝሙትን የሚፈጽም ሰው ግን በገዛ ሰውነቱ ላይ ኃጢአትን ያደርጋል፤ ሰውነታችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በውስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን? እንግዲህ እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም እንግዲህ ሰው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔርም እርሱን ያፈርሰዋል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነው፤ ይህም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ።» በማለት ያስተምራል። (፩ኛ.ቆሮንቶስ ፫፥፲፮–፲፯፤ ፮፥፲፰–፲፱)።

ከእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዲት እንኳ ብትሆን እንዳትፈርስና እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር ቤትነት የፈረሰ እንዳይሆን መጠንቀቅ ግዴታ ነው። እያንዳንዱ ሰው ጠዋት ከመኝታው ተነስቶ ለቁርስ፤ ቀን ከዋለበት ውሎ ለምሳ፤ ማታ ከአመሸበት አምሽቶ ለራት የሚያስበውን ያህል ለበጎ ምግባርና ከአበው ለተቀበለው እምነት ማሰብና መጠንቀቅ አለበት። ጌታ በወንጌል «የበግ ልብስ ለብሰው ወደ እናንተ ከሚመጡ ከሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ፤ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ናቸው» ብሎ የተናገረው ስለዚህ ነው።

እያንዳንዱ በግ እርቢ ከበጎቹ አንዲት ስትጠፋ እንደሚያዝን ከእያንዳንዱ አማኝም ሃይማኖትና ምግባር ሲታጣ እግዚአብሔር ያዝናል። ፍጡር ሁሉ የእግዚአብሔር ገንዘብ ስለሆነ በገንዘብነቱ የሚያዝበት ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። (ሉቃ.፲፭፥፩፤ ማቴ. ፲፰፥፲፩–፲፬፤ ሕዝ.፴፬፥፩–፴፩፤ ፴፫–፲፩)።

ስለሆነም እምነት በሥራ መገለጽ አለበት፤ እምነት ያለ ሥራ ጥቅም አያስገኝም። በሃይማኖታዊ መንፈስ፣ በሰብአዊ አመለካከት ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የሚደረገው የተቀደሰ ሥራ እምነትን ከፍ ሊያደርገው እና መሠረቱንም ሊያፀናው ይችላል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ከእምነት ጋር ሥራ አስፈላጊ መሆኑን ሲያረጋግጥ «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ከሥራ የተለየ እምነትም የሞተ ነው» ይላል። (ያዕ.፪፥፳፮)።

እምነትን ለማጽናት፣ ምግባርን ለማቅናት የደጋግ ሰዎችን ታሪክ ማንበብ ይጠቅማል። በአንጻሩም የክፉዎችን ምግባር መያዝ በረከትን ያሳጣል።

ማንኛውም ሰው በዚህ ዓለም የሚኖረው በሚቀጥለው (በወዲያኛው) ዓለም የሚኖርበትን ቤት ሲሠራ ነው አኗኗሩም በሁለት ዋና ዋና ግዴታዎች የተያዘ ስለ ሆነ ሁለቱም እንዳይታጡ አስተካክሎ መያዝ ግዴታው ነው።

ከሁለቱም ግዴታዎች አንዱ ሃይማኖት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መልካም ሥነ ምግባር ስለሆነ በእነዚህ በሁለቱ ዐበይት ነገሮች ሙሉ ሆኖ መገኘት አለበት። ከሁለቱ አንዱ ከጎደለ የጎደለው ክፍል ምውት መሆኑን ሐዋርያው ያዕቆብ በግልጽ አስቀምጦታል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው በተፈጥሮው የተሰጡት ሃይማኖትና ምግባር ቀንበር የሌለው ሞፈር፣ ወይም ሞፈር የሌለው ቀንበር ሊሆኑ አይገባም። የአንዳንዱ ጠባይ ሰባራ ሰንጣራ፣ እራራ መራራ እየሆነ ሁለቱንም እጁን ባዶ አድርጎት ይቀራል። ሁለት እጅ የተባሉትም ሃይማኖትና ምግባር ናቸው።

ሰው አንድ እግሩ ቢቈረጥ በምርኩዝ እየታገዘ በሁለተኛው እግሩ ያነክሳል፤ አንድ ዓይኑ ቢፈርጥ በሌላይቱ ዓይኑ ያጮልቃል፤ አንድ ጆሮው ቢደነቁር በሁለተኛው ለማዳመጥ ይሞክራል። ስለሆነም ምግባርና ሃይማኖት ግን እንደዚህ አይደሉም። በማንኛውም ትክክለኛ አእምሮ ባለው ሰው ዘንድ ሁለቱም ባለመለያየት፣ ባለመከፋፈል መገኘት ይኖርባቸዋል።

እየዋሹና እየቀጠፉ እግዚአብሔርን ቢያምኑ ከማመን አይቈጠርም። እየሰረቁ ቢመጸውቱ ደግ ሥራ ተሠራ ለማለት አይቻልም የሃይማኖትና የምግባርም ምሳሌያቸው ሥጋና ነፍስ ናቸው። ሥጋ ያለነፍስ ሕይወት የለውም፤ ነፍስም ያለ ሥጋ ሕይወት ሊኖራት አይችልም። ጽድቅም ሆነ ኵነኔ የሚመጣው እነሱን ተከትሎ ነው።

ለማንኛውም ሰው ምግባሩ አበባ ሲሆን ሃይማኖቱ ደግሞ ፍሬ ነው። አበባው ያልተጨናገለበት ተክል ፍሬውን ለማሳመር የሚችለውን ያህል ምግባሩ ያማረለት ሰውም ሃይማኖቱ የተቃና ሆኗል። እንጀራ ያለወጥ ብቻውን ሙሉ ምግብ አይሆንም፤ ሥጋዊ እውቀትም መንፈሳዊ እውቀት ካልታከለበት ብቻውን ጥቅም አይኖረውም።

«ራስን በሥጋዊ ነገር ማለማመድ ጥቅሙ ጥቂት ነው፤ ራስን በመንፈሳዊ ነገር ማለማመድ ግን ለአሁንና ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለሁሉ ነገር ይጠቅማል» በማለት ሐዋርያው ያስተምራል። (፩ኛጢ.ሞ.፬፥፰)።

ከላይ በዝርዝር ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድ ዓይና ከመሆን ሁለት ዓይን፣ አንድ እጅ ከመሆን ሁለት እጅ፣ አንድ እግር ከመሆን ሁለት እግር ያለው መሆን በጣም የተሻለ መሆኑን ፍጡር አይዘነጋውም።

ስለዚህ በአንድ ትክክለኛ አማኝ ሕይወት ውስጥም ሥጋዊነትና መንፈሳዊነት ሚዛናቸውን ጠብቀው መገኘት ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው ማለት ነው።

## መ. ወጣቶችና ሥነ ምግባራቸው

ሰው በሕፃንነቱ ተክል ነው። ተክል የሚሆነውን ሁሉ ሊሆን ይችላል። ይለመልምና በልምላሜው ደስ ይሰኛል። ያብብና በአበባው የዓይን ደስታ ይሆናል። ያፈራና በፍሬው የልብ ደስታ ይሰጣል። ከላይ እንደ ተጠቀሱት ምሳሌዎች ለመሆን የሚችል ወጣት ሰውነቱን በተጎሳቈለ ምግባር ያጎሳቈለው እንደ ሆነ ተስፋ ያስቈርጣል። በተስፋ የሚጠበቀው ሰብአዊ እድሉም በመጥፎ ግብሩ ይቀጭጫል።

በአበባ ውስጥ የፍሬ እንቡጥ ለመያዝ መጀመሪያ የአትክልቱ አያያዝ ደንበኛ ሆኖ ሲገኝ ለመልካም ፍሬ ያበቃል በአንጻሩም አንድ ወጣት ከፍሬ ለመድረስ የሚችለው በወጣትነቱ በሰራው ወይም በሚሠራው መልካም ሥነ ምግባር መሆኑ ነው።

ለዚህም ጠቢቡ «ወጣት ሆይ! ወጣትነት እጅግ ግሩም ስለሆነ በወጣትነትህ ዘመን ደስ ይበልህ፤ በልብህም ሐሤት አድርግ፤ ዓይንህ የሚያየውንና ልብህ የሚመኘውን መልካም ሥራ ሁሉ ፈጽም፤ ሆኖም ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንደሚያመጣህ ዕወቅ የወጣትነትና የብርቱ ጎልማሳነት ጊዜ ቶሎ ስለሚያልፍ ኃዘንን ከልብህ ጭንቀትህንም ከአእምሮህ አስወግድ» በማለት ለወጣቱ ምክርን ይለግሳል። (መጽ.መክብብ ፲፩፥፱–፲)።

መንፈስ ጥበብን የተመላው፣ የልዑል እግዚአብሔር ምርጥ መሣሪያ የተሰኘው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ምንት ብከ ዘኢነሣዕከ እምካልዕከ» ከሌላው ያላገኘኸው ምን ነገር አለ? እንዳለው ልጆች ከአባቶች የሚያገኙት ከወላጆቻቸውስ የማይወርሱት ምን ነገር አለ? አባቶች ለልጆች የሚያወርሱት ልጆችም ከወላጆቻቸው የሚወርሱት ቢኖር ማጀት በጎረስ ደጃፍ በመለሰ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብታቸውንና ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን ከቀደሙት አባቶች





www.ethiopianorthodox.org

የተወረሰውን፣ ፍጹም የሆነ እምነታቸውን፣ ከብረት የጠነከረ ሥነ ምግባራቸውን፣ ቁራጥነት የተሞላበት ጀግንነታቸውን፣ ብሔራዊ ስሜታቸውን ትክክለኛ አስተሳሰባቸውንና አፈጻጸማቸውን ጭምር ሁሉ መሆን አለበት።

የአእምሮና የሥነ ምግባር ሕጸጽ የእምነት ጳህጽ ያለበት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ወላጅ ልጆቹ የተሟላና የተደላደለ አእምሮ አግኝተው አርቆ አስተዋይነት እንዲኖራቸው የማይጥርና የማይመኝ አይኖርም። ይህንንም ጌታ በወንጌል «ከእናንተ ልጁ እንጀራ ቢለምነው ድንጋይ፣ ዓሣ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን?» በማለት እያንዳንዱ ወላጅ ለልጆቹ ደህንነት የማያስብ፣ መልካም ነገርን የማይመኝ አለመኖሩን አስተምሯል። (ማቴ.፯፥፱–፲)።

ስለዚህ የሰውን ልጅ በሕፃንነቱ ወላጆቹ ተቈጣጥረው ደጉንና ክፉውን ለይተው የሚበጀውንና የሚጠቅመውን እንዲይዝ መርሐ ግብር ይሰጡታል። ዕድሜው እየገፋ፣ በዕውቀቱም እየዳበረ ሲሄድ ግን አካባቢው የሚወደውን ወዶ፣ አካባቢው የሚጠላውን ጠልቶ እንዲኖር ግድ ይሆንበታል። ምክንያቱም የሥነ–አእምሮ ሊቃውንት እንደሚያምኑት የቁመት መርዘምና ማጠር፣ የአጥንት ስፋትና ጥበት የሥነ ላሕይ ውበት ከእናት አባት በዘር የሚገኝ ሲሆን ጠባይ ግን ከአካባቢው የሚወረስ ስለሆነ ነው። ኢትዮጵያውያን አባቶች ስለዚህ ሁኔታ ስለ ግብረ ጥፉ ልጅ ሲገልጹ «መልኩ የኔ ግብሩ የአረመኔ» በማለት በምሳሌ ይናገራሉ። ይህም ማለት ከላይ እንደ ተገለጸው ግብር ከአካባቢ የሚወረስ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ለሁሉም ነገር ዓይነተኛ መፍትሔው ቃለ እግዚአብሔርን መስማት፣ የቤተ ክርስቲያንን ድምጽ ማዳመጥ የመምሕራንን ትምህርት በተናጠልም ሆነ በማኅበር እየተረዱ ራስንና ሕሊናን ማስገዛት ከምንም በላይ ጠቃሚ ነው።

ምክንያቱም መንፈሳዊነት ያላሸው ሰውነት መልካም ሥራን ሥራ ሲሉት ወገቤን፣ ሃይማኖትህን አጥብቀህ ያዝ ሲሉት ልቤን እያለ እግዚአብሔርንና ሰውን ማሳዘኑ የማይቀር ስለሆነ ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወት ያልታሸ ሰውነት የሀገር ፍቅር የለውም፣ የወገን ኩራት ልቡን አይነሽጠውም ሊሞት ቢፈቅድ ለገንዘብ ሲል ይሞታል። ሊድንም ቢወድ ለገንዘብ ሲል ይሞታል።

ስለዚህ እያንዳንዳችን በምን ሕይወት ላይ እንዳለን ራስን መርምሮ አቋምን ማስተካከል እጅግ በጣም ወቅታዊና አስፈላጊም ነው።

ይህ በመሆኑ አባቶቻችን ያስጨበጡንን እምነት (ሃይማኖት) አለመልቀቅ፣ ያወረሱንን መልካም ሥነ–ምግባር አክብሮ መያዝ መንፈሳዊ ግዴታችን ነው።

ሐዋርያው «ለምትዋጁበት (ለመድኃኒት ቀን) መያተ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑት፤ መራራነት፣ ንዴት፣ ቁጣ፣ ጩኸት፣ ስድብና ማናቸውም ዓይነት ክፋት ሁሉ ከእናንተ ወዲያ ይራቅ» በማለት ያስተማረውን ሁል ጊዜ ልናዘክረው ይገባል። (ኤፌ.፬፥፴–፴፩)።

ለሰውነት ባልደረባው መልካም ሥነ–ምግባር ነው፤ የምግባርም ተያዥ ሃይማኖት ወይም እምነት ስለሆነ ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱ እንኳ ሲታጣ ክብር ይታጣል። ስለዚህ ለእያንዳንዱ ታዳጊ ወጣት ኢዮባዊ ትዕግሥት፣ አብርሃማዊ እምነት፣ ይስሐቃዊ ፈታደኝነት፣ ያዕቆባዊ ቅን አገልግሎት ዮሴፋዊ ኅዳጌ በቀልነት፣ ሙሴያዊ ለወገን ተቆርቋሪነት በጠቅላላው ክርስቶሳዊ ትሩፋት ሊኖረው ያስፈልጋል።

የዘመናችን ወጣት ጠባይ እያነሰው ምግባር እየጎደለው፣ ሃይማኖታዊ ሕግ እየፈረሰበት ፍቅረ ቢጽ (ሰውን መውደድ) እየተቀነሰበት ሊሠራው የሚገባውን ትቶ የማይገባውን እየሠራ በሃይማኖታዊ አካሄድ መራመድ እያቃተው፣ መንፈሳዊ ሥራ እየጎደለበት ወደ ገደል ለመግባት ሲፍገመገም ይታያል። መፍትሔው ግን ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ ነው። ሕገ እግዚአብሔር ከተጠበቀ፣ በየወቅቱ እናት ቤተ ክርስቲያን የምታስተላልፈው ቃለ ምእዳን ከተደመጠ ጥቅሙም ሆነ ጉዳቱ ከታወቀ በዘመናችን እንደሰደድ እሳት ከሚቀጣጠለው የዘመኑ በሽታ ራስን ማዳን ለወገንም መትረፍ ይቻላል።

በመሠረቱ በመንፈስ ጥበብ ያደገ፣ ከመልካም ቤተሰብ የተገኘ ማንኛውም ወጣት የራሱን ፈላጎት የመወሰን ከእናት ቤተ ክርስቲያኑ የሚገኘውን መንፈሳዊ ትምህርት የመግለጽ ችሎታ ስለሚኖረው አካባቢውን የመጠበቅና የማስተማርም ኃላፊነት አለበት። በመልካም ምሳሌነቱ፣ በአርቆ አስተዋይነቱ አካባቢውን ከመጥፎ ስሜትና አስተሳሰብ መለወጥ ይቻላል። «ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማዩ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» ተብሏልና። (ማቴ.፭፥፲፮)።

የመልካም ቤተሰብ ረድኤት ያልተለየው ማንኛውም ወጣት ከአካባቢው መጥፎ ልምድና አስተሳሰብ የራቀና የመጠቀ መሆን ስላለበት የአባቶቹን ፈለግ ተከትሎ የራሱንም ፈር ሳይለቅ፣ ማንንም ሳያፍርና ሳይፈራ ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዞ የሚራመድ መሆን ይኖርበታል።

ከቀደሙት ጀግኖች አባቶቻችን የምንማራቸውና ልናጤናቸው የሚገቡ ብዙ ዓበይት ቁም ነገሮች አሉ። አባቶች ስጦታ ከላይ በረከትም ከእግዚአብሔር መሆኑን ያምኑ ስለ ነበር በገንዘባቸው ንፍገት፣ በሰውነታቸው ጉትት፣ በአንደበታቸው ሐሰት፣ በልባቸው ክዳት ፈጽሞ አልነበረባቸውም።

«አባት ያቆየው ለልጅ ይበጀው» እንደሚባለው ልጆችም የአባቶችን ፈለግ ተከትለው፣ ወግና ሥርዓታቸውን ጠብቀው በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ጽኑእ እምነት ይዘው አቋማቸውን በሥነ ምግባር አስተካክለው ካልተጓዙ ዋግ እንደ መታው ቡቃያ ያለ ፍሬ መቅረታቸው የማይቀር ነው። «መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል» እንደ ተባለው ዕድል ፈንታቸውም መቀጨትና መቆረጥ ወደ እሳትም መጣል ነው። ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት እንደማይችል እምነተ ቢስ የሆነ፣ ሥነ ሥርዓት ያነሰው፣ ሥነ–ምግባርም የጎደለው ኅብረተሰብም ለሀገር ጠቃሚ፣ ለወገን አኩሪ ተቆርቋሪ የሆነ ትውልድ መተካቱ ያጠራጥራል።

ተክልን ካነሳን ዘንድ የሰውን ጠባይ በእንጨት ጠባይ መስለን ጥቂት አሳብ መግለጽ ይቻላል። መልካም ዛፍ ጥቅም በማስገኘቱ ደስ ያሰኛል መጥፎ ዛፍ ግን ያለ ፍሬ የበቀለበትን መሬት ሥራ ማስፈታቱ ያሳዝናል። ስለዚህ ጉዳይ በወንጌለ ሉቃስ ጌታ በምሳሌ ያስተማረውን ከዚህ ላይ መጥቀስ ያስፈልጋል። ቃሉም እንደዚህ ይነበባል «ለአንድ ሰው በወይኑ ሥፍራ የተተከለች በለስ ነበረችው። ከእርሷም ፍሬ ያገኝ ዘንድ ቢሔድ ሳያገኝ ቀረ። አትክልት ጠባቂውንም ከዚህች በለስ ፍሬ ባገኝ ብዬ ፫ ዓመት ተመላለስኩ። ነገር ግን አላገኘሁም ለምን ምድራችንን ታበዝናለች ቁረጣት አለው» (ሉቃ.፲፫፥፮–፰)።

ከምሳሌው የምንማረው ከሰውም ወገን ላንዱ የመልካም ዛፍ ጠባይ፣ ለሌላው ደግሞ የመጥፎ ዛፍ ጠባይ ሳይኖርው አልቀረም። መልካም ሰው ራሱን ከመጥቀሙም በላይ ማኅበራዊ ሕይወቱንም ፍሬያማ ያደርጋል። መጥፎ ሰው ግን ለመጥፎነቱ ከሚደርስበት ጉዳትም በላይ ማኅበራዊ ሕይወቱን ጨው የሌለበት አልጫ ያደርገዋል። እንግዲህ ሁላችንም የበለሲቱ ፈርድ እንዳይደርስብን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በተለይም መጥፎ አመል መታረሚያው በልጅነት ስለሆነ ወቅቱ ካለፈ ላርምህ ቢሉት እሺ በጄ አይልም።

ስለዚህ ምግባረ ጠማማ፣ ሃይማኖተ ደካማ ላለመሆን ሁላችንም ልናስብበት ይገባል። ከመልካም ሥነ–ምግባርና ከእውነተኛው ሃይማኖት ራቆቱን ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ሰው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ልብስ ልሁንህ ማለቱ የማይቀር ስለሆነ ማንኛውም ዜጋ ከሃይማኖትና ከመልካም ሥነ ምግባር ሊራቁት አይገባውም። ✣


ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል

የትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ኃላፊ




# የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የትንቢት ቀጠሮ


ከመምህር ዕንቈባሕርይ ተከስተ

የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ምክትል ኃላፊ




## ፩. ስለ መሲሑ የዓለም መድኅን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድና የበዓሉ አከባበር:-

ዝርዝር ሐተታ ከመሄዳችን በፊት ገና ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ትርጉሙ እነሆ።

ገና ማለት ከጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋ የተወረሰ ነው። ትርጉሙም ልደት ማለት ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ አዳም አባታችን ወዶ በሥራው ኃጢአት ምክንያት የዓለም መድኅን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ተወለደበት ጊዜ ድረስ ዓለም በጨለማ ጉዞ ይጓዝ ነበር። (ኢሳ.፱፥፪)

ጌታችን ከተወለደ በኋላ ግን በጨለማ ጥላ ሥር ይንከራተትና ፍዳውን ይቈጥር ይኖር የነበረ ሕዝብ ብርሃን አየ፣ ተስፋ ያልነበረው ሕዝብ የተስፋ ባለቤት ሆነ፣ የጨለማና የኀዘን የሥቃይ፣ የፍዳ፣ የገፈና የተገፈ መናኸሪያ የነበረው አሮጌው ዓለም በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ዓለም ሆኗል። (ኢሳ.፱፥፪፣ ሮሜ.፲፫፥፲፪)።

## ፪. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለምን ይሆን?

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ብዙ ብዙ መንፈሳውያን አባቶችና የዓለም ሊቃውንት ብዙ ብለዋል። ብዙ ጽፈዋል። የሁሉንም ሐሳብ አጠቃሎ የምናገኘው ግን እነሆ እውነቱን ከሐሰት በመለየት አምላካዊ ቃል ብቻ የያዘ ቅዱስ መጽሐፍ ሲሆን እሱም ትንቢቱን ከፍጻሜው ፍጻሜውን ከትንቢቱ በማገናዘብ የትንቢቱ ተናጋሪና የትንቢቱን ፍጻሜ ምዕራፍና ቁጥሮች በትክክል በማያሻማ መልኩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

፫. ትንቢት ማለት ወደ ፊት የሚሆነውን፣ ወይም የሚመጣውንና ጊዜው ሲደርስ የሚፈጸመውን ነገር ገና ከመድረሱ በፊት የማወቅ ዕድልና ስጦታ ነው።

በዚህ ቃል የሚጠቀሙበት መጽ አያትን ሁሉ አስቀድመው አውቀው፣ በእንደዚህ ያለ ዘመን ውስጥ እንዲህ ይሆናል፣ ብለው ትንቢት የሚናገሩትን አዋቂዎች ነቢያት ተብለው ይጠራሉ። ትንቢትም ሲባል በሁለት ክፍል የተመደበ ነው።

፩. በእግዚአብሔር መንፈስ ለሰው ልጆች የሚገለጽ ትንቢትና ራእይ፣

፪. ለጥቅም ፍላጎት ጳላዕያን ሠናያት ከሆኑ ከልዩ ልዩ ረቂቃን መናፍስት የሚገኝ ሐሰተኛ ትንቢት ነው። በሁለተኛ ቁጥር የተጠቀሰው የትንቢት ዓይነት ጥንቆላ እንጂ ትንቢት ሊሆን አይችልም።

እንግዲህ የሐሰቱን እንተወውና ወደ እውነተኛው ትንቢት እንሻገር።

አዳም በእባብ ምክንያት ከምድረ ርስት (ገነት) ቢሰደድም እግዚአብሔር አምላክ ግን አልተወውም በኋለኛውም ዘመን እንደሚያድነው ለዚህም የባሕርይ ልጁን ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጅን እንደሚልክ የድኅነት ተስፋ ሰጥቷል። የአዳም ልጆችም ይኸንን የድኅነት ተስፋ ቀን ለማወቅና ለመረዳት ፈልገው ያች የሚወለድባትን (የድኅነት) ቀን ለማግኘት እኩሌቶቻቸው በጨረቃ፣ እኩሌቶቻቸው ደግሞ በከዋክብት፣ በፀሐያዊ ብርሃን ሲቆጥሩ ኑሯል። እግዚአብሔርም የዘመኑ (የመከራ መዋዕል) ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ የወዳጆቹ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ አንድያ ልጁን ወደዚህ ዓለም ላከ።

## ትንቢት

፩. በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ ጠላትን አደርጋለሁ። ርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ። (ዘፍ.፫፥፲፭) እግዚአብሔር።

፪. ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፣ ርሱንም ታደምጣለህ። (ዘዳ.፲፰፥፲፭) ነቢዩ ሙሴ።

፫. የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ (ዘፍ.፳፪፥፲፰) እግዚአብሔር።

፬. አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም፣ እመለከተዋለሁ፣ በቅርብ ግን አይደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል (ዘኁ.፳፬፥፲፯) በለዓም።

፭. እነሆ ድንግል ወልድን ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች (ኢሳ.፯፥፲፬) ነቢዩ ኢሳይያስ።

፮. «ሕፃን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ» ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል (ኢሳ.፱፥፮–፯) ኢሳይያስ።

፯. አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ...ከአንቺ አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ በእስራኤል ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል (ሚክ.፶፥፪) ነቢዩ ሚክያስ።

፰. አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ (ዘካ.፱፥፱)።




www.ethiopianorthodox.org

፱. ነቢዩ ዳንኤል የተናገረው የተነበየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚወለድበት ጊዜና ስለሚጠመቅበት፣ ራሱን አሳልፎ ስለሚሰጥበት፣ ከሰው ልጆች ጋር ቃል ኪዳን ስለገባበት ጊዜ ለይቶ ያስረዳል። (ዳን. ፺፡፳፭–፳፯)።

## ፍጻሜ

፩. የዘመኑ ፍጻሜ (ቀጠሮ) በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ። (ገላ.፬፡፬) (ቅዱስ ጳውሎስ)

፪. ሙሴም ለአባቶች ጌታ አምላክ እኔን እንደ አስነሳኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ፣ ያስነሳላችኋል፣ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት ያንም ነቢይ የማትሰማ ነፍስ ሁሉ ተለይታ ትጠፋለች (የሐዋ.፫፡፳፪) ቅዱስ ጴጥሮስ።

፫. የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ (ማቴ.፩፡፩፤ ቅዱስ ማቴዎስ ገላ.፫፡፳–፲፰) ቅዱስ ጳውሎስ።

፬. የንጋት ኮከብ እኔ ነኝ (ራእ. ፳፪፡፲፮) ቅዱስ ዮሐንስ።

፭. (ማቴ.፩፡፲፰፤ ፊልጶ. ፫፡፲፰)። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል (ሮሜ. ፰፡፴፰) ቅዱስ ጳውሎስ።

፮. እርሱ ታላቅ ነው የልዑልም ልጅ ይባላል። ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊት ዙፋን ይሰጠዋል (ሉቃ.፩፡፴፪) ቅዱስ ገብርኤል።

፯. ማብራሪያ ሚክያስ የተነበየው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚወለድበት ቦታ ነው። (ማቴ.፪፡፩–፮፤ ዮሐ.፯፡፵፪)።

፰. ዮሐ.፲፪፡፲፱፤ ማቴ.፳፩፡፮–፲፩።

፬. በዓሉ መከበር የተጀመረው መቼ ነው? ቀኑስ ምን ቀን ይውላል?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን እርግጠኛውን ዕለት ለማወቅ የአስትሮኖሚ፣ የአርኪዎሎጅና የታሪክ ምርምር ሰዎች (ሊቃውንት) ብዙ ጥናት አድርጓል። ዳሩ ግን በአንድ ሐሳብ ሊስማሙ ባለመቻላቸው፣ የክርስቲያኑ የቀን መቁጠሪያዎች በዚሁ ሁኔታ አንድ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ መከበር የተጀመረው ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ታሪክ ያስረዳል።

ለዚህም በጎርጎርዮሳውያን የዘመን አቈጣጠር የሚጠቀሙት የዓለም ሕዝቦች የክርስቶስን ልደት እኛ ኢትዮጵያውያን ከምናከብረው የልደት በዓል ፲፫ ቀን ቀድመው ያከብራሉ።

የሮም ቤተ ክርስቲያን የጌታን ልደት በታኅሣሥ ፳፭ ቀን ታከብር እንደ ነበር ከ፫፻፴፮ ዓ.ም ጀምሮ ግልጽ ነው። ይህ ቀን በአህዛብ ዘንድ የፀሐይ በዓል እየተባለ ይከበር ስለ ነበር ክርስቲያኖች ይኸንን የጣኦት አምልኮ ጠባይ ያለውን በዓል ለማጥፋት ሲሉ የጌታን ልደት በዚሁ ቀን ማክበር ጀመሩ።

## የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያንም

ቅድሚያ ሰጥታ የምታከብረው እ.ኤ.አ ጥር ፮ ቀን የሚውለን የኤጲፋንያ በዓል ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የጌታን ጥምቀቱና ልደቱን ጥር ፮ ቀን ስታከብር እንደ ቆየች የእውቀትና የታሪክ መድበል (ኢንሳይክሎፕዲያ) ይገልጻል።

## ፭. ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስት ሆን በክርስቲያን ዓለም ውስጥ እንዲህ ያለ ልዩነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ?

በመሠረቱ ዓለም ከመለያየት በስተቀር አንድ ለመሆን ያሰበበት ወቅት ምን ጊዜ የለም። (በታሪክ እንደ ምንረዳው)

## ልዩነቱ እንዴት እንደ ሆነ እንመልከት።

ከጌታ ልደት አስቀድሞ (በፊት) በ፵፮ ዓ.ዓ ጁሊዮስ የተባለው የሮማ ቄሣር በጊዜው የከዋክብት መርማሪ የነበረው ሶስግነስን አስጠርቶ ተመሰቃቅሎ የነበረውን የዘመናቸ አቈጣጠር እንዲያስተካክል አዘዘው።

ይኸም፣ ሊቅ ፈቃደኛ ሆኖ ዓመቱንም በ፲፪ ወሮች ከፋፍሎ እያንዳንዱን ወር ከየካቲት በስተቀር በማፈራረቅ ፴፩ እና ፴ ቀናት እንዲኖራቸው አድርጎ አዘጋጀ። የካቲት ወር ግን ፳፱ ቀን እንዲኖረው አደረገ።

ነገር ግን በየአራቱ ዓመቱ አንድ ቀን ትርፍ ስለሚመጣ በአራተኛው ዓመት የካቲት ፴ ቀን እንዲሆን ወሰነ። ጁሊየስ ቄሣርም የሮማው ሕዝብ በዚሁ እንዲገለገል አዋጅ አወጀ። በተጨማሪም ጁሊየስ የዓመት መለወጫ መጋቢት የነበረውን ለውጦ (አዛውሮ) ጥር እንዲሆን አደረገ።

በዚሁም የጁሊየስን የዘመን አቈጣጠር ብዙ አገሮች ለ፩ ሺህ ፭፻ ዓመት ያህል ሲገለገሉበት ቈይተዋል። ምክንያቱም የዓመቱ ቀናት ተቀምረው ፫፻፷፭ ቀን ከሩብ ሊሆን መቻላቸው ነበር። ይህም ሆኖ የጁሊየስ አቈጣጠር ህጸጽ አልታጣበትም ምክንያቱም ፲፩ ደቂቃ ከ፲፬ ሰኮንድ ትርፍ ያሳይ ነበርና። ከዚህም የተነሳ እ.ኤ.አ በ፩ ሺህ ፭፻፹፪ ዓ.ም የነበረው የሮማው ፓፓ ጎርጎርዮስ (ስምንተኛ) የከዋክብትን ሊቃውንት ሰብስቦ ከተመካከረበት በኋላ የዘመኑ አቈጣጠር ተሻሽሎ እንዲሰራበት አዋጅ አስተላለፈ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጎርጎርዮስ የዘመን አቈጣጠር መቍጠር ጀመረች። በእምነት ተከታዮቻቸው የሆኑትም አገሮች ተቀብለው ወድያውኑ በሥራ ላይ ሲያውሉት የጀርመን ግዛቶች ግን እስከ ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በጁሊዮስ አቈጣጠር ይጠቀሙ ነበር። እንግሊዝም ብትሆን አዋጁን የተቀበለችው በ፩ ሺህ ፯፻፶፪ ዓ.ም እ.ኤ.አ ነው። ከዚያ ወዲህ ግን ምዕራባውያን አገሮች ተቀብለውታል።

ይህም ሊሆን የቻለው በ፩ ሺህ ፭፻፹፪ ዓ.ም የተጨመሩት ፲ ቀናት ተጠራቅመው ጎርጎርዮስና ጁሊዮስ በተባለው የዘመን አቈጣጠር መኻከል ልዩነት ስለፈጠሩ ነው።

በዘመን አቈጣጠር ልዩነት ተነሳ የምዕራባውያንና ኢትዮጵያውያን የልደት በዓልን በማክበር በ፲፫ ቀኖች ይለያያሉ። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው እንደተናገርኩት ዓለም ብዙ ጊዜ ስለ ዘመን አቈጣጠር ችግር ገጥሟት እንደ ነበረ ግልጽ ቢሆንም ኢትዮጵያ ግን በዘመነ ኦሪትም ሆነ በዘመነ ሐዲስ እንደ ንጋት ኮከብ የሚያበሩ ልጆች ስለ ነበሯት በቍጥር ግራ አልተጋባችም ቀድሞም ዛሬም ባህልዋንና ቀመርዋን እንደያዘች ትገኛለች።

ስለዚህ የኢትዮጵያ አቈጣጠር ደግሞ እንደሚከተለው እንመልከት

## ፮. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቈጣጠር

በዘመናችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታ ልደት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንደሚያከብሩት ለምን አታከብርም? የሚል ጥያቄ በየአቅጣጫው ከተሰማ ውሎ አድሯል። አንድ ነገር መታወቅ ያለበት ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለ ልደትን ፳፱ ቀን የምታከብረው ብቻዋን ሳትሆን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር መሆኑ ነው።

በቀን አከባበር ስለተፈጠረው መለያየት ምክንያቱንና የነገሩን ምንጭ ከእንማስረጃው አትቶ «በእንተ ልደት ድንግልናዊ» በሚል ርዕስ የእስክንድርያው ሊቅ ዮሐንስ አቤል ሄሬም ጽፎት ይገኛልና ከዚያ መመልከት ይጠቅማል (አንቀጽ ፹፬) ዓይነተኛ ጉዳዩ ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት የተመሠረተ ነው ብላ ስለ አመነችበት እንጂ ብዙ ዘመናት ሲሠራበት በመቈየቱ ወይም ደግሞ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ስለምታከብረው ብቻ አይደለም።

በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አለው ማስረጃ እንደሚከተለው እንረዳለን። መጥምቁ ዮሐንስ የተፀነሰበትም ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማኅፀን ለተጸነሰበትና ለተወለደበት ቀን መነሻ ሆኖ የሚገኝበት አለ።

ይኸንም ለመረዳት ወንጌላዊ ሉቃስ የጻፈውን እንመልከት።

በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ። ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች፣ ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ። ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ።

ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፣ ሁለቱም በዕድሜያቸው አርጅተው ነበር። እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል፣ እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት።

በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር። የጌታም መልአክ በዕጣኑም መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፣ ፍርሃትም ወደቀበት። መልአኩም እንዲህ አለው። «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ፣ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፣ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፣ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና» (ሉቃ.፩፡፭–፲፭)።

ወንጌላዊው ከተረከው የተገኘ ቅርጸ ሐሳብ የቱ ነው? ተብሎ ቢጠየቅ ትክክለኛ ጥያቄ ሆኖ ይገኛል።

ፍሬ ሐሳቡ መልአኩ ገብርኤል ለዘካርያስ ስለመጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ያበሠረበት ጊዜው መቼ ነው? የሚለው ነው። ይኸ በዕብራውያን ዘንድ «በዓለ አስተሥርዮ» ተብሎ ይከበር የነበረው ቀን መሆኑ ነው። በዓለ ሥርየትም ሲባል ደግሞ በዕብራውያን አቈጣጠር በሰባተኛው ወር ማለት (ጥቅምት አሥር ቀን የሚውል ታላቅ በዓል ነው) (ዘሌ. ፲፯፡፳፱–፴፬፤ ዘኁ.፳፱፡፯–፲፩)። እነሆ ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ መልአኩ ያበሠረው በዚህ ጊዜ ነው። (ሉቃ.፩፡፰–፲፤ ፳፩)።

ይህ ዘካርያስ የተበሠረበት ቀን የአይሁድ በዓለ ሥርየት የዋለበት በዕብራውያን የዘመን አቈጣጠር ጥቅምት ፲ ቀን ለመሆኑ ከጥንት አባቶች ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ማር.ዮሐንስ መስክረዋል።

አሁንም ደግሞ ይህ ቀን ከኢትዮጵያ የቀን አቈጣጠር ያለው ተዛምዶ እንደሚከተለው ነው። መጀመሪያ ነገር በባሕረ ሐሳቡ የአቈጣጠር ሕግ እንደሚታወቀው ሁሉ ፭ ሺህ ፭፻ ዓመተ ዓለምን በዐቢይ ቀመር፣ በንዑስ ቀመር፣ በማዕከላዊ ቀመር ተተንትኖ ተከፋፍሎ ውጤቱ የ፭ ሺህ ፭፻ ዓመተ ዓለም ተረፈ ቀመር ፱ ሆኖ ስለሚገኝ አንድን ለዘመን አትቶ መነበሩ ፰ ይሆናል። አበቅቴው ፳፰፣ ካለፈው የተያዘ ፲፩ የጨረቃ እና ዕለቱ ፳፰ አበቅቴ ሲደመር ሠረቀ ሌሊቱ ፲ ሆኖ መጥቅዑም ፪ ይሆናል።

በሠረቀ ሌሊቱ ፲+፬=፲፬ ጨረቃ ሆነ።

እንግዲህ ፲፬ የጨረቃ ሌሊት ይዘን እስከ መስከረም ፲፯ ቀን ብንሄድ በዚያን ጊዜ የጨረቃ ብርሃን ፳፱ መሆኑን ያሳየናል። መስከረም ፲፰ ቀን ደግሞ የጨረቃ ብርሃናዊ ልደት ነው። የአይሁድ የቀዳማዊ ወርኀ ታሥሪን (መባቻ) ነው።

በኢትዮጵያ ዐሐያዊ አቈጣጠር መስከረም ስለ አሳለቀ እንዲህ እያልን እስከ መስከረም ፳፯ ቀን እንሄዳለን። በዕብራውያን ጥቅምት ፲ ቀን ሲሆን በእኛ ደግሞ መስከረም ፳፯ እንደ ነበረ እንረዳለን።

በዚሁ ዘካርያስ ልጅ እንደሚወልድ ተበሠረ።

ዘካርያስም ይህን አገልግሎት ከፈጸመ በኋላ ከበዓለ ሥርየት በኋላ እስከ ፲፭ኛው የጥቅምት ጨረቃ በዓል ስለ አልነበረ ወደ ቤቱ ገባ መጥምቁ ዮሐንስ ተጸነሰ። ይህም ሊቁ ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ «ከሁለት ቀንም በኋላ ኤልሳቤጥ ጸነሰች» በማለት አስረድቶናል። (በጎ «ብርሃነ ሕይወት» ድጓ የታኅሣሥ ገብርኤል) ቅዱስ ያሬድ ከሁለት ቀን በኋላ ኤልሳቤጥ ጸነሰች ያለው ቀንና ዘካርያስ ልጅ እንደሚወልድ እስከ ተበሠረበት ድረስ ያለው ቀን ብንደምረው ከመስከረም ይዘነው የመጣን ፳፯ ቀን፣ የክህነት አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ ቤቱ እስከ ተመለሰበት ድረስ ያለው ጊዜ ፫ ቀን፤ ፳፯+፫=፴ ቀናት ይሰጠናል።

ሐዋርያው ሉቃስ ወደ ጻፈው ቃል እንመለስ

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ኤልሳቤጥ ከጸነሰች በስድስተኛው ወር ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መላኩ፣ እና ቅዱስ ሉቃስም ዮሐንስ ከተጸነሰ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስም በስድስተኛው ወሩ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ሰው የሆነበት ዕለት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜና የቁጥር መምህራን በማያሻማ መልኩ ተንትነው ቀምረው ለዚህ ትውልድ ማድረሳቸው እግዚአብሔር ከእነሱ ጋር እንደ ነበር ቋሚ ማስረጃ ነው።

እንግዲህ የዮሐንስ ትንቢታዊ መጸነስ ክርስቶስ ሰው ለሚሆንበት ቀን የዕለታት ሩናው እያበራ ክርስቶስ ተጸንሶ እስከ ተወለደበት ዕለት ያደርሰናል።

## ፯. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጋቢት ፳፱ ቀን ተፀንሶ፣ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ስለመወለዱ:-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መቼ ተጸንሶ መቼ እንደ ተወለደ ለማወቅና ለመረዳት ሐዋርያው ሉቃስ ወደተለመልን የአኀዝ ቁጥር እንመለሳለን።

«እነሆም በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል በናዝሬት ወደምትኖር ወደ ድንግል ማርያም ተልዕኮ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትጸንስና እንደምትወልድ ነገራት (ሉቃስ ፩፡፳፮–፴፰) ይህም ቀን በኢትዮጵያ አቈጣጠር መጥምቁ ዮሐንስ ከተጸነሰበት ዕለት ጀምሮ ተቈጥሮ መጋቢት ፳፱ ቀን መሆኑ እንገነዘባለን። ለምሳሌ ጥቅምት፣





www.ethiopianorthodox.org

ኅዳር፣ ታኅሣሥ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት ድምር ፮ ወር ነው።

ስለዚህ መጋቢት ፳፱ ቀን ቃል ሥጋ የሆነበት በድንግል ማኅፀን ያደረበት በዓለ ትስብእት ነው። አሁን (ሰው የመሆኑ) ሰው የሆነበት ቀን ከተረዳን የተወለደበት ቀንና ወር ለማረጋገጥ ከመጋቢት ፳፱ ቀን እስከ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ጳጉሜን ጨምሮ ያለው ጊዜ ፪፻፸፭ ቀናት ይሆናሉ። ይህም ፪፻፸፭፣ ለ፴ ሲካፈል ፱ ወር ከአምስት ቀን ይሆናል። ይህም ማለት ከመጋቢት ፪ ቀን፣ ከሚያዝያ እስከ ኅዳር መጨረሻ ወር ያሉት ወራት (፰×፴=፪፻፵) ቀናት፣ ፭ ቀን የጳጉሜን፣ ፳፱ ቀን ከታኅሣሥ፣ አጠቃላይ ድምር ፪፻፸፭ ቀናት ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሠ ድንግል ፱ ወር ከአምስት ቀን ከቈየ በኋላ በዕለተ ሠሉስ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በ፭ ዓ.ም ከሌሊቱ ፯ ሰዓት እስከ ፲ ሰዓት ባለው ጊዜ በቤተልሔም ተወለደ። (ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ገጽ ፩፻፶፰ እና ፩፻፶፱)።

ይህም በሐሳባዊ መንገድ የሚደረስበት ስለሆነ አያጠራጥርም። ሕጋዊ የሆነ የወንድ ልጅ በእናቱ ማኅፀን ተጸንሶ እስከሚወለድበት ጊዜ ድረስ የሚቈይባቸው ቀናት ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ለመሆኑ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ታምኖበት የቈየ ነው። አንዳንድ የቀናት መብዛትና ማነስ የሚታየው ህጸጽ አይነካውም (ኢሳ.፯፥፲፬፤ ገላ.፬፥፬።)

እነሆ ምሥራቃዊ ኮከብ ሰብአ ሰገልን የተወለደው ሕፃን እስከ አለበት ቦታ እየመራ እንዳደረሳቸው ሁሉ ወንጌላዊው ሉቃስም እያነጣጠረ ያመለከተው ዘካርያስ የተበሠረበት ኮከባዊ ቀንም ፋናውን እየተቈጣጠረች ለምትከታተል ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ተወለደበት እንዳደረሳት ታምናለች።

ስለዚህም ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታን ልደት ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በታላቅ ምሥጋና ታከብረዋለች። (ማቴ. ፪፥፩–፲፩፤ ፪ጴጥሮስ ፩፥፲፱–፳፩)።

ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር በዓለ ልደትን የሚያከብሩ አገሮች ወይም አብያተ ክርስቲያን:- ግብጽ፣ ሶርያ፣ ህንድ፣ ኢትዮጵያ፣ አርመን ሲሆኑ ከሩቅ ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የግሪክ ኦርቶዶክስ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

አውሮፓውያን በዓለ ልደትን የሚያከብሩት ከእኛ ፲፫ ቀናት ቀደም ብለው ነው። ይህም ማለት በእኛ አቈጣጠር ታኅሣሥ ፲፮ ቀን ነው እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቈጣጠር December ፳፭ ቀን ነው።

ልዩነቱ ለማወቅ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለ ልደትን የምታከብረው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው ይህም ማለት ከ፳፱–፲፮=፲፫ ቀናት ወይም ፲፮+፲፫=፳፱ ቀን ይሆናል።

ይህ ቁጥር የሚያሳየን አውሮፓውያን ከእኛ በ፲፫ ቀናት ቀድመው በዓለ ልደትን ሲያከብሩ ኢትዮጵያውያን ግን ከ፲፫ ቀናት በኋላ ቈይተው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በዓለ ልደትን ያከብራሉ።

## ፰. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ለመወለዱ የመሰከሩ ሊቃውንት

፩. ማሬ ኤፍሬም ሶርያዊ
፪. ሰዓ..ድ ወ/በጥሪቅ
፫. መበንጋዊ/ማኅበብ
፬. ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ
፭. ወልደ መነኮስ
፮. በዲድስቅልያ አንቀጽ ፳፱
፯. የኢትዮጵያ መምህራን ሁሉ ናቸው።

## ፱. የልደት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ ከሕዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት።

በኢትዮጵያ የገና (የበዓል ልደት አከባ በር) ገና በዋዜማው ጀምሮ የአከባበሩ ሥርዓት ይጀመራል። ከምሽቱ ፪ ሰዓት ሲሆን የጌታን መወለድ የምሥ ራች የሚያበሥሩ የአብያተ ክርስቲያናት ደወሎች ለ፳ ደቂቃ ድምጻቸውን ያስተጋባሉ። ካህኑም ሆነ ሕዝቡ (ከልሂቅ እስከ ደቂቅ) ነጭ የባህል ልብሳቸውን እየለበሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ። ከዚያም ካህናቱም ሕዝቡም በማኅሌት፣ በጸናጽል በከበሮ «ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም» እያሉ በኅብረት እየዘመሩ እስከ ቅዳሴ ይቈያሉ። ቅዳሴ ተቀድሶ ሠርሆተ ሕዝብ የቅዳሴ ፍጻሜ ከሆነ በኋላ በ፱ ሰዓት ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። ከነጋም በኋላ ዘመድ ከመጠየቅ አስቀድመው በአካባቢው ያሉ ድሆች ጠርተው በአንድ ላይ ዘመድም ሆነ ድሃው ሁሉ በአንድ ላይ በቤት የተገኘውን አብረው ይቀምሳሉ። ስጦታም ይለዋወጣሉ። ቤታቸውንም ቀጤ[illegible]ፊላ በመጎዝጎዝ፣ አበባ በማዘጋጀት ያሳምሩታል። የሚበላውም የሚጠጣውም በሰፊው ይቀርባል። ማለት ዳቦ በመጋገር፣ ጠላ በመጥመቅ፣ ጠጅ በመጣል፣ በግ፣ ደሮ በማረድ ሰንጋውን በመቁረጥ በዓሉን ያከብራሉ።

የልደት ዕለት መሶቡ ሁሉ ሳይቀር በተለይ በከተማ አካባቢ አጊጦ ይውላል። ስለዚህ «ልደትሰ በኵሉ ልደት ጸውአኒ በካልዕ ዕለት» ተብሏል። (የአገሬው ሰውም «እሰይ ጌታ ተወለደ ዲያብሎስ ልቡ ነደደ») እያሉ መንፈሳዊ ስሜታቸውን ይገልጻሉ።

## ፲. እረኞችና ባህላቸው

እረኞቹ በዚሁ ዕለት በቡድን በቡድን ሆነው ገናን ይጫወታሉ። ብትራቸውን እየሸለሙ በማቁራቱስ ደስታቸውን ይገልጻሉ። ይህ የሚደረገው «ዮም መላእክት ወሰብእ አሐደ መርዔተ ኮኑ» «ዛሬ ሰውና መላእክት አንድ ሆነዋል» ከሚለው በማያያዝ ነው። (ሉቃስ ፳፰፥፲፭) ብትሩም ሽልምልም መሆኑ በያዕቆብ ብትር ምሳሌ ነው። ያዕቆብ «ልብን ለውዝ ኤርሞን ከሚባሉት እንጨቶች እርጥብ በትርን ወስዶ በበትሮቹ ውስጥ ያለው ነጭ እንዲታይ ነጭ ሽመልመሌ አድርጎ ጣላቸው።

የጣላቸውንም በትሮች በጎቹ ውኃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ በውኃ ማጠጫው ገንዳ ውስጥ በጎቹ ፊት አኖራቸው፣ በጎቹ ውኃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ ይጎመጁ ነበር። በጎቹም በትሮቹን አይተው ከመጎምጀታቸው የተነሣ ፀነሱ፣ በጎቹም ሽመልመሌ መሳይና ዝንጉርጉር ነቁጣም ያለበቱን ወለዱ።» (ዘፍ.፳፱፥፴፯–፵)።

ያዕቆብ የራሱ የሆነው ጥሪት (ንብ ረት ለመለየት ሲል መልአኩ በሕልም በነገረው መሠረት በመታዘዙ የእግዚአብሔር በረከት አገኘ። በጎቹም በዙለት። ያ ባህል ያ ልምድ በእረኞቻችን የሚፈጸመው ከጥንት ተያይዞ የመጣ ነው።

ይኸም ሁሉ የፍቅር ምልክት ነው። እረኞችና መላእክት አብሮ መዋላቸው ሰውና እግዚአብሔር የታረቁ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ✣

«ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር» ብለው አብረው አመስግነዋልና። እንግዲህ የልደት አከባበር በኢትዮጵያ ይህን የመሰለ ነው።

ስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን

# ቅዱስ ላሊበላና ቅድስት መስቀል ክብራ

ከግርማ ኤሊያስ

ቅዱስ ላሊበላ ንጉሥ ከአባቱ ከገርን ስዩምና ከእናቱ ከሬውራ በተወለደ ጊዜ አእላፍ ንቦች በሰውነቱ ላይ አረፉ፣ በዚህ ምክንያት እናቱ ከሬውራ የአገው ብሔረሰብ ተወላጅ ስለ ነበረች የተወለደው ልጅዋ ንቦች ከበውት ባየች ጊዜ ላል ይበላል ስትል ተናገረች በአገውኛ ቋንቋ የንብ ልጅ ማለት ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ላሊበላ የሚል ስም አወጣችለት።

ቅዱስ ላሊበላ እንደ ሀገሩ የትምህርት ባህል መሠረት አባ ዳንኤል ከተባለ አስተማሪ መነኩሴ ፊደልን፣ ንባብን፣ ዳዊትን፣ እየተማረ ካደገ በኋላ የተሻለ ትምህርት ለመማር ሲል ከላስታ ወደ ጎጃም ሄዶ አጠቃላይ መንፈሳዊ ትምህርትን እየተማረ ሳለ በትምህርቱና በእውቀቱ ከጓደኞቹ በልጦ ስለ ተገኘ ጓደኞቹ ቀንተው በምቀኝነት በመነሳሳት ሰው የሚበላ ነው ለማሰኘት ለመምህሩ ከሚያፈላው የእህል ወጥ ውስጥ የወጣት ልጅ ቀኝ እጅ ቆርጠው በማምጣት ወጥ ከሚያፈላበት ድስት ላይ በመጨመር ይኸውና ከድስቱ ውስጥ የሰው እጅ ብለው በማውጣት በተንኮል ከመምህሩ ጋር አቀያየሙት።

ቅዱስ ላሊበላም የራሱን ንጽህና ሐቀኝነት በሚገባ ስለሚያውቅ ሰው በላ ከተባል ኩኝ ብሎ እያዘነ አንድ ዲያቆን አስከትሎ ወደ ትውልድ ሀገሩ ላስታ ቡግና ደብረ ሮሃ ተመልሶ ሥልጣነ መንግሥት ይዞ ሀገር ከሚያስተዳድረው ሐርቤ (ገብረ ማርያም) ዘንድ አብሮ መኖር ሲጀምር ሲወለድ ንቦች የከበቡት ላሊበላ የሚባለው ልጅ ይነግሣል የሚል ትንቢት በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ በስፋት በምሥጢር ይሰራጭ ጀመር።

የቅዱስ ላሊበላን የወደፊት የንግሥና ትንቢት የሰማች ለሀርቤ የአባትና እናት ልጅ ለላሊበላ ግን ያባት ልጅ የሆነች ዮዲት የተባለች እህቱ ሰምታ ለእናቷ ልጅ ሀርቤ እድልታ ላሊበላን የምትገድልበት ዘዴ ስታውጠነጥን ቈይታ ከዕለታት አንድ ቀን ላሊበላ ኮሶ ታይቶት እንደ እህት መጠን የሚያሽር ኮሶ አዘጋጅታ በውስጡ ከመቅዕበት የሚገድል መርዝ አንድ ላይ ቀምማ ጠጣ ብላ ስትዘጋጅ ላሊበላን በቅርብ የሚረዳ ዲያቆን አስቀድሞ መቅመስ ነበረበትና ዲያቆኑ ቢቀምሰው ወዲያውኑ ደም ተፍቶ ሞተ። የዲያቆኑ ትውከት የቀመሰች ውሻም ወዲያውኑ ተንፈራፍራ ሕይወትዋ አለፈ።

ቅዱስ ላሊበላም እርሱን በቅናት ለመግደል ተብሎ ባባቱ ልጅ በተቀመመው መርዝ ረዳቱ ዲያቆንና ውሻው ከግንባሩ ተደፍተው ባየ ጊዜ እጅግ በጣም ከልቡ አዝኖ እኔም መሞት አለብኝ ብሎ ከዋንጫ የተረፈውን የተመረዘ ኮሶ የያዘ ዋንጫ አንስቶ ቢጠጣ እርሱም እዚያው ሕይወቱን ስቶ ወደቀ።

በዚህ ጊዜ ምን ጊዜም የሚጠብቀውና የሚረዳው ቅዱስ ገብርኤል በአካለ ነፍስ ይዞት ሰማየ ሰማያት በማረግ ኤረር፣ ራማ፣ ኢዮር፣ ዓለመ እሳት፣ ሰማይ ውዱድ፣ መንበረ ስብሐት፣ ጽርሐ አርያም፣ የተባሉ ሰማያትን ደረጃ በደረጃ እያዞረ በማሳየት ዝማሬ መላእክትንና ስብሐተ መላእክትን እያዞረ አሰማው፣ በመጨረሻም ከእግዚአብሔር መንበር ፊት ቀርቦ ብርሃን መለኮቱን ባየ ጊዜ በድንጋጤ ወድቆ ሰገደ።

በዚህ ወቅትም ፈጣሬ ኵሉ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ገብርኤል አማካይነት ከፊቱ ተደፍቶ ለወደቀው ቅዱስ ላሊበላ እንዲህ ሲል ተናገረው።

«ታማኙ ተከታዬ ላሊበላ ሆይ እንዴት አለህልኝ ጥበብና ስልጣኔ እገልጽልህ ዘንድ፣ ስልጣኔ እዚህ ድረስ አመጣችህ፣ አሁንም አይዞህ በሥራህ፣ በሞያህና በታሪክህ የድንቅ ድንቅ የሚባል ስም ይወጣልሀል፣ የጥበብህና የሞያህ ውጤት በዓለማት ሁሉ እየተነገረ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይኖራል። ወዳጄ ላሊበላ ሆይ አንተ ስለ እኔ ፍቅርና ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ስትል የሚገድል መርዝ እንደ ጠጣህና እንደ ሞትክ ሃይማኖት ፅኑዕ ሆነህ ስለተገኘህ ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ገልጩልሀለሁኝ ዓይነ ልቦናህን ሳታባክን አስተውለህ ተመልከት ያሳየሁህን ልብ አድርግ በዚህ ዓለም እኔ የምመሰገንበትንና አንተም ስምህ ለዘለዓለም ሲጠራበት የሚኖር ቤተ መቅደስ በመላእክት ረዳትነት ከአንድ የዓለት ቋጥኝ ፈልፍለህ ታንፃለህና ልብ አድርግ»

በማለት የጥበብ ምስጢር በመግለጽ ሌላም ቃል ኪዳን ገባለትና አሰናበተው።

ቅዱስ ላሊበላም ከፈጣሪው ፊት ቀርቦ የጥበብ ምስጢርና ቃል ኪዳን ከተሰጠው በኋላ አሁንም ከምድር ወደ ሰማየ ሰማያት ይዞት ያረገው መልአከ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ሦስት ሌሊትና ሦስት መዓልት በሰማየ ሰማያት አቈይቶ ለቤተ ዘመዱ አስከሬን ሆኖ የሰነበተው ቅዱስ ላሊበላ እንደ ገና ነፍሱን ከሥጋው ጋር በማዋሀድ ከእንቅልፉ እንደሚባንን ሰው መቀትና ሕይወት ተዋሕዶት ሕያው ሆኖ ተነሣ።

ቅዱስ ላሊበላ ቀደም ሲል በጎጃም ትምህርት ቤት ጓደኞቹ፣ አከታትሎም በነገሠው ወንድሙና እህቱ ሴራ መርዝ ጠጥቶ ከደረሰበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ከዘመድ ከወገን ተለይቶ፣ ይህ ዓለም ይቅርብኝ ብሎ፣ አገሩ ጥሎ ጓዙን ጠቅልሎ ከተወለደበት ሀገር በጣም ርቆ በመሄድ ሰው ወደ ማይዞርበት፣ ድምፀ አራዊት ብቻ ወደሚሰማበት ደንና ዱር አራዊት ወደሚኖርበት በረሃ ገብቶ በጾምና በጸሎት በምህላ ተወስኖ ለብዙ ዓመታት ተቀመጠ።

በዘመኑ አደባና ምንዳቤ ሁል ጊዜ የሚረዳው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደሚጸልይበት ዋሻ መጥቶ የያዝከው የምናኔ ተግባር እግዚአብሔርን ያስደሰተና ጸሎትህንም ቅድመ እግዚአብሔር የደረሰ ስለሆነ የምናኔ ዘመንህ አብቅቶ አንተ ወደ አለህበት በዓት እግዚአብሔር የላከልህ ድንግል ልጃገረድ ትመጣለችና ምንም ነገር ሳትፈራና ሳትጠራጠር ቀርበህ አነጋግራት አለው። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዳለውም ያቺ እግዚአብሔር የላካት ድንግል ልጃገረድ ቅድስት መስቀል ክብራ ሳማ የተባለ ጎመን እየለቀመች እርሱ ወደ ተደበቀበት ዋሻ በድንገት መጣችና በትዕግሥትና በጥበብ በፍቅርና በአክብሮት በሰላም አነጋገር ከወላጆችዋ ጋር እንድታስተዋውቀው በትህትና ጠየቃት እርሷም የዋኅ ደግ ነበረችና ወደ ወላጆችዋ ወስዳ አስተዋወቀችው።

ገድለ ላሊበላ ከላይ የተጠቀሰውን የታሪክ ፍንጭ ቢያመለክትም ቅዱስ ላሊበላ በወንድሙ ቤተ መንግሥትና በእባቱ ልጅ ቅናትና ምቀኝነት መርዝ ጠጥቶ ከሞት ከተረፈ በኋላ የላስታና ዋግ ምድር አቋርጦ ወደ ትግራይ ገዳማት ሄዶ በምናኔ መኖር እንደ ጀመረና በዚህ ወቅት በትግራይ አካባቢ ከአለት ተፈልፍለው የታነጹትን አብያተ ክርስቲያናት እየዞረ እንደ ጎበኘ ከሚጠቁሙ ማስረጃዎች መካከል በደሰዓ ምንበርታ አጼ ገብረ መስቀል ካነጸው ድንቅ ቤተ ክርስቲያን ሚካኤል እምባ በተባለው ደብር የተገኘው አፈ ታሪክ እንደሚገልጸው ከሆነ ቅዱስ ላሊበላ በወጣትነት ዘመኑ መንፈሳዊ ትምህርት እየተማረ እንደ አደገና ቀጥሎም ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄድ ሲነሳ ከቅድስት መስቀል ክብራ ጋር ሆኖ በዚህ አካባቢ እንደ ሰነበተ ይነገራል። ይህም አፈ ታሪክ እንደዚሁ ወሬ ብቻ ሳይሆን የሚካኤል እምባ ውስጣዊ ግብረ ህንጻና የሦስቱ ቤተ መቅደሶች አስተናንጽና በልዩ ሐረግና ቅርጽ የተዋቡትን የቤተ መቅደሱ መዝጊያዎች ጥበባዊ አሠራር ቅዱስ ላሊበላ ለታቦታቱ ማስቀመጫ ካሰራቸው መናብርተ ታቦታት ሐረግና ቅርጽ ጋር በእጅጉን ይመሳሰላሉ።

ከዚህ ሌላ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ በረሃ ውስጥ ተደብቆ ሲጸልይ ድንግል ልጃገረድ የሆነች መስቀል ክብራ እንደ ተገናኘችውና ከቤተሰብዋም ጋር አስተዋውቅኝ እንደ አላት ጠቆም አድርጎ ያለፈ ቢሆንም ቦታው ግን የት

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ሆነ አልገለጸምና በዚህ ጉዳይ ላይ ቅዱስ ላሊበላ እየተዘዋወረ ከኖረባቸውና ከጎበኛቸው ገዳማት መካከል አንድ ደብረ ሊባኖስ ሐም የተባለ ገዳም ሳይሆን እንደማይቀር የሚጠቁሙ ጽሑፋዊ ማስረጃዎች ተገኝተዋል ይኸውም ገድለ ላሊበላ ቅድስት መስቀል ክብራ «በዓልተ ቢሃት» እያለ መጥቀሱ የቢሐት ተወላጅ ባላባት ማለት ስለሆነና ቅዱስ ላሊበላ ከነገሠ በኋላ በከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ያስቀመጣቸው የቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ባለ ስልጣናት ከቅድስት መስቀል ክብራ ቤተሰቦች የተውጣጡ ለመሆናቸው ቅዱስ ላሊበላና ቅድስት መስቀል ክብራ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሐም ሄደው ለገዳሙ መተዳደርያ ርስተ ጉልት መስጠቱን የሚያረጋግጠውና ራሱ ቅዱስ ላሊበላ በብራና ላይ አጽፎ ለገዳሙ የሰጠው ወንጌለ ዘወርቅ ዘደብረ ሊባኖስ ሐም እንዲህ ይላል:-

፩. «ወእንዘ ሀለዉ ክልኤሆሙ ኅቡረ ላሊበላ ንጉሥ ወብእሲቱ መስቀል ክብራ በእልተ ቢሐት ከመ ይኩኖሙ መድኃኒተ ነፍሶሙ በመንግሥተ ሰማያት ወለብእሲትየኒ ከመ ይደምራ ምስለ ቅዱሳት አንስት ምስለ ሳራ ወሰሎሜ ምስለ ሐና ወሶፍያ ወኢይዝክር ላቲ ኃጢአታ ወይደምስስ መጸሐፈ ጌጋያ አሜን ወአሜን። ለይኩን ለይኩን ወእንዘ ሀለዉ ዐበይተ ብሔና ቃለጳስ አብት፣ ጳጳስ አባ ጊዮርጊስ፣ ወኤጲስ ቆጶስ ኅረዮ፣ ዓቃቤ ሰዓተ መጣዕ ይርድአነ ክርስቶስ፣ ሊቀ ዲያቆናት ሳውን፣ ቀይሰ ገበዘ ጽዮን አብ ይኩን፣ መልሐዘ ይትባረክ፣ ቀስ ሐዪና ዘአዶናይ፣ ጸዋርሬ ናርጌ መአሰሬ ክርስቶስ ብነ፣ ጸሐፌ ላም ሰብሐት፣ ሐሰን ይዕቀበነ፣ ማእከለ ባሕር አስገደ፣ ዕቃ ጸንጸን ባራ ጽዮን፣ ዐቃቤ ደጌ ማሰረይ ይምሐረነ፣ ሊቀ አቃይታት ዘረውድም፣ እንዘ ሊቀ ኬናት ዘአመላይ፣ ወእንዘ ሊቀ ኀዳር ያሞ፣ ሊቀ መሰንቆ ወልደ ብጉናይ፣ ወከመዝ አጕለትኩ ዘአልቦ ግብረ መገብጋበ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዘወሀቦ ላሊበላ ዘንቱ ጕልተ ዘገፍዐ ውጉዘ ለይኩን አሜን ዘንተ ዘአጽሐፈ ዐቃቤ ሰዐተ መጣዕ ስመ ልደቱ ይርድአነ ክርስቶስ ስመ ምንኩስናሁ ጸጋ መጣዕ ለዘአጽሐፈ ወለዘ ጸሐፈ ፰ ስረዩ ወባርኩኑ አሜን።»

ቅዱስ ላሊበላና ቅድስት መስቀል ክብራ የተጠቀሱትን ንጉሣዊያን ቤተሰቦቻቸውና ከፍተኛ የመንግሥት ባለ ስልጣኖቻቸውን ይዘው ወደ ደብረ ሊባኖስ ሐም ድረስ በመሄድ ንጉሡ ርስተ ጉልት የሰጠው ራሱ ቅዱስ ላሊበላ ቅድስት ወቡርክት ብሎ የሰየማትን ባለቤቱ መስቀል ክብራን ለማስደሰት ሲል ከዛሬይቱ ዛላ አንበሳ ከተማ ወደ ምዕራብ ወረድ ብሎ የሚገኘው ሰፊ መንደር ቢኻት ማርያም ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስ ሐም የተባለውም ከመንደሩ ግዶ ባለው ቱራራስር ተጠግቶ የተመሠረተ ጥንታዊ ገዳም ነውና ቅድስት መስቀል ክብራ የተወለደችበት ሀገርና ለመጀመርያ ጊዜ ቅዱስ ላሊበላ በስደት ሄዶ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከዚች የተቀደሰች ባለቤቱ ጋር የተዋወቀባት መንደር ናት። ስለዚህ ገድለ ላሊበላ ብዙ ነገር ሳያትት በዓልተ ቢሀት ብሎ አልፎታል።

ቅዱስ ላሊበላ ለደብረ ሊባኖስ ሐም የሰጠው ርስተ ጉልት ወንጌል ዘወርቅ ዘደብረ ሊባኖስ ሐም ዳግመኛ ሲጠቅስ

«ዘወኅቦ ንጉሥ ገብረ መስቀል ለአባ መጣዕ ሰርኤ፣ ለጎ፣ እና፣ ሰያባ፣ ወንከብ፣ ስዓጋ፣ ማርያላ ገማዕ፣ ዜና ዙዶ፣ አዲ ሕልሙ፣ ጽዳዕ እሲራ፣ ለባሲር፣ ገዳሞሙ ለመነኮሳት ቤተ ሰማዕት እናንያ ወአዛርያ ወሚካኤል ፰ተ አዲ በጊኤን ፃዕዳ ብእቲ አዲ አይኬማ አዲ አይሰሑት ምድፋዕ ወልታ እእመ ረጌንያ ሰማዝ ጉናጉና ቀዳማዊ ጉልቱ ለአባ መጣዕ በሕይወቱ በአኮቴተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እነ ገብረ መስቀል ዘንተ ጉልተ ወሐብኩ አዳሚርየ ከመ የሐልፍ ኵሉ ብዕል ኵዳ ወይባ አወገር ፰ቱ አዳ ምስለ ምድሮሙ ሐፉሁ ወመሰኖሁ ደረቃ በሲሬ»

፪. አቀድም በረድኤተ እግዚአብሔር ጉልተ ዘንጉሥ ገብረ መስቀል ገለባ፣ አረገን፣ እፍ ቡራእ ፈለግ፣ ልገት፣ ሜሲት፣ ግዶም፣ ዕፅ፣ ማሬ አንበስት ቀርን እም ቢሐት በራቂት በድእዱዕ ሰብአቱ አዲ ሕዩን አለንታ። ሰብአቱ አዲ አዲ ሰራዊ ጉሕዊዖ ምስለ ምድሮሙ ቴደረር ስላ ልጋዕ ገበታ ሐቢ ዕንተላም ቅብዕ ዘወሐቦ ለአባ መጣዕ ንጉሥ ገብረ መስቀል ከመ ይኩኖ መርሐ ለመንግሥተ ሰማይ።

፫. «ምድረ ቴደረር በሐምሐም ቀላይ ወበናዕሉ ወበአረገን በክልኤቱ ፈለግ ወኅበ ጉልተ ለቅዱስ ሊባኖስ ንጉሥነ ገብረ መስቀል ከመ ይኩኖ መርሐ በመንግሥተ ሰማያት ዘወሀቦ ጕልተ ኢይትጌለጦ እስመ ብዙኅ ውእቱ»

፬. «በአኰቴተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወሀብኩ እነ ገብረ መስቀል በአሃም ፰። ገራህተ ለቤተ ክርስቲያን ወከመ ይግበሩ ተዝካር ለመጣዕ ከመ ይተወሀበኒ በመንግሥተ ሰማያት እመቦ ዘተኀየሎ ወዘተአገሎ ውጉዘ ለይኩን በአፈ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ»

ቅዱስ ላሊበላ በዚህ አካባቢ በነበረበት ወቅት የሰጠው ርስተ ጉልት ለተከበረው የደብረ ሊባኖስ ሐም ብቻ ሳይሆን ውድ ባለቤቱ መስቀል ክብራ ለተወለደችባት ደብረ ማርያም ቢሓትም መተዳደርያ ይሆናት ዘንድ ስምንት ማሳ እንደሰጣት ወንጌል ዘወርቅ ላይ ተጽፎ የተገኘው ማስረጃ ያረጋግጣል።

ቅዱስ ላሊበላ እስከ ዛሬ ድረስ ወደር ያልተገኘላቸው አሥሩን አብያተ ክርስቲያናት ከአለት ፈልፍሎ በማነጽ ከፈጸመ በኋላ በዚህ ቅዱስ ተግባር ላይ ያለ ምንም ማመንታት ጉልበታቸውን እውቀታቸውን ገንዘባቸውን አዋሕደው በግብረ ሕንጸት ሥራ ላይ ለተሳተፉ ሰዎች ሁሉ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የመጨረሻ ምስጋናውንና ጸሎቱን ምኞቱን ቅዱስ ላሊበላ ሲያቀርብ ላቸው በቤተ ጊዮርጊስ መንበረ ታቦት ላይ ተጽፎ የተገኘው ማስረጃ እንዲህ ይላል:-

፭. «ጸለየት ማርያም ወትቤ እግዚአብሔር እምላክነ ዘትንብር ውስተ ሰማይ ዘበፈቃድከ ፈነውኮ ለወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ ወኀደረ ውስተ ከርሥየ እስእለከ ወእስተበቍዓከ በእንተ ኵሎሙ ውሉደ ጥምቀት እለ ይገብሩ ተዝካርየ ወያቀርቡ መሥዋዕተ ስማዕ እግዚእ ጸሎቶሙ ወተወከፍ ስዕለቶሙ ወአዕትት እምኔሆሙ ዄዋዌ ወቀትለ፣ ወረሃበ፣ ወኀዘነ፣ ወምንዳቤ፣ በኀበ ያቀርቡ ሊተ ቍርባነ እድኅን ተግባሮሙ እምአንዜዋ፣ ወእም አንበጣ፣ እም ደጎቢያ ወእም በረድ፣ ወእም እስሐትያ፣ ወእም አናኩዕ፣ ወኵሎሙ ሕሙማን እለይጼውሁ ስምየ ይሕየው እምደዌሆሙ፣ ወእለኒ አኀዞሙ ጋኔን ወዶሪን ይትፌወሱ እምደዌሆሙ፣ ወእለኒ ይነግዱ ውስተ ባሕር በአሕማር እለ ይጼውዑ ስምየ አድኅኖሙ እም ማዕበለ መዋግደ ባሕር፣ ወእም ኃይለ ነፋሳት፣ ወእለኒ ሖሩ ርሑቀ ብሔረ ወይጼውዑ ስምየ ፍጡነ አግብኦሙ ውስተ ብሔሮሙ፣ ወገራውህ እለ ያወጽኡ ፍሬ መሥዋዕት በስምየ ይኩኑ ቡሩካነ ወአጸደ ወይን እንተ ያቄርቡ እምኔሃ ትኩን ቡርክት፣ ወይትባረኩ ኵሎሙ እለ ይገብሩ ተዝካርየ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፮. ማርያምም እንዲህ እያለች ጸለየች በሰማይ የምትኖር አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በፈቃድህ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስን ላክኸው በማኅፀኔም አደረ አሁንም የጥምቀት ልጆች ስለሆኑ ስለ ሁሉም እለምንሃለሁ፣ እማጸንሃለሁ፣ መታሰቢያየን ለሚያደርጉ፣ መሥዋዕትን ለሚያቀርቡ፣ አቤቱ ጸሎታቸውን ስማ ስለታቸውንም ተቀበል ከእነርሱም ምርኮን፣ ጦርነትን፣ ረሃብን፣ ኀዘንን መከንንትን አስወግድ፣ ለኔ ቍርባንን በሚያቀርቡበት ቦታ ሁሉ ሰብላቸውን ከአይጥ፣ ከአንበጣ፣ ከኩብኩባ፣ ከበረዶ፣ ከውርጭ፣ ከፈንጣ (ተምች) ጠብቅላቸው፣ በበሽታ የተያዙ ሕሙማንም ስሜን በሚጠሩበት ጊዜ ከደዌያቸው ይፈወሱ፣ በአጋንንትና በዶሪን የተያዙትንም ፈውስን ያግኙ፣ በመርከብ ሆነው በባሕር ላይ የሚነግዱም ስሜን ሲጠሩ ከባሕር ሞገድ ማዕበልና ከኃይለኛ ነፋስ አድናቸው፣ ወደ ሩቅ አገር የሄዱትንም ስሜን ሲጠሩ በፍጥነት ወደ አገራቸው መልሳቸው፣ መሥዋዕት የሚሆን ፍሬ የሚያስገኙ እርሻቸውም የተባረኩ ይሁኑ ከእርሷ መሥዋዕት የሚሆን ወይን የሚያቀርቡባት የወይን ቦታም የተባረከች ትሁን መታሰቢያየን የሚያደርጉ ሁሉ የተባረኩ ይሁኑ ለዘለዓለሙ አሜን።

ይህ ጸሎት ለሀገርና ለሕዝብ በሚውል መልኩ መርጦ በመንበረ ታቦት ላይ ጽፎ ማስቀመጡ ቅዱስ ላሊበላ በተግባርና በሕሊና ጸሎት ለሰው ልጆች ሁሉ ምን ያህል አሳቢ ተቆርቋሪ ቸር ርኅሩኅ፣ እንደ ነበር የሚያረጋግጥልን ጽሑፋዊ መረጃ ነው።

ቅዱስ ላሊበላ በዘመነ መንግሥቱ እነዚያን የመሰሉ የጥበብ ሥራዎች ሁሉ በዘመኑ ከነበሩት የሀገር መሪዎችና ጠበብቶች በሙሉ አስበልጦ አብያተ ክርስቲያናትንና ሌሎች ድንቅ የሆኑ ንዋያተ ቅድሳትን አሰርቶ ካደራጀ በኋላ በዘመኑ በሠራው ሥራ ሁሉ ሳይኩራራና ትዕቢት ሳያድርበት ራሱን ከሁሉ በታች ዝቅ በማድረግ ቸሩ ፈጣሪያችን ጸሎቱንና ድካሙን እንዲቀበልለት አሁንም በቤተ ጎልጎታ ከሚገኘው የታቦተ ሰንበተ ክርስቲያን መንበር ላይ በሰፊውና በመንበሩ ዙርያ በመላ ጽፎ ካስቀመጠው ምልጃ መካከል ስለ ራሱ እንዲህ ብሎ ጽፎአል፣

«ወእነሂ ተሰፈውየ ዘዚእከ ምሕረተ ስአልክዋ ለዛቲ ታቦት ወሰመይክዋ ሰንበተ ክርስቲያን ይኩን ምሕረትከ ህየ ኀበ ዘተኀድር ዛቲ ታቦት ወሰበ ያበውኡ ቍርባኖሙ ይኩን ኅሩየ ወሥሙረ በቅድሜከ፣ ለእለሂ ያበውኡ ዕጣነ፣ ወሥርናየ፣ ወወይነ፣ ወልብሰ፣ ወኵሉ ዘይደሉ ተሰፈዎሙ ምሕረተ ዚእከ ጸዊዖሙ ስመከ ኀበ ዘተኀድር ዛቲ ታቦት ለለሰሙን እንተ ዕሥዮሙ ዕሤተ ሠናየ በመንግሥትከ።»

ወሊተኒ ለገብርከ ኀጥዕ ላሊበላ ኢታስተኃፍረኒ እምተስፋየ ዘተሰፈውኩከ ኢታማስን ፃማየ ዘፃመውኩ በእንቲአከ ወኢትረስዖ ከመ ወኢያምንት በከመ እንተ ትቤ ኢታስአ ዕብዋ ለነኒስ መሬትከሙ እስመ ሠምረ አቡክሙ ረሲ ሊተ እግዚእ ህየንተ ፃማየ ኀደጥ ብዙኅ በኀቤከ፣ ተወከፍ መባዕየ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ ኖኅ፣ ተወከፍ መባዕየ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አቤል ጻድቅ፣ ተወከፍ መባዕየ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አብርሃም፣ ይስሐቅ ወያዕቆብ፣ ተወከፍ መባዕየ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አሮን ወሙሴ፣ ሊተ ለገብርከ ላሊበላ እመ ታቀውም አባግዓ በየማንከ ወአጣሌ በፀጋምከ ምስለ እለ በየማንከ ሆልቁኒ ሊተ ለገብርከ ላሊበላ ውስተ ሰንበተ ሰንበታቲከ፣ አብእኒ ውስተ ዕረፍተ ክብር ወሕይወት ለገብርከ ላሊበላ።

ለከ ስብሐት ወአኰቴት፣ ወለከ ሥልጣን፣ ወለከ መንግሥት፣ ወለከ ምሕረት፣ በሰማይ ወበምድር ብውህ ለከትቀትል ወታሐዩ፣ ወከመ ታንዲ ወታብዕል፣ ወአልቦ ዘይትካፈለከ ውስተ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም ዓለም አሜን።

«እኔም የአንተን ምሕረት ተስፋ በማድረግ ይህችን ታቦት ሰንበተ ክርስቲያን ብየ ሰየምኳት ይህች ታቦት ባለችበት በዚያ ምሕረትህ ይብዛ ቍርባንም ሲያደርጉ በፊትህ ያማረና የተወደደ ይሁን ምሕረትህን ተስፋ አድርገውና ስምህን ጠርተው በየሳምንቱ ዕጣን፣ ስንዴ፣ ወይን፣ ልብስ፣ ማንኛውም የሚያስፈልገውን ሁሉ ለሚያቀርቡ አንተ በመንግሥትህ ዕጥፍ ድርብ ዋጋ ስጣቸው።

ኃጥዕና በደለኛ ለሆንኩ አገልጋይህ ላሊበላም አስበኝ፣ ተስፋ ካደረግሁብህ ሁሉ ከንቱ ብላሽም አታድርግብኝ አንተ «ታናሽ መንጋ የሆንችው ምእመን አታስቸግርዋት አባታችሁ ወዷልና» ብለህ እንደ ተናገርህ ጥቂት የሆነው ድካሜን ባንተ ዘንድ ብዙ አድርግልኝ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ የአሮንና የሙሴን መሥዋዕት እንደ ተቀበልከ የኔን የባሪያህን መባ ተቀበልልኝ፣ በጎችን በቀኝህ ፍየሎችንም በግራህ ባቆምህ ጊዜ እኔን አገልጋይህ ላሊበላን በቀኝህ በኩል ካሉት ጋራ ቁጠረኝ የክብርና የሕይወት ዕረፍት ወደሚገኝባት ሰንበትም አግባኝ ምስጋና፣ ስልጣን፣ መንግሥትና ምሕረት ያንተ ነው።

ትገድልና ታድን ዘንድ፣ ታበለጽግና ታደኸይ ዘንድ፣ በሰማይና በምድር ስልጣን ያንተ ብቻ ነው ከዓለም በፊት ጀምሮ እስከ ኅልቀተ ዓለም ድረስ በስልጣንህ ውስጥ የሚገባ የለም። አሜን።

በማለት ፍጹም ትሁት ቸርና ርኅሩኅ በሆነው ሕሊናው ለራሱና ለወገኖቹ ሊደረግ የሚገባውን ቸርነት ሁሉ በመመኘት ፈጣሪውን በሚገባ ማልዶአል።

ቅዱስ ላሊበላ በዘመኑ ከነበሩት ቤተሰቦቹና ወዳጆቹ ሁሉ አስበልጦ ይወድና ያከብራት ለነበረችው ቅድስት ባለቤቱ መስቀል ክብራ ከላስታ ወደ ትጋራይ ተጉዞ ባለቤቱ ለተወለደችባት ደብርና በሥርዓት መንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ ለነበሩት የደብረ ሊባኖስ ሐም ገዳም መነኮሳትና ለደብረ ማርያም ቢሓት በርከት ያለ ርስተ ጉልትና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳትን ከመስጠቱም ሌላ አሁን በዘመነ መንግሥቱ ሁሉ ራስዋንና ምሁራን ወገኖችዋን አስተባብራ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ላደረገችለት ቅድስት መስቀል ክብራ ምድራዊ ክብር ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ክብርም ከእርሱ ጋር እግዚአብሔር እንዲያድላት በማሰብ አሁንም በቤተ ጊዮርጊስ ቤተ መቅደስ ለታቦተ ቅድስት ድንግል ማርያም ባሰራው መንበረ ታቦት ላይ ጽፎ ባስቀመጠው ምልጃ ላይ እንዲህ ይላል፣

፯. «ማርያም ወላዲተ አምላክ እመ ሰማዕት ወእኅተ መላእክት እንተ ሐሠሥዋ ወዖድዋ ነቢያት ዘብዙኅ ውዳሴኪ እስመ ኪያኪ ሠምረ ወለኪ ይደሉ ዘእምኵሎሙ ቅዱሳን ትሰአሊ ለነ እ ምልዕተ ጸጋ አንቲ ተዓብዪ እምሊቃነ ጳጳሳት ወትከብሪ እምነቢያት ብኪ ግርማ ራዕይ ዘየዓቢ እምግርማ ሱራፌል ወኪሩቤል አንቲ በአማን ምክህ ዘመድነ ወሰአሊት ሕይወተ ለነፍሳቲነ ሰአሊ ለነ ኀበ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ያጽንዓነ በርትዕት ሃይማኖት ውስተ አሚነ ዚአሁ ይጸግወነ ሣህሎ ወምሕረቶ ይሥረይ ኃጢአትነ በብዙኃ ምሕረቱ ለገብርኪ ላሊበላ ወአመትኪ መስቀል ክብራ»

፰. አምላክን የወለድሽ፣ የሰማዕታት እናት የመላእክት እህት ነቢያት በትን ቢታቸው የፈለጉሽ (የተናገሩልሽ) ማርያም ሆይ ምስጋናሽ ብዙ ነው እግዚአብሔር አንቺን ወዷልና ጸጋን የተመላሽ ሆይ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ትለምኚልን ዘንድ ላንቺ ይገባል አንቺ ከሊቃነ ጳጳሳት ትበልጪያለሽ፣ ከነቢያትም ይልቅ ትከብሪያለሽና ከሱራፌልና ከኪሩቤል የሚበልጥ የመወደድ ግርማ አለሽ አንቺ በእውነት የባሕሪያችን መመኪያ ነሽ ለሰውነታችንም ሕይወትን ትለምኚያለሽ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ለምኚልን እርሱን በማመን በቀናች ሃይማኖት ያጸናን ዘንድ ይቅርታውንና ምሕረቱን ይሰጠን ዘንድ ለባሪያሽ ላሊበላና ገረድሽ መስቀል ክብራም በቸርነቱ ብዛት ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ!!

በማለት ለውድ ባለቤቱ ተገቢው ክብርና ሞገስ ሰጥቶአታል ይህንን የመሰለ የቅዱስ ላሊበላ ተግባራት እንደ ሌሎቹ ትምክህተኛ ነገሥታት በዘመነ መንግሥታቸው የተሠራውን ሥራ ሁሉ ከንግሥታት ባለቤቶቻቸው ጋር እየተመካከሩ የሠሩት መሆኑን በመዘንጋት በታሪካቸው ውስጥ ግን የራሳቸው ስም ብቻ ከመጠን በላይ አግንኖ በማውጣት የፈጸሙት የነበረ ተግባር በቅዱስ ላሊበላ ዘንድ ቦታ አልተሰጠውም።

ቅዱስ ላሊበላ ባለቤቱ ቅድስት መስቀል ክብራን ብቻ መውደድና ማክበር ሳይሆን ከቤተ ሰቦችዋ መካከል ምሁራትንና የጥበብ ሰዎቹን መርጦ በስልጣነ መንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ሰጥቶ ስልጣኑን በማጋራት ከሾማቸው ሰዎች መካከል አንዱ የቅርብ አማካሪውና በስልጣነ መንግሥቱ ውስጥ አድራጊ ፈጣሪ የሆነውን የእቃቤ ሰዓት ስልጣን ለቅድስት መስቀል ክብራ ታላቅ ወንድም የሆነው አባ ይርድአነ ክርስቶስ ወይም ስመ ምንኵስናሁ አባ ጸጋ መጣዕ የተባለውን ሰው እቃቤ ሰዓትና ጸሐፌ ትእዛዝ አድርጎ በመሾም በቅድስት መስቀል ክብራና በቤተሰቦችዋ የነበረው ሙሉ እምነት በተግባር አረጋግጦአል።

እቃቤ ሰዓት አባ ይርድአነ ክርስቶስ ወይም አባ ጸጋ መጣዕ የሥነ ጽሑፍ የሥዕልና የቅርጻ ቅርጽ ጥበብ ባለሞያ ስለ ነበር ቅዱስ ላሊበላ ለመጀመርያ ጊዜ ያነፃትን ቤተ ማርያምን የሳለና በልዩ ልዩ ሐረጋትና ቅርጻ ቅርጽ ያስዋበ የሥነ ጥበብ ሰው ስለ ነበር ቅድስት መስቀል ክብራ በዘመንዋ ታላቅ ወንድምዋ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ እንዲሆን ከፍተኛ ፍላጎት ስለ ነበራት በዘመኑ ለነበረው ግብጻዊ ጳጳስ አባ ሚካኤል ወንድሜን ጳጳስ አድርገህ ሹምልኝ ብለው ኢትዮጵያዊያን ጳጳስ እንዳይሆኑ በሲኖዶስ የተከለከለ ነው ስለ አላት በከፍተኛ ደረጃ ተጣልተው እንደ ነበር በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የተገኘው ታሪክ በሰፊው ይገልጻል። ከዚህ የተነሳም ግብጻዊው ጳጳስ መስቀል ክብራ ታስገድለኛለች ብሎ በመፍራት ከኢትዮጵያ ጠፍቶ እንደሄደና እርሱ በሄደ በሁለተኛው ዓመቱ ቤተ ማርያምን የሳለው አባ ይርድአነ ክርስቶስ ወይም ጸጋ ሊባኖስ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ግብጻዊያን መነኮሳት በሪፖርታቸው ገልጸዋል። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

*ይህ ዓምድ በሰው ልጅ ሥነ ምግባርና በሌች አያ ቪ (ሌድስ) ዙርያ ጥናታዊ ትምህርት ይቀርብበታል።*

## የ፳ኛው ክፍለ ዘመን ሰውና ጥያቄው

ከዶ/ር የማነ ገ/ማርያም

ስለ ፳ኛው ክፍለ ዘመን ሰው ጥቂት ልናገር እወዳለሁ። ያን ሳደርግ ግን ስለ ምግባሩ በጎነት ወይም ክፋት ለመናገር አይደለም። የ፳ኛው ክፍለ ዘመን ሰው በምግባሩ በኩል ከዚህ በፊት ከነበሩት ክፍለ ዘመናት ሰው ብዙም የሚለይበት ነገር የለውም። በምግባሩ ከዚህ በፊት ከነበረው ሰው ብዙም አይለይ እንጂ በንቃተ ሕሊና ዕድገት በኩል ብዙ ይለያል። የ፳ኛው ክፍለ ዘመን ሰው ወይም ያለንበት ዘመን ሰው ከዚህ በፊት ከነበረው ሰው በአስተሳሰብ የተሻለ ነው። ነገሮችን በጥሞና የመገምገምና ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው። ማንም ሰው ተነሥቶ ስለ አንድ የሆነ ነገር የነገረውን ሐሳብ በጭፍን አይቀበልም፤ የሚነገረውን ነገር እውነተኛነትና ሐሰተኛነት ለመለየት ለምን ወይም እንዴት በማለት ነገሩን ከብዙ አቅጣጫ ይገመግማል፤ የሚነገሩትን ነገር በተጨባጭ ማየት ይፈልጋል፤ ዘመኑም የሳይንስ ዘመን ስለ ሆነ በተለይም የተማረው ወጣት ትውልድ በዚሁ በሳይንስ አእምሮው ስለ ተሞረደ ሁሉንም ነገር በሳይንሳዊ መንገድ ተመልክቶ ራሱ አይቶና አረጋግጦ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን ረጋ ብሎ አስቦ ውሳኔ ይሰጥበታል። እንጂ እንደዚያ ተብሎ ተነገረ ኛል በሚል ሐሳብ ብቻ በየዋህነት የማንንም ሰው ቃል በጁ ብሎ አይቀበልም።

በተለይም ማን ማን እንደሆነ የሚፈርደው ከሚናገረው ሳይሆን ከሚያደርገው ነው። የመንፈሳዊያን አባቶች ስብከትም ዛሬ በመላው ዓለም በዘመኑ ሰው በተለይም በወጣቱ ትውልድ ተደማጭነት ለማግኘት ችግር እየገጠመው ያለው ሥራቸውና ቃላቸው ሳይጣጣም እየቀረ በመምጣቱ ምክንያት ነው። የሚናገሩት ቃል ጥሩም እንኳ ሁኖ ሳለ፤ የሚናገሩት ቃል የእግዚአብሔርም ቃል እንኳ ሁኖ ሳለ ልቡን ሰጥቶ ሊሰማቸውና የሚሉትን ተግባራዊ ለማድረግ እያመነታ ነው። በእርግጥ በጎ ምግባር፤ ክርስቲያናዊ ሕይወት ያላቸው መንፈሳውያን አባቶች ዛሬ ጨርሶ የሉም ማለቴ አይደለም መኖሩን አሉ። ነገር ግን እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው የሚበዙት እንደዚያ አይደሉም። ስለዚህም ተደማጭነታቸው በተለይም በተማረው ወጣት ትውልድ እየቀነሰ መጥቷል። ሊያስተምሩ ገና ከመድረክ ላይ ብቅ ሲሉ «ዛሬ ደግሞ ምን ሊቦተልኩ ነው?» «ዛሬ ደግሞ ምን ሊዋሹ ነው?» በማለት ስብከታቸውን በጥርጣሬ እየተመለከተው ነው። ከዚሁ ጋር የሚሄድ የዛሬውን ዘመን ወጣቱን ትውልድ የሚመለከት ነገሩንም እያባባሰው የመጣ አንድ ቁም ነገር አለ። ያሁኑ ወጣት ትውልድ በተለይም የተማረው ወጣት ትውልድ ሁል ጊዜ ሲነገር እንጂ ሲፈጸም የሚያየው ብዙ ነገር ስለሌለ የሚነገረውን ለመስማት እየሰለቸው መጥቷል። በዚህም ምክንያት ትዕግሥቱ እየተሟጠጠ ስለሆነ ይናደዳል፤ ይበሳጫል። በብስጭቱም ምክንያት አዋቂዎችን ደስ የማያሰኛቸው ቃል ይናገራል፤ ይዳፈራቸዋልም። አዋቂዎችም ይህ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅና መፍትሄ ለማግኘት በመሞከር ፈንታ በቁጣ «የዘመኑ ልጆች» «የ፳ኛው ሺህ ልጆች» «የተረገመ ትውልድ» በማለት ነገሩን ይበልጥ አባብሰውታል።

በዚህም ምክንያት እንደዚያ እየተባለ የሚወረፈው ወጣት ትውልድ በዕድሜ ከእርሱ ጋር የሚቀራረበው በዕድሜ ጥቂት ጠና ያለው ምሁሩ ክፍል ጭምር እርሱም በበኩሉ አጸፌታውን እየመለሰ ነው። ወጣቱን ትውልድ እንደዚያ ብሎ መዝለፍና ለክፉ መልስ መጋበዝ ባልተገባ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ በወጣቱ ላይ የሚሰነዘረው የዘለፋ ቃል ፍትሐዊነት የጐደለው አነጋገር በመሆኑ ምክንያት ወጣቶችን ይብሱኑ ቁጡዎችና ተናጋሪዎች እያደረጋቸው ነው። ልናቀርባቸው ሲገባን ሳለ ይባሱኑ እያራቅናቸው ነን። ይህም ትልቅ ኪሣራ ነው ምክንያቱም ወጣቱን ያላቀፈና በወጣቱ ያልታቀፈ ፖለቲካም ሆነ ሃይማኖት ስንኩል ሁኖ ይቀራልና ነው። ወጣት ነገ በእኛ በዛሬዎቹ ሽማግሌዎች የሚተካ ትውልድ በመሆኑ ምክንያት ያለ እርሱ ሁሉም ነገር ከንቱ ሁኖ ይቀራል። ያለ ወጣቱ ፖለቲካው ብቻ ሳይሆን ሃይማኖቱም ጭምር ክፉ ዕጣ ይጠብቀዋል። ሃይማኖትን ብቻ እንኳ ለይተን ብንወስድ ወጣት የራቀው ሃይማኖት ተስፋ የለውም። ለምሳሌ ወጣቱ ጭልጥ ብሎ የያዘውን ሃይማኖት ትቶ ወደ ሌላ ሃይማኖት እንኳ ቢሄድ ለቅቆ በሄደበት ሃይማኖት ላይ ወደ ፊት የሚደርሰውን ችግር መለስ ብሎ በሐሳብ መመልከት ይበቃል። በወቅቱ ያሉት ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ሲያልፉ የሚተካቸው ትውልድ ይጠፋል ምክንያቱም ለቅቆ ሄዷልና።

ሰነፍ እረኛ በጎቹን ርቀው ሳይሄዱ በትክቅርቡ መመለስ ሲገባው ሳለ ከፉቅ ይመልሳል ይባላል። ነገር ግን ርቀው ከሄዱ ሊመልሳቸው ቀርቶ ድምፁንም ለይተው አይሰሙትም ምክንያቱም ርቀው (እንደኛውን ርቀው) ሂደዋልና። ሰው ከሌለ የሃይማኖት ትምህርትስ የምናስተምረው ማንን ሊሆን ነው? — ሰው ከሌለ ማንን ነው ወደ ክርስቶስ የምናመጣው? — መንፈሳውያን አባቶችስ ማንን አስተምረው ነው በመንፈሳዊ አባትነታቸው የሚቀመጡትና ለሥራቸው ደሞዝ ወይም ሌላ ጥቅማ ጥቅም የሚያገኙት? — ተማሪዎች ሳይኖሩ የመምህራን ምደባ ትርጉም ይኖረዋል? — አይኖረውም። ተማሪዎች ከሌሉ መምህራንም አያስፈልጉም። ስለዚህ ያለ ተማሪዎች የመምህራን ምደባ ጥያቄም አይነሣም ምክንያቱም አስተማሪ የሚያስፈልገውና የሚፈለገው ተማሪ ሲኖር ነውና ነው። ያለ ወጣት መቅረትም የዛሬዎቹን ሽማግ



ሌዎችና አሮጊቶች የሚተካቸው ትውልድ ማጣት ማለት ስለሆነ ለራሳቸው ለመንፈሳውያን አባቶችም መዘዙ ከፍተኛ ይሆናል። የዛሬዎቹ አረጋውያን ሲያልፉ የሚተካቸው ወጣት ትውልድ ከሌለ ነገ የምናስተምራቸው ምዕመናን አይኖሩንም። ያለ ምዕመናን ደግሞ ዳቦ አይገኝም። እንኳንስ በቀን ሦስትና አራት ጊዜ በልቶ ጠግቦ ማደር ቀርቶ ለአንዱም ይቸግራል። ስለዚህ ወጣቱን ትውልድ የሚያስከፋና የሚያሸሽ ሥራ መፈጸም ለምንም ለማንም አይበጅም። የሚበጀውስ ወጣቱን ይዘን መጓዝ እንጂ ያለ ወጣቱ የትም አንደርስም። ለወጣቱ ቁጡነትና ትብጥብጥነት ምክንያት እየሆንን ያለነው እኛው ራሳችን አዋቂዎቹ መሆናችንን ልናስተውለው ይገባል። ወጣቱ ትውልድ በአዋቂዎች ላይ አንዳንድ ጉድለት እያየ እንጂ ምንም ጉድለት ሳያይ እንዲሁ ከመሬት ተነሥቶ አይተችም፤ ያለ ምክንያት እንዲሁ አይቈጣም።

ቀደም ሲል ስናገረው ወደ ነበረው ሐሳብ ልመለስና የምናስተምረው በጎ ትምህርትም ቢሆን፤ የምናስተምረው የእግዚአብሔርንም ቃል ቢሆን የምናስተምረውን ቃል ስናስተምር ራሳችንም ጭምር ልንፈጽመው ያስፈልጋል። ያለበለዚያ ትምህርታችን ተሰሚነት አይኖረውም። ለሰሚዎቻችን ጠቃሚዎች መሆናችን ቀርቶ መሰናክሎች እንሆናለን። የፊተኞቹ ክፍለ ዘመናት ሰው ሰባኪው ማንም ይሁን ማን የእግዚአብሔርን ቃል እስከሰበከው ድረስ ቃሉን በጥሞና ሰምቶ ለመፈጸም እያመነታም ነበር። ስለ ሰባኪው ማንነት ብዙም ግድ አልነበረውም። ዛሬ ግን የሰው አስተሳሰብ ተለውጧል። የዛሬው ሰው ጉዳዩን ከቃሉ ብቻ ሳይሆን ከራሱ ከሰውየውም ጭምር ነው የሚል ነው። ራሱ ሰውየው ለሚናገረው ቃል የማይመጥን ከሆነ፤ የሚናገረውን ራሱ የማይፈጽመው ከሆነ አይናገረን፤ አርፎ ይቀመጥ የሚል ትውልድ ነው። በዓለም ላይ ያሉ ሃይማኖቶች ሁሉ ዛሬ ትምህርታቸው ተቀባይነቱ እየቀነሰ የመጣው መንፈሳውያን አባቶች ሕይወታቸው ከሚያስተምሩት ቃል ጋር አብሮ ስለማይሄድ ነው። ይሁንና ከራሱ ከዘመኑም ሰው ስሕተት አለ። ሰባክያኑ ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት በአኗኗራቸው ጉድለት ቢኖርባቸውም የሚናገሩት ቃል የራሱ የእግዚአብሔር ቃል እስከሆነ ድረስ ልንፈጽመው ይገባል። ይህም ራሱ ክርስቶስ በራሱ ዘመን የነበሩትን ጻፎችንና ፈሪሳውያንን አስምልክቶ ትምህርቱን ለመስማት ለተሰበሰበው ሕዝብና ለደቀ መዛሙርቱ ያስገነዘበው ቃል ነው። የቃሉ መንፈስ ዛሬም ጭምር እየተደገመ ነው።

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው — ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስለዚህ ያዘዙዋችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፤ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ። ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም (ማቴ.፳፫፥፩–፬)

ሰባክያኑ የሚናገሩትን ቃል ራሳቸው አይፈጽሙትም ተብሎ የሚናገሩትን ቃል ከመፈጸም ወደ ኋላ ማለት የማያዋጣ ሰበብ ይሆናል። የማንም ሰው ሥራ በጎም ይሁን ክፉ እኛን አያጸድቀንም አያስኰንነንምም። ሁሉም የሚጠየቀው ስለ ራሱ ሥራ ነው። ስለዚህ የራስን ግዴታ መወጣት ያስፈልጋል እንጂ እነገሌ መቼ ግዴታቸውን ተወጡ? በሚል ሐሳብ የራስን ግዴታ አለመወጣት ከቅጣት አያድንም። ከላይ የተጠቀሰው የክርስቶስ ቃልም መንፈስ ይኸው ነው። ከዚህ አንጻር የዘመናችን ወጣት ትውልድም እሮሮና እምቢታ ተጋንኗል እላለሁ። ይህን ስል ግን የሚናገሩትን የማይፈጽሙትን ሰባክያን ድረጊት ምንም አይደለም ለማለትና ስለ እነርሱ ለመከራከር አይደለም። ድርጊታቸው በጎ እንዳልሆነ ይሰማኛል። ስለዚህ እኔም እወገዘዋለሁ። ነገር ግን የሚወገዘው ድርጊታቸው ግዴታችንን ከመወጣት ወደ ኋላ ሊያደርገን አይገባም ነው የምለው።

መንፈሳውያን አባቶች በየትም ሀገር እንደሚያስተምሩት በጎ ትምህርት ራሳቸውም ደህና ሕይወት የርኅራኄ ሥራ ቢኖራቸው ኑሮ ግን በእርግጥ ትምህርታቸውም ይበልጥ ይሰምርላቸው ነበር። እንኳንስ የሚሰብኩት የራሳቸው ሃይማኖት ተከታዮች ቀርተው የሌላ ሃይማኖት ተከታዮችም እንኳ አግድመው ሲያልፉ ቃላቸውን ቢሰሙ ወደ እነርሱ ይሳቡ ነበር። ዝም ብለው አያልፏቸውም ነበር። መንፈሳውያን አባቶች ርኅሩኆች ሆነው ያገኙዋትን ከመንፈሳውያን ልጆቻቸው ጋር ተቃም ሰው የሚያድሩ፤ ስለ ልጆቻቸው ሲሉ ሳያጡ የሚያጡ አባቶች፤ ስለ መንፈሳውያን ልጆቻቸው ጥቅም ደፍረው የሚከራከሩ ሐቀኛች አባቶች ዛሬም ቢሆን የእነርሱን ቃል የማይሰማ ምክራቸውን የማይከተል አንድም አማኝ አይኖርም። ሊናገሩ ሊሰብኩ ገና ከመድረክ ላይ ብቅ ሲሉ ሁሉም እንባ ባቀረረ ዓይኑ ይቀበላቸዋል። ባይናገሩም እንኳ በአካል መታየታቸው ለምእመናኖቻቸው በቂ ነው። ለበጐ ሥራ መልካም አርአያ የሆኑ መንፈሳውያን አባቶች ካሉ ብዙዎች ምእመናን ከእግራቸው ሥር ይነጠፋሉ። እግሮቻቸውንም ተጐንብሰው ወይም ተንበርክከው ይስሙታል። ያደለውም እጃቸውን ካገኘው ደጋግሞ ይስመዋል። የሚሄዱበትንና የሚቆሙበትን አፈር ሳይቀር የሚሳለመውና ተጐንብሶ የሚስመው አማኝ ጥቂት አይሆንም። ታዲያ እንዲህ ያሉ የተወደዱና የተከበሩ መንፈሳውያን አባቶች ተናግረው ቃላቸው የት ይወድቃል? እነርሱ ትምህርት እንደሚሰጡ ሰምቶ ትምህርታቸውን ለማዳመጥ ወደሚናገሩበት ቦታ የማይመጣስ ማን ነው? በእውነት እንዲህ ዓይነት መንፈሳውያን አባቶች ያሉዋቸው ምእምናን እነርሱን የሚያዩባቸውና የሚናገሩትን ቃል የሚሰሙባቸው ዓይኖቻቸውን ጆሮዎቻቸው የታደሉ ናቸው። ነገር ግን ዛሬ በብዙዎቹ መንፈሳውያን አባቶች ላይ ያለው ሐቅ ከዚህ የተለየ ነው። ለራስ ብቻ ማሰብ፤ እኔ ብቻ አይጉደልብኝ የሚለው የራስ ወዳድነት ስሜት፤ ስለ ሌላው ሰው ግዴለሽነት ብዙዎቹን መንፈሳውያን አባቶች ያጠቃቸዋል። ይህ ግን አብሮ የሚያኖር ስሜትና አስተሳሰብ አይደለም።

ሰው ለወንድሙ ግድ እንዲኖረው የሚያስፈልገው ሃይማኖቱ ያን እንዲያደርግ ስለሚጠይቀው ብቻ አይደለም። የሂዩማኒዝምን መንፈስ ተግባራዊ ለማድረግም ብቻ አይደለም። አብሮ ለመኖርም ጭምር የሚያስፈልግ ነው። ሃይማኖት ኖረህም አልኖረህም ጐረቤትህ እየተራበ አንተ ለዘለቄታው በሰላም እንደማትኖር ልታውቀው ይገባል። የተራበ ጎረቤት ጥሩ ጎረቤት አይሆንም። ጐረቤቱ እየራበው እያየ ለራሱ ብቻ የሚያስብ አንድ ቀን በራሱ ላይ መቅሠፍት ያመጣል። መቅሰፍቱም ከሰማይ ሳይሆን ከራሱ ከጐረቤቱ እጅ ይመጣበታል። ስለዚህ ለዘለቄታው በሰላም ለመኖር እንድትችል ጐረቤትህም ከአንተው ጋር አብሮ ይብላ። እንዳንተው በልቶ ካደረ በአንተ ላይ ለመሸመቅ ምክንያት አይኖረውም። ምክንያቱም አንተ ያለህን እሱም አለውና። ስለዚህም አርቀው አስተዋዮች የሆኑ ሰዎች የሚኖሩት ለሌላውም ሰው ጭምር እያሰቡ ነው። የዚህች ዓለም ነዋሪዎች ሁሉ የአንዲት ጀልባ ተሣፋሪዎች ናቸው። በጀልባዋ ላይ ሁከት ቢነሣ ጀልባዋ ትገለበጣለች። ያን ጊዜ ሁሉም አብረው ወደ ባህር ይሰጥማሉ። ስለዚህም ስለ ጀልባዋ ደህንነት ሁሉም ተሳፋሪ በአንድነት የበኩሉን መወጣት አለበት።

ይቀጥላል

www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከቀሲስ በላይ መኮንን
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ
የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊትና ጥንታዊት የሆነች ከ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ፲፱፻፷ዎቹ አጋማሽ ብሔራዊት የነበረች ከአገሪቱ ሕዝብ ግማሹ ምእመናኗ የሆኑ ከ፬፻ ሺህ (አራት መቶ ሺ) አገልጋይ ካህናት እና ከ፴፪ ሺህ ፭፻፴፯ (ሰላሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት) በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ያሏት ከዚህም ውስጥ ከ፩ሺ በላይ ጥንታዊያን ገዳማት ያሏት ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ናት።

እንደ ጥንታዊነቷ ልማት በቤተ ክርስቲያንም ረዥም ታሪክ አለው ጥንታዊያን ከድንጋይ የተፈለፈሉ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት፣ የብራና ሥራና ጽሑፍ ጥበብ የዕውቀት ምንጭ የሆኑ የአብነት ት/ቤቶች፣ ጥንታዊያን ሐውልቶችና ቅርፃ ቅርፆች በቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ በልማት ከሚፈረጁ ቀደምት ሥራዎች ጥቂቶች ናቸው። በዘመናችንም ቤተ ክርስቲያን ሲሶ መሬት በነበራት ጊዜ የእርሻ ልማትና በከተማችን ዕውቅ ሕንፃዎች የተሠሩት በቤተ ክርስቲያናችን ነው።

ሆኖም ግን የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር መሠረት በማድረግ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ምእመናንን በማሳታፍ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲጠናከር አጋዥ የሆኑ የልማት ሥራዎች በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በእኩል አስተሳሰብ እየተከናወኑ እንዳልሆነ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የአንዳንድ ገዳማት በጥንቃቄ አለመያዝ፣ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት መዘጋት ወይም አገልግሎት መስጠት ማቆም እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል።

ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ውስጥ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ገዳማትና አድባራት አገልግሎታቸውን በአግባቡ ለመስጠት ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ እንደሚችሉ ይገመታል።

በመሆኑም በዚህ አጭር ጽሑፍ ልማት በቤተ ክርስቲያን ምን ማለት እንደሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ለሚካሄዱ ልማቶች የገንዘብ ምንጫቸው ከየት እንደሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ልማት ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች፣ ልማትን በቤተ ክርስቲያን ለማፋጠን መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው፣ እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አካል በልማት ያለው ድርሻ ምንድን ነው በሚሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ለንባብ በሚያመች መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል።

## I. ልማት በቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

በቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን ለመፈጸምና ለአማንያንም ሆነ ለኢአማኒያን ማኅበራዊ አገልግሎትን ለመስጠት የምታካሂደው የልማት እንቅስቃሴ በሙሉ በዚህ ርእስ ሥር ይካተታል።

በአጠቃላይ ሲታይ የቤተ ክርስቲያን ልማት በአምስት ዘርፍ ተከፍሎ መታየት ይችላል።

፩. ለመንፈሳዊ አገልግሎት:- የሚውሉ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማሠራት፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችን እና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት፣ ቅርሳ ቅርስ ጥበቃን ማጠናከር።

፪. የሰው ኃይል ልማት:- ካህናትና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ማሠልጠን የሥልጠና ዓይነቶች የሙያ (ዕደ ጥበብ) ሥልጠና የሥራ አመራርና አስተዳደር ሥልጠና፣ መንፈሳዊ አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድ የሚደረጉ ሥልጠናዎችን ያካትታል።

ለምሳሌ:- መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ ሰዋሰወ ብርሃን፣ ጎፋ ዕደ ጥበባት፣ ሰበታ ዕደ ጥበብ

፫. ለገቢ ማስገኛ የሚቋቋም ልማት:- አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለአገልጋዮች መተዳደሪያ ወይም በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላትን የሐዋርያዊ ተልዕኮ ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስችል ገቢ የሚያስገኙ ትርፋማ የሥራ መስኮችን ያጠቃልላል።

ለምሳሌ:- ወፍጮ፣ ሸመና፣ ዳቦ ቤት፣ ዘይት መጭመቂያ፣ የሚከራይ ቤት፣ አትክልትና ፍራፍሬ ቤት፣ ንብ ርባታ፣ ከብት ማድለብ፣ የወተት ሀብት ልማት፣ ትምህርት ቤት መክፈት ወዘተ...

፬. የበጎ አድራጎት ልማት:- የዚህ ዓይነቱ ልማት በማኅበረሰቡ ውስጥ የተቸገረውንና ደሀው የኅብረተሰብ ክፍል ማለትም መጠለያና ምግብ ላጡ ለአረጋውያንና ለሕፃናት የበጎ አድራጎት ሥራን ያጠቃልላል።

ለምሳሌ:- የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አረጋውያን መረጃ በጎ አድራጎት ማኅበር፣ የአዲስ ዓለም ቅድስተ ማርያም አረጋውያን መርጃ ወዘተ.

፭. ለአካባቢው ኅብረተሰብ ግልጋሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የልማት ተቋማት

ለምሳሌ:- ትምህርት ቤት ማቋቋም የአካባቢው ኅብረተሰብ ልጆቹን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲልክ የሚረዳ ግልጋሎት ነው። ክሊኒክ በመክፈት ሕክምና አገልግሎት በመስጠት ምሳሌ ሰበታ ቤተ ደናግል

## II. በቤተ ክርስቲያን የሚካሄዱ ልማቶች የገንዘብ ምንጫቸው የት ነው?

አሁን ባሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ለሚካሄዱ ልማቶች የሚከተሉት የገንዘብ ምንጮች ካሉት አማራጮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

፩. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ምእመናን አስተዋጽኦና ስዕለት የሚገኝ ገቢ

፪. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ በግልና በማኅበር የሚደረግ የምእመናን የርዳታና የስዕለት ገቢ

ምሳሌ:- ምዕመናን በማኅበር ሆነው የመረጡትን ገዳም በመሄድ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ

፫. ከአጥቢያ ጀምሮ በየደረጃው ወደ ላይ እስከ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ከሚደረግ ፈሰስ ለልማት ተግባር የሚመደብ በጀት።

፬. ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ትላልቅ ደብሮች ምንም ገቢ የሌላቸው ወይም አነስተኛ ገቢ ላላቸው የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሚደረግ የልማት ድጎማ ነው። ይኸኛው ገቢ ገንዘብ ያላቸው የሌላቸውን እንዲደግፉ የልማት ፕሮጀክት በመቅረፅ የሚደረግ ሊሆን ይችላል።

፭. ዕቅዱ ይፋ በሆነ ልማት ስም የሚሰበሰቡ ገቢዎች፣ ለምሳሌ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ወይም ለማሳደስ፣ ወይም ትምህርት ቤት ለማሠራት፣ መንበረ ጵጵስና ወይም መንበረ ፓትርያርክ ለማሠራት በየደረጃው የሚሰበሰቡ ገቢዎችን ያጠቃልላል።

፮. የውጭ ዕርዳታ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት አባል ድርጅቶች የሚለገስ የልማት ዕርዳታ ናቸው።

## III. በቤተ ክርስቲያን ልማት ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች

ልማትን በቤተ ክርስቲያን ስናስብ ምን ማለታችን እንደሆነና በቤተ ክርስቲያናችን የተከናወኑ ወይም እየተካሄዱ ያሉ የልማት ዘርፎችን ለማየት እንደሞከርነው በቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል ሰፊት ያለው ልማት እንደሚሠራ ለመገንዘብ እንችላለን። በተጨማሪ እስካሁን የሚሠራባቸውንና ወደ ፊት ቢሠራባቸው ልማትን በቤተ ክርስቲያን በበለጠ ያፋጥናል ተብለው የቀረቡ የገንዘብ ምንጮችን ተመልክተናል። ይሁን እንጂ እነዚህ የልማት ሥራዎች ሲሠሩ ምንም ችግር አልገጠመንም ማለት አይቻልም። በልማት ዙሪያ ያጋጠሙንን ችግሮች ለይቶ ማወቁ ደግሞ ችግሮችን አስወግዶ በቀጣይነት የተሻለ ለመሥራት የሚቻልበትን ዘዴ ለመቀየስ ይረዳል። በመሆኑም ዋና ዋና ችግሮችን በማንሣት መፍትሔያቸውን በጋራ እንፈልግላቸዋለን።

### ልማትን ወደ ኋላ ጎተቱ ተብለው ከሚጠቀሱት ችግሮች ጥቂቶቹ

፩. የቅንጅት ማነስና የልማት እቅድ አለመኖር:- ይህ ማለት ለምሳሌ ለአንድ ገዳም ከግለሰቦች የሚሰጥ ስጦታ ይኖራል በማኅበር ከተደራጁ ምእመናን የሚደረግ ዕርዳታ ይኖራል እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ መዋቅር የሚደረግ ድጎማ ሊኖር ይችላል። ሦስቱም የገንዘብ ምንጭ ስለማይተዋወቅ ወጥ የሆነ ዕቅድ ለማዘጋጀት ይቸግራል። ምን አልባትም ሦስቱም ገንዘብ የሚሰጡት ለአንድ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። በዚህ የተነሣ የገንዘብ መባከን ወይም ያለ አግባብ ወጪን ሊያስከትል ይችላል። እነዚህ ረጂ አካላት በቅንጅትና በዕቅድ ቢሠሩ መልካም የሥራ ፍሬ ማሳየት ይቻላል።

፪. የልማትን ፅንሰ ሀሳብ አለመረዳት:- በቤተ ክርስቲያን ልማት ሲባል ትኩረት ተሰጥቶት የቆየው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን መገንባት ነው። በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ዕርዳታ ሲጠየቅ የሚስተዋለው የዚሁ ጉዳይ ነው። ይኸኛው ባልከፋም ነበር። ሆኖም ግን ከሕንፃው ባሻገር ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ቋሚ ገቢ ማስገኘት የሚችሉ ድርጅቶችን በማቋቋም የአካባቢው ኅብረተሰብ ማኅበራዊ አገልግሎት መስጠትን ትኩረት ሊነፈገው አይገባም።

፫. የልማት ተቋማት የአስተዳደር ብቃት ማነስ:- ለገቢ ማስገኛ ተብለው ለቤተ ክርስቲያናት የሚቋቋሙ የልማት ድርጅቶች በአብዛኛው በአስተዳደር ብቃት ማነስ ውጤታማ አይሆኑም። ወይም ለአጭር ጊዜ ይሆናሉ። ስለዚህ አብዛኞቹ የገቢ ማስገኛ የልማት ተቋማት ዘላቂነት ሊኖራቸው አልቻሉም። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት በመስኩ የሰለጠነ ሰው አለመኖር፣ ሥልጠና ሲሰጥም የሠለጠኑ ሰዎች ከቦታው ሲነሱ ችግሩ ይከሰታል። ለምሳሌ ብዙ ወፍጮዎች አንድ ዓመት ሳያገለግሉ ቀርተዋል።

፬. የሠለጠነ የሰው ኃይልን በአግባቡ አለመጠቀም:- በአስተዳደርና በትምህርተ መለኮት ከፍተኛ ትምህርት ቀስመው ከውጭ ሀገርም ሆነ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የተመረቁ ተማሪዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ መስተዳድር ውስጥ ከተመደቡት አገልጋዮች የተፈለገውን ያህል አለመጣጣም በመኖሩ አጥጋቢ አገልግሎት አለመስጠቱ ይታያል።

፭. ጠቅላይ ቤተ ክህነትና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤቶች ከሚደረግላቸው ፈሰስ ላይ ለልማት በጀት በበቂ አለመመደብ፣ ቢመደብም ለክትትል እንዲረዳ ለምእመናንና ለካህናት አለማሳወቅ። ይህ ማለት በየደረጃው ያለው



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር በዓመት ከሚያገኘው ፈሰስ ለልማት በጀት የሚመደበውን ከፍ አድርጎ መመደብና አፈጻጸሙንም መከታተል ይገባዋል።

፮. ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ደብሮች ደካማዎቹን የሚረዱበት ስልት በበቂ ሁኔታ አለመኖር:- ቤተ ክርስቲያን አንድ እንደመሆኗ መጠን ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን ትላልቅ ደብሮችና ገዳማት ምንም ገቢ የሌላቸውን ወይም መጠነኛ ገቢ ያላቸውን የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት የሚደጎሙበት ስልት ሊነደፍና ሥራ ላይ ሊውል ይገባዋል። በቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ የበለጠ የልማት ሥራ ለመሥራት የምንፈልግ ከሆነ?

## IV. ልማትን በቤተ ክርስቲያን ለማፋጠን መወሰድ የሚገባቸው ዕርምጃዎች ምንድን ናቸው?

ከላይ ልማትን አንትተዋል ተብሎ የተጠቀሱ ችግሮችን ማቃለል ቢቻል ማስወገድ።

፩. ከተለያየ ምንጭ የሚገኘውን ገቢ በማቀናጀት የልማት ዕቅዶችን መንደፍ ማስፈጸምና አፈጻጸማቸውን መከታተል።

፪. ለማኅበረ ካህናትም ሆነ ምእመናን የልማትን ፅንሰ ሀሳብ ማስጨበጥና እንደ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ሌሎች የልማት ዘርፎችም ምእመናንን በማሳተፍ መሥራት እንደሚቻል ማሳወቅ እንዲለምደውም ማድረግ።

፫. የልማት ተቋማትን የአስተዳደር ብቃት ለማሳደግ፣ በሙያው ተከታታይ ሥልጠናዎችን ማካኼድና ቤተ ክርስቲያኒቱን በሙያው (በዘርፉ) ያፈራችውን የሠለጠነ የሰው ኃይል በአግባቡ መጠቀም። ይህን ካደረግን ዘላቂነታቸውንና የታሰበውን ጠቀሜታ እንደሚሰጡ ማረጋገጥ እንችላለን።

፬. በየደረጃው ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ወደ ላይ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከሚደረገው ፈሰስ የልማት በጀት መያዝና ምእመናንና ካህናት እንዲሳተፉበት ማሳወቅ፣ ማስፈጸምና መከታተል።

፭. ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ደብሮችና ገዳማት ገቢ የሌላቸውም ወይም አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የሚደጉሙበት ስልት መቀየስ።

ለምሳሌ:- ፕሮጀክት መቅረፅ

## V. እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አካል በልማት ያለው ድርሻ ምንድን ነው?

፩. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ካህናትና ምእመናን

- ለቤተ ክርስቲያናቸውና ለአካባቢያቸው የሚያስፈልግና የሚስማማ ልማትን መለየት፣ ማቀድ፣ መፈጸምና ማስተዳደር።
- ለልማት የሚሆን የገንዘብ ማግኛ ዘዴ መቀየስ ምእመናን ማስተባበር፣ የተገኘውን ገንዘብ በአግባቡ ለታቀደለት ሥራ ማዋል።

፪. የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትና የሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

- በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ድጋፍ መስጠት፣ ማበረታታት፣ እንዲሁም አፈጻጸሙንና ዘላቂነቱን መከታተል።
- የደከሙ ቤተ ክርስቲያናትን ለልማት ማነቃቃት፣ የበጀት ድጎማ ማድረግ፣ የተሻለ ገቢ ያላቸው ደብሮች እንዲረዷቸው ማበረታታት።
- በወረዳ ወይም ሀገረ ስብከት ደረጃ የልማት ሥራዎችን ማቀድ፣ መተግበርና ማስተዳዳር።

፫. ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

- በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያኒቱ በአገሪቱ የምታካሂዳቸውን የልማት ሥራዎች ማነሣሣት፣ መደገፍና ማበረታታት።
- ለደካማ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ከፈሰስ ድጎማ በጀት መመደብ፣ ገቢ ያላቸው ደብሮች ደካሞቹ የሚረዱበትን ስልት መንደፍና መተግበር።
- በአገር አቀፍ ደረጃ የቤተ ክርስቲያን ልማቶችን ማቀድ፣ መተግበርና ማስተዳደር።

፭. የልማት ኮሚሽን

- ገቢ የሌላቸው ወይም አነስተኛ ገቢ ያላቸው የገጠር ቤተ ክርስቲያንና ገዳማት የገቢ ምንጭ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ማቋቋም።
- ካህናትን በዕደ ጥበብ፣ በልማት ሥራ፣ በአስተዳደርና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከል ያሉትን ማስተማርና ማሠልጠን።
- ለማኅበረ ሰቡ ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ትምህርት ቤቶች ክሊኒክ ወዘተ ያሉትን መገንባት።

፮. ማኅበረ ቅዱሳን

- አድባራትና ገዳማትን በማጥናት ለልማት የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፣
- ራሳቸው የልማት ገንዘብ ለሚያሰባስቡ አድባራትና ገዳማት በጥናትም ሆነ የምክር አገልግሎት በመስጠት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ።

፯. በበጎ ፈቃደኝነት የሚረዱ ግለሰቦችና ማኅበራት

- ማኅበራትም ሆኑ ግለሰቦች ለገዳማትና አድባራት የሚሰጡት ገንዘብ በልማት ተግባር ላይ ለማዋል ፈቃደኛ እንዲሆኑ ማስተማርና ማሳወቅ የሚለግሱት በልማት ዕቅድ ላይ መካተቱን እንዲያውቁት ማድረግ።
- በግልም ሆነ በማኅበር ልማትን እንዲያግዙ ማኅበራትና ግለሰቦች መቀስቀስ፣ የልማት ዕቅዶችን ማሳወቅ፣ በቅንጅት የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠር እና እንደነዚህ ዓይነቶችን ማብዛት።

፰. ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ገዳማትና አድባራት

- የእርሳቸውን አጥቢያ ከማልማት ባሻገር ገቢ የሌላቸውን ወይም አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ቤተ ክርስቲያናት እንዲረዱ ማመቻቸት ነው ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ፍሬ ሐሳቦች ሁሉም ተባብሮ ለመፈጸም ቢንቀሳቀስ እቅዱን በአጭር ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል። ✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



# ከወጣቱ ለወጣቱ

## ኃጢአትን የምናሸንፈው ሕግን በመጠበቅ ነው

በመምህር ዕንቈባሕርይ ተከሥተ



ብዙዎቻችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን መኖሩን ብናውቅም በእርዳታው ከሚጠቀሙ በስተቀር በቅርብ ሆነን ኮሚሽኑ ምን እንደሠራ ምንስ እንዳል ሠራ ለማወቅ በቂ ግንዛቤ አላገኘንም። በእርግጥ ልማት ኮሚሽን ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ሳንካ ባይለየውም የሚሠራው ሥራ በሚድያና በሌላ መንገድ ለሕዝቡ ማሳወቅ ነበረበት።

ይህም ባለማድረጉ ኮሚሽኑ በሕዝቡ ዘንድ ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ቆይቷል። ሩቅ ሳንሄድ ስለ ልማት ኮሚሽን የሥራ እንቅስቃሴ ካህናቶቻችን የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶቻችን ብዙ አያውቁም። ለምን ቢባል የገለጻላቸው ባለመኖሩ ነው። አሁንስ ከምን ላይ ነው ያለው ባለፉት ሰባት ዓመታትስ ምን ሠራ ለሚለው መልሱ በዚህ ጽሑፍ ተካቶአል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ባለፉት ሰባት ዓመታት (ከ፲፱፻፹፯– ፲፱፻፺፫ ዓ.ም) ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

በአካባቢ ጥበቃና የግብርና ምርት ለማሳደግ ከ፹፯ ሚሊዮን በላይ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ተደርጓል፤ ፩ ሺህ ፳፻ ኪ.ሜትር ለአፈርና ውሃ ዕቀባ የሚውሉ እርከኖች ተሰርተዋል፤ ከ፫ ሺህ ፳፻ ሄክታር መሬት በላይ ተከልሏል የተፈጥሮ ደን እንዲያቆጠቁጥ ተደርጓል፤ ፳፻፶ ሞዴል ገበሬዎች ሰልጥነው ፯ መቶ ፹፰ ሺህ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞች እንዲተከሉ ተደርጓል፤ ፲፪ የእንስሳት ጤና ክሊኒክ ተሰርቷል፤ ፰ መለስተኛ መስኖ ግንቦችን በመሥራት ፳፻ ሄክታር አልምቷል። በድርቅ የተጎዱ ገበሬዎችን ለማቋቋም ፩ ሺህ ፯፻፶፯ በሬዎችን ፩፻፶፪ ፈረሶች ከእርሻ መሣሪያዎች ጋር እንዲሰጣቸው ተደርጓል። ንጹሕ የመጠጥ ውኃን ለማዳረስ ፬፻፶፰ ምንጮችና የእጅ ጉድጓዶች እና ፲፰ ጥልቅ የውኃ ጉድጓዶች ተቈፍረው ከ፫ መቶ ፲ ሺህ ሕዝብ በላይ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል። በጤና ረገድ ፱ የጤና ኬላዎች ፫፻፵ የተሻሻሉ የጋራ ሽንት ቤቶችና ፩ ሺህ ፬፻፵፰ የተሻሻሉ የግል ሽንት ቤቶች ተገንብተው ከ፺ ሺህ ሕዝብ በላይ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል።

ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ፯ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋ፤ የገጠሩን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማገዝ ፩፻፳፯ ኪ.ሜ የገጠር መንገድ ተሰርቷል።

ባለፉት ሰባት ዓመታት ፩ መቶ ፴፰ ሺህ ፳፻፹ ኩንታል የምግብ እህል በዕለት ደራሽ ርዳታ ለ፫.፯ ሚሊዮን ሕዝብ አከፋፍሏል። በአማካይ በዓመት ፪፻፰ ሺህ ሠራተኞች የምግብ ልብስና መጠለያ ሕክምናና ሌሎች ርዳታዎችን በማድረግ በአማካይ ፫፻፳፫ የስደተኛ ልጆች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል።

ስልጠና በአለፉት ፯ ዓመታት በድምሩ ፲፯ ሺህ ፮፻ ገበሬዎች ፩ ሺህ ፯፻፹ ካህናትን ፫ ሺህ ፳፻ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችና ፲፩ ሺህ ፬፻፵፳ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የአጠቃላይ ዕውቀት የአስተዳዳር የሞያ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

በዚሁ ከወጣቱ ለወጣቱ አምዳችን ልማት ኮሚሽኑ ምን እየሠራ እንደ ሆነ እንዲገልጹልን አቶ አደሬ አዱኛ በኮሚሽኑ የጥናትና ፕላኒንግ መምሪያ ኃላፊ አነጋግረናል መልካም ንባብ:-

ፈለገ ጥበብ – በመጀመሪያ ስምህን ብትገልጽልኝ?

አቶ አደሬ – ስሜ አደሬ አዱኛ እባላለሁ የእናቴ ስም ብዙነሽ ቶላ ነው የተወለድኩት አርሲ ክፍለ ሀገር ነው። እድገቴ ገጠር ነው ኮራ ማርያም ይባላል። እረኝነት (ከብት) መጠበቅ ሞክሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – የእረኝነት ጉዳይ ከተነሣ እስኪ ትንሽ ገለጥ አድርግልኝ?

አቶ አደሬ – ትንሽ ነበርኩ አያቴ ጋር ነበርኩ እሳቸው እያረሱ እኔ ከብት እመልስ ነበር፤ በጣም እንደምሯሯጥ ትዝ ይለኛል። እርሻ ሳልጀምር ነው ወደ ከተማ የገባሁት ቤተሰቦቼ ቀደም ብለው ወደ ከተማ ገብተው ስለ ነበር። እኔ ከአያቴ ጋር እያለሁ አባቴ አስተርእዮ ማርያም ቤተሰብ ሊጠይቅ ሲመጣ እኔ አብሬ ወደ ከተማ ገባሁ በዚያው ቀረሁ።

ፈለገ ጥበብ – የተወለድክበት ዓመተ ምሕረት ታስታውሰዋለህ?

አቶ አደሬ – በዚህ በኩል ሁለት አስተሳሰብ ነው ያለው። የፋሲካ ዕለት እንደ ተወለድኩ የሚነገረኝ። ዓመተ ምሕረቱ እናቴ ቁስ ነው እሱ በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም አባቴ ደግሞ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም ይላሉ። እኔ ግን አማካይ ወስጄ በ፲፱፻፵፮ ዓ.ም የሚለውን ወስጄ አለሁ።

ከዚያ ወደ ትምህርት ቤት እንደገባሁኝ ለመማር ጉጉት ነበረኝ። እኛ ገጠር ስለሆን ከተማ ሂደው ተምረው የሚመጡ ስናይ ትልቅ ነገር ይመስለን ነበር፣ የዚያ ጊዜ ጧት ፫ ሰዓት ነበር ትምህርት የሚገባው ለጥናቱ ጊዜ የረዳኝ እቤታችን ፈረስ አለችን ፈረስዋን ለመልቀቅ ጧት እነሳለሁ። ከዚያ ወደ ጥናቴ እገባለሁ። በዚህ ዓይነት የጥናቱ ልምድ በዚያ ተለምዶ ቀረ። መምህራኖቼም በጣም ይወዱኝ ስለ ነበረ በርታ ይሉኛል።

ፈለገ ጥበብ – አሁን አንተ ያለኸው በዚህ ልማት ኮሚሽን በዕቅድና ፕላን ላይ ነው። ከዚህ አንጻር ወጣቱ በዕቅድና ፕላን እንዲሠራ ምን ትመክረዋለህ?

አቶ አደሬ – በእርግጥ እኔም እንደአየኋቸው አብዛኛው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ያሉ ልጆች ናቸው። በእርግጥ እንኳ ልጆች ይቅርና ትልልቅ ሰዎች አብዛኛው በዕቅድ መሥራት የተለመደ አይደለም። በዕቅድ መሥራቱ በጣም ጠቃሚ ነው። በዕቅድ ለመሥራት አንድ ነገር ከመሥራቱ በፊት በተለየ ደረጃ ሐሳብ መለዋወጥ ያስፈልጋል። ለምሳሌ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ የበላይ አካሉ ሰበካ ጉባኤ ነው። የሰበካ ጉባኤው እና የሰንበት ትምህርት ቤት የሥራ አመራር በቅርብ ተገናኝተው መነጋገር መቻል አለባቸው። አንዳንድ ስህተቶች የሚከሠቱ ዝም ብለው ሥራዎች ይጀምራሉ ሳይነጋገሩ ማለት ነው። ቢያንስ በዓመት ይህን ገንዘብ ይህን ያህል የሰው ኃይል ያስፈልጋል የሚለው በእቅድ መቅረብ አለበት። የተለያዩ አካላትን የቤተ ክርስቲያን አካላት ምእመናን ጨምሮ ይህን ያህል ርዳታን እንጠብቃለን ማንኛው ለቤተ ክርስቲያን ቀናኢ የሆነ ሰው የሚሳተፍ ከወዲሁ መነጋገርና ያንን በጽሑፍ ማስቀመጥ እንደ ገና መመያየት ብዙ የሐሳብ መንሸራሸር ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው መሆን ያለበትም በዚሁ መልኩ ነው።

ፈለገ ጥበብ – እንደሚታወቀው በሰንበት ትምህርት ቤቶች ብዙ የሰው ኃይል አለ ይህን የሰው ኃይል በሥራ ላይ ለማዋል ምን ቢታቀድ? ወደ ኢኮኖሚ እና ወደ ልማት ለማሸጋገር ምን ቢደረግ ነው የሚሻለው?

አቶ አደሬ – ይኸ ቀላል ነገር አይደለም ስልህ ብዙ ሙከራ ብዙ ጥናት በመንግሥትም በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃም በተለያዩ በአደጉ አገሮችም ጥናት ተካሂዷል። ይኸኛው እንግዲህ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ወሳኝ ነው።

ወጣቱና ማኅበረሰቡ ብንመለከት አንድ የሚታየኝ ነገር የሥራ ባህል ማዳበር ያስፈልጋል። በእኛ ሀገር ብዙ የሥራ ባህል አልዳበረም።

ፈለገ ጥበብ – በከተማ ልትለኝ ነው? ባለአገሩ ሠራተኛ ነው።

አቶ አደሬ – በከተማ ማለት ነው። የከተማው ነው ለማለት የፈለኩት የቅጥር ሠራተኛ



www.ethiopianorthodox.org

የሚመለከት ነው። የግል ጥቅም ለማካበት ነው የሚያደሉ። ለኅብረተሰብ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሥራ በየአካባቢ ያተኮረ ሰፋ ያለ እቅድ ማድረግ ያስፈልጋል። እኔ ዛሬ ገንዘብ ቢኖረኝ ለነገ ማለት አለብኝ። ዛሬ ለቤተ ክርስ ቲያን ብንሠራ ለነገ ለትውልድ የሚተርፍ ነው። ለነገው ትውልድ የሥራ ባህል ማቆየት አለብን ቅርሳችን እምነታችን ጠብቀን ማቆየት አለብን። አሁን የምናየው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶች እንቅስቃሴ ከተወሰኑ ዓመ ታት በፊት አልነበረም ወደፊት ደግሞ በተጠ ናከረ ሁኔታ የሚቀጥልበትን ማጥናትና መሥ መር ማስያዝ አለብን።

ፈለገ ጥበብ – ድህነት ከማስወገድ (ከማ ጥፋት) አንጻር ድህነት ስልህ የቁሳቁስ (የማቴ ሪያል) ድህነት አይደለም ድኅነታችን የአስተሳ ሰብ ነው። ያለን ማቴሪያል ቢሆንም በአግባቡ ባለመጠቀማችን ድህነት በእኛ ላይ ተንሠራ ፍቶ ይገኛል። ከዚህ የተነሣ የውጪ ርዳታ ከመቀበል አልዳንም፤ና ወጣቱ ምን ቢሠራ ነው ከዚህ ድኅነት መውጣት የምንችለው?

አቶ አደሬ – ድህነት ብዙ ገጽታዎች አሉት በዓለም አቀፍ ደረጃ የራሱ ገጽታ አለው፤ ማለት የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ራሱ በሀገራቱ ላይ እንዳለ የሚያመጣው ጫና አለ። ለምሳሌ:- እኛ ኤክስፖርት የምናደርገው ቡና ነው። የምንገዛው ግን መኪና ማሽነሪ ነው። የአደጉ ሀገሮች ራሳቸው በሚያስተካክሉት የገንዘብ ምንዛሬ አርጅመንት የታዳጊ አገሮች ገበያ መጣልና የእነሱ የፋብሪካ ዕቃዎች ማስወደድ የግብይይት ሁኔታ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው። የመንግሥት ፖሊስ ራሱ ተጽዕኖ አለው። መንግሥት ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ ፍትህ ያለው አስተዳደር ካልዘረጋ በስተቀር አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ሰው ራሱ የሰንበት ትምህርት ቤት አባል ምእመን ከውስጥ የመ ነጨ ለአገሪቱ ዕድገት በአእምሮው ማሰብ መኖር አለበት። ከድኅነት ለመውጣት መሥ ራት አለበት። እያንዳንዳችን ሊሠማን ይገባል።

ፈለገ ጥበብ – ድህነት ሲባል በማቴሪያል ብቻ አይደለም የድሮ ድህነት ከተባለ የአቅም ማነስና የምግብ እጥረት ይሆናል። በአሁኑ እኔ የማየው ባህል የሚሸረሸር ነው። አንድ ኅብረ ተሰብ ባህሉ ከተሸረሸረ በአንጻሩ የሌላ ባህል ተገዥ ከሆነ ትልቁ ድህነት የሚባለው ይኸው ነው። በሁለተኛ ደረጃ ቅርስን የመጠበቅ የማስከበር የነበረው ባህል እየናቀና የባዕድ ሀገሮች አፍራቃ ሆኖ ይገኛል በራስ የመተማ መን ባህል እየጠፋ ነው። ሌላው ድህነት በገን ዘብ ሊጠገን ይችላል፤ ይኸን በምን ይጠገናል ብለህ ታምናለህ?

አቶ አደሬ – ይኸን በመሠረቱ ማንነትን የማወቅ ጉዳይ ነው። እኛ በእውነት ነው የም ልህ ብዙ ቅርስ አለን ማንነታችንም የተጠበቀ ነው። ነጻነታችን ተጠብቆ የቆየ ነው።

ለዚህች ሀገር ቤተ ክርስቲያናችን በሥር ዓት የማሳደግ በቅርስ አጠባበቅ ባለውለታ ናት። ሥርዓቷ ራሱ ማንነትህን የሚገልጽ ነው።

አስታውሳለሁ ድሮ ኢለመንተሪ ሆነን የግብረ ገብ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ የነበ ረው የተማሪና የአስተማሪ ግንኙነት ዛሬ በዚ ያው ዓይነት አይደለም ያለው እኛ ድሮ አስተ ማሪዎችን ስናይ መንገድ ለቀንላቸው እንሄድ ነበር፤ የዛሬ ጊዜ ተማሪ አስተማሪ ልምታ የሚል ነው። ይኸ ምንድን ነው? ብንል ልቦ ናው በግብረ ገብ አልተገዛም ወይም ልጆች ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት አልተላኩም። ወላጆች ቢሆኑም ስለ ሥነ ምግባር አልተ ጨነቁም ድሮ በባህላችን ውስጥ ሥራ አጥነት ታላቅን አለማክበር ታላቅ ውርደት ነበር፤ በእምነት መቀለዱ የመጣ አሁን ነው።

በእኔ እድሜ እንዴት ያለ ክብር ነበር፤ ቤተ ክርስቲያን ሂደን አልባሳት ለመልበስ እንዴት ነበር የምንሽቀዳደመው። የዛሬ ልጅ አርሞኒካ ይዞ ነው የሚደንሰው እና ወላጆችም ማወቅ ያለባቸው በሰንበት ትምህርት ቤት ለሌላው የሚጨነቅ ሕግን ሽማግሌን ሀገርን የሚያከብር እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ፈለገ ጥበብ – ልማት ኮሚሽናችን ወጣቱን በልማት ለማሳተፍ ያደረገው ነገር አለ ወይ?

አቶ አደሬ – በልማት ኮሚሽን ለብቻ ለወጣቶች ተብሎ የተቀመጠ ባይኖርም አንድ አንድ የኅብረተሰቡ አካል በምናደርጋቸው የልማት ሥራ ማለት ነው ከኅብረተሰቡ አብ ሮው ይጠቀማሉ። ከዚህ ባሻገር እንደሚ ታወቀው በሰንበት ትምህርት ቤቶች በኩል የሥራ አመራር እንዲሠለጥኑ በበጀት ይደግ ፋል ለመጽሔትዋም በተወሰነ መልኩ ይረ ዳል። ቀደም ሲልም የሰንበት ትምህርት ቤቶችን በማደራጀት በኩል የበኩሉን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በሰበካ ጉባኤም በካህ ንት ማሠልጠኛም እንዲሁ በማቋቋም ረገድ ሰፊ ሚና ተጫውቷል። አሁንም ቢሆን በቀጣ ይነት ይሠራል።

ፈለገ ጥበብ – ግን አሁን አሁን ስናይ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ከ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ጋር ስናነጻጽረው በከፍተኛ ደረጃ በጀቱ ቀንሰዋል በአሁኑ ጊዜ በልማት ኮሚሽን የነበረው በጀት እየተስተካከለ አይደለም ያለው ለመንቀሳቀስ ያህል ነው ይህ የሚከሠተው በምን አንጻር ነው? በእርዳታ ሰጪዎች በኩል ነው? ወይስ ኮሚሽኑ ሌላ የሥራ ዕቅድ ስለ አወጣ ነው።

አቶ አደሬ – አሁን ያነሳኸው ጥያቄ በጀቱ የሚገኘው ከብ ጠረጴዛ ከሚባለው ፕሮግራም ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዚህ ከክብ ጠረጴዛ የሚገኘው በጀት እያነሰ ነው የመጣው። ለሌሎች ፕሮግራሞች የሚገኘው በጀት ከክብ ጠረጴዛ ውጪ ነው።

ፈለገ ጥበብ – ልማት ኮሚሽናችን ሌላ መንገድ መፍጠር አይችልም እንዴ? ከዚያ ብቻ ካልሆነ መቆም አለበት ወይ? ምክን ያቱም ይኸ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክሎ ነው የሚንቀሳቀሰው ቅዱስ ሲኖዶስ እንደወሰነው።

የሰንበት ትምህርት ቤቶች የካህናት ማሠ ልጠኛ የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ በራሳቸው ርዳታ መጠየቅ አይሉምና።

አቶ አደሬ – ለወደፊቱ ለሚደረገው ነገር በዚህ አካባቢ በይበልጥ ደግሞ ገዳማትና አብ ያተ ክርስቲያናት ለመርዳት የአብነት ትምህ ርት ቤቶችን መንከባከብን በገዳም ለማቋየት፤ ቅርሶችን ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ በጥናት ደረጃ ላይ ነው። እንዲሁም ካህናት በልማት እንዲንቀሳቀሱ እና ልማቱን እንዲመሩ ሥልጠ ናም ለማድረግ በጥናት ላይ ነው ያለው።

ፈለገ ጥበብ – የዘመኑ ትውልድ ከምንም በላይ እያጠቃው ያለ ኤች አይቪ (ኤድስ) ነው። ወጣቱ ከመቅሠፍቱ ለመዳን ምን ማድ ረግ አለበት? ልማት ኮሚሽንስ በዚህ በኩል እያደረገ ያለ እንቅስቃሴ በቂ ነው ወይ?

አቶ አደሬ – በኤች አይ ቪ ዙሪያ ችግሩ በጣም እየከፋ የመጣ ነገር ነው በይበልጥ ጠቀ ሚታ ያለው በእያንዳንዱ ወይም እያንዳንዱ ሰው ስለ ነገሩ ተገንዝቦ ስለሚያደርገው ጥንቃቄ ነው። የኤች አይቪ (ኤድስ) በሽታ ከ፹፭ ፐርሰንት የሚተላለፈው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንደምታዘው ወጣቶች ቅድመ ጋብቻ ምንም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንደሌለባቸው ነው። እንዲ ያውም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጸንተው በነፍሳቸውም በሥጋቸውም ተጠብቀው በቤተ ክርስቲያን መጋባት አለባቸው። ይኸ በሽታ የመጣው ስለ ኃጢአታችን ብዛት ነው። ስለ ዚህ ኃጢአትን የምናሸንፈው ሕግን በመጠበቅ ነው።

ፈለገ ጥበብ – አደሬ አንተ በእቅድና ጥላን መሥራት ምን ያህል እንደሚጠቅም ታውቀዋለህ፤ ትረዳዋለህ፤ ስለዚህ ልማት ኮሚሽኑ ርዳታን ከማቅረብ ባሻገር ቋሚ የሆነ ሥራ እንዲሠራ አልተደረገም፤ በአጠቃላይ፤ ጊዜያዊ ርዳታ ከመስጠት ይልቅ ለምን ራሱን ችሎ የሚሠራበት መንገድ አልፈጠረም?

አቶ አደሬ – ልማት ኮሚሽን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት እየጣረ መሆኑን ነው የማውቀው።

ፈለገ ጥበብ – ወደ አሁኑ እንምጣ እንደ ምሳሌ አድርጌ የምናገረው የሕፃናትና ቤተሰብ ድርጅት ሆስፒታል ሠርቷል ገንዘብ የሌላቸ ውን በነፃ፤ ገንዘብ ላላቸው እንደየአቅሙ እያስከፈለ የሕክምና አገልግሎት ይሠጣል። ኮሚሽኑ ለምን እንደዚህ አልሠራም? የገንዘብ ችግር ነው? ወይስ ሌላ ምክንያት ነበረው?

አቶ አደሬ – የልማቱ ሥራ ገጠር ነው ያደረገው በአብዛኛው ከ፲፱፻፸፫ እንደ ኤ.አቆ ጣጠር ፕሮግራሙ ያደረገው መንገድ ለሌላ ቸው መንገድ፤ ውሃ ለሌላቸው ውሃ በማገል በት ነው የቆየው። ትምህርት ቤቶች እየተሠሩ ነው፤ ክሊኒኮች ይሠራሉ። ቢያንስ በዓመት ፫ ከዚያም በላይ ክሊኒኮች ይሠራሉ። በዓመት እስከ ፰ ሺህ ሕዝብ የሚጠቀምበት እየሠራ ነው። አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማም ችግር መኖሩን አምኖ እቅድ እያወጣ ነው።

ፈለገ ጥበብ – የምታስተላልፈው መልእክት ካለ?

አቶ አደሬ – ወጣቱን ትውልድ የቤተ ክርስቲያን አደራ እንዲረከብ ነው። የቤተሰ ክርስቲያኒቱ አደራ የሚረከበው ደግሞ ቤተክ ርስቲያንን ሲያውቅ ነው። እያንዳንዱ ወጣት ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች ገብቶ ማየት አለበት ያን ማድረግ ሲችል ነው እምነቱን የሚ ያውቀው አንዳንድ ጊዜ እኮ በወጣትነት ጊዜ መኖርህን ትረሳለህ እኮ!

ፈለገ ጥበብ – አመሰግናለሁ።

አቶ አደሬ – በጣም አመሰግናለሁ። ✣





# ዜና መጽሔት

## የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ አዲስ ኃላፊ ተመደበለት


መልአከ ኃይል ቃለጽድቅ እውነቴ

የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል አስተዳዳሪ በተሠማሩባቸው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደ ራዊ ሥራዎች በሁሉም አቅጣጫ ያስመዘገቡት የሥራ ውጤት የላቀና ሁሉንም ያስደሰተ በመ ሆኑ በያዙት ሥራ ላይ ደርበው በመንበረ ፓትርያርክ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ ሆነው እንዲሠሩ ቋሚ ሲኖዶስ ጥቅምት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም በስብ ሰባ መረጦ እንዲመደቡ በ፫/፫/፺፩ በቁጥር ፶፪/፪፻፸፰/፺፩ ባዘዘው መሠረት የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትም ከኅዳር ወር ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ጀምሮ በቁጥር ፩ ሺህ ፪፻፵፩/፲፩ ሺህ ፫፻፯/፺፩ በጻፈው ደብዳቤ መልአከ ኃይል ቃለጽድቅ እውነቴ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ ሆነው መሾማቸውን አስታውቋል።

## ቅዱስ ሲኖዶስ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከጥቅምት ፯–፱ ዓ.ም ባደረገው ፳ኛው መደበኛ ስብሰባ ያሳለፈውን የውሳኔ ሐሳብና የሰጠውን ዓመታዊ የሥራ መመሪያ መርምሮ ለማጽደቅ የተደረገ ስብሰባ ነው።

ከጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም በቁጥር ሰአ ፩/፲፪/፺፩ ከሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ከተጻፈው ሸኚ ደብዳቤ ጋር የተላከው የውሳኔ ሐሳብና የሥራ መመሪያ ለቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ቀርቦ በንባብ ተሰምቷል።

ሥራው ከሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲ ያኒቱ አስተዳደር ዘርፎች የተጠናቀረው የ፲፱፻፺፫ ዓ.ም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት መነሻ አድርጎ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪ ያጅ ሪፖርት መሠረትነት የተዘጋጀው የጋራ መግለጫ በሦስት ደረጃ ማለት፤

፩ኛ. ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ቅድመ ሰበካ ጉባኤ የነበራትን አስተዳደር በመተንተን

፪ኛ. በ፲፱፻፺፫ በጀት ዓመት የተሠራውን በመዘርዘር

፫ኛ. በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም መከናወን የሚገባውን የሥራ ዕቅድ በመንደፍ ተጠናቅሮ የቀረበ ዘገባ መሆኑንም ቅዱስ ሲኖዶስ ለመገንዘብ ችሏል።

በጋራ መግለጫው በተመለከቱት ባለ ሃያ ነጥቦች ዝርዝር እንደ ተገለጸው የሥልጣነ ክህ ነት አሰጣጥ ጉዳይ መስፈርት እንዲኖረው ሆኖ ጥራትና ብቃት ያላቸውን ተተኪ ካህናት ማስገ ኘት አስፈላጊ እንዲሆን በተራ ቁጥር ፲፰ ላይ ተጠቁሟል።

በዚህ መነሻነት ሥልጣነ ክህነትን የሚቀ በሉ ዲያቆናትና ቀሳውስት ሊያሟሉት የሚገባ ቸው መስፈርት መጠናትና መዘጋጀት እንዳ ለበት ምልዓተ ጉባኤው በስፋት ተነጋግሮአል።

በተለይም የዲቁናንና የቅስናን ሥልጣነ ክህነት የሚቀበሉ አገልጋዮች የሚከፍሉት ገንዘብ ጉባኤውን ሲያነጋግሩ ከዋሉት ነጥቦች አንድ ሆኖ ተመዝግቧል።

እንደዚሁ ሁሉ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥራ ዘርፍ የሚከናወን ሆኖ ክፍያን የሚጠይቅ ሌላው የገቢ ምንጭ ማስገኛም ጉዳይ ለውይ ይት ቀርቦ ምልዓተ ጉባኤው በየአንዳንድ ዝር ዝር ነጥብ የውሳኔ ሐሳብ ሰጥቶበታል።

ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተ ዳደር ዙሪያ የተለያየ መልክ ያለው የክፍያ ዓይነት እንደሚፈጸም በማስመልከት ከየአቅጣ ጫው የቀረበውን ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ ሊደ ረግ በሚገባው አፈጻጸም ተወያይቶ የሚከ ተለውን ውሳኔ ሰጠ።

## ውሳኔ

ከፍ ብሎ እንደ ተመለከተው የቤተ ክር ስቲያኒቱን ምግኔ ሀብት ለማዳበር በሚል እም ነት ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ ጀምሮ ለሚፈጸመው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገል ግሎት አስፈላጊው የገንዘብ ክፍያ እንደሚደ ረግ ይታወቃል።

የሚፈጸመው የክፍያ ዓይነት፤

- የዲቁናና የቅስናን ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል
- የክርስትና የምስክር ወረቀት ለማግኘት
- በሥርዓተ ተክሊል የጋብቻ ሕግ መሠረት ሕጋዊ ጋብቻን ለመፈጸምና የምስክር ወረቀት ለማግኘት
- የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እድሳትና ለመሳ ሰለው የሚደረገው ክፍያ ሁሉ እንደ ማስረጃ ሊጠቀስ የሚገባ ነው።

ይሁንና ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምትፈ ጽመው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በየደረጃው እየተደረገ ያለው የክፍያ ዓይነት ተስተካክሉ ሥርዓት መያዝ እንዳለበት ቢታ መንበትም በተለይ የዲቁናና የቅስና ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል ከብር ፭–፲፭ በሚደርስ ሁኔታ የገንዘብ ክፍያ እንደሚፈጸም ስለተነገረ የክፍያው ዓይነት አንድ ወጥ ሆኖ በሕጋዊ ደረሰኝ ይፈጸም ዘንድ እንዲስተካከል ማድረግ አስፈልጓል።

ስለዚህ በየአቅጣጫው የሚካሔደው የክፍያ ዓይነት በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በኩል ተጠንቶ በቀረበ ጊዜ ሁኔታው እየታየ በቋሚ ሲኖዶስ የሚወሰን ሆኖ ሥልጣነ ክህነትን በሚመለከት ግን፤

፩ኛ. የዲቁናን ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል የሚፈልግ ደቀ መዝሙር አስፈላጊውን መስ ፈርት አሟልቶ ሲገኝ ለሚሰጠው የክህነት ማስረጃ የኅትመት ዋጋ ብር ፩ (አንድ ብር) እየከፈለ የዲቁናን ሥልጣነ ክህነት እንዲቀበል።

፪ኛ. እንደዚሁ ሁሉ የቅስናን ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል የሚፈልግ ዲያቆን አስፈ ላጊውን መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ለሚሰጠው የክህነት ማስረጃ የኅትመት ዋጋ ብር ፪ (ሁለት ብር) እየከፈለ የዲቁናን ሥልጣነ ክህነት እንዲቀበል ሆኖ ለተደረገውም ክፍያ ሕጋዊ ደረሰኝ እንዲኖረው

፫ኛ. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፤ ያሳለፈው የውሳኔ ሐሳብና የሰጠው የሥራ መመሪያ ያለፈውን የሥራ ሒደት በመገምገምና የወደፊቱን የሥራ ዕቅድ በማመቻቸት የቀረበ የሥራ አፈጻጸም ውጤት የመሆኑን ያህል በይዘቱም ሆነ በትምህርት ሰጭነቱ ጠቀሜታ ያለው የሥራ መመሪያ መሆኑ ታምኖበት ቅዱስ ሲኖዶስ የተላለፈውን የውሳኔ ሐሳብና የተሰጠውን የሥራ መመሪያ ተቀብሎ አጽድቆታል።

በዚህ መሠረት ከሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ የቀረበው ባለ አሥር ገጽ የሥራ መመሪያና የውሳኔ ሐሳብ በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች በኩል በተግባር ይተረጎም ዘንድ ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ወስኗል። ✣





www.ethiopianorthodox.org

# መድፍን ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንንና ስጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት፣ የእመቤታችን፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ ስጣላጅነትና ተራዳኢነት የሚተነተንበት ስለሆነ መግረረ ፀር ተባሉ::



በመሠረቱ ታቦት ማለት ምን ማለት ነው? ታቦት የሚለው ቃል በተለያዩ ቋንቋዎች የተለያየ ስም ተሰጥቶት እናገኘዋለን። ለምሳሌ:-

በቅብጥ ቋንቋ ቴቢ
በዕብራይስጥ ቴባ ቴቡታ
በዓረብ ታቡት

በግዕዝ ደግሞ ታቦት ትርጓሜውም ማኅደር ማለት ሲሆን ማኅደርነቱም ቃለ እግዚአብሔር ለሆነው አሠርቱ ቃላት ለተጻፈባት ፅላት ነው። ይኸውም በቅዱሳት መጻሕፍት እንጻር ሲታይ:-

ታቦት ዘመርጡል ከምን እንዲሠራ እንደታዘዘ (ዘጸ.፳፭፥፲) ከብዙ ዘርፍ ጋር ተናቦ ይገኛል። ለምሳሌ (ዘጸ.፴፮፥፩) ስያሜው ታቦተ እምላክ ታቦተ እግዚአ ብሔር

ታቦተ ጽዮን
ታቦተ ኪዳን
ታቦተ ሕግ
ታቦተ ጽሉ

ታቦት ምሥዋዕ ሌላም ብዙ መጥቀስ ይቻል ነበር። ከጊዜ እጥረት አኳያ ነው እንጂ ስለ ታቦት የማይናገር መጽሐፍ አይገኝምና ስለ ታቦት ይህን ካልን:-

ጽላት የሚለውስ? በመሠረቱ ጽላት ለሁለትና ከሁለት በላይ ላለው የሚነገር ሲሆን በልማድ ግን በአንድ ይነገራል። ሕግዚአ ኃያላን እግዚአብሔር በደብረ ሲና ዐሠርቱ ቃላትን በላዩ ላይ ጽፎ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ ለሰ ጠው ቃላት ማኅደር መቅረጫ ማኅሪያ የሆነው ነው። በሐዲስ ኪዳን ዘመን አጠራር ግን ታቦቱን ፅላት ፅላቱንም ታቦት እየተባለ ይጠራል። ይህም የሚያማይ አዳሪውን በማደሪያው፣ ማደሪያውም በአዳሪው «በስመ ሐዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር ወበ ስመ ማኅደር ይጼዋዕ ሐዳሪ» እንደ ተባለው ሁሉ በዚሁ ስያሜ አጠራር ለመጥራት ይመስላል።

በመሠረቱም ታቦት የጽላት ማደሪያ ማኅሪያ ብቻ ሳይሆን መቃም መገለጫም ነው። ለምሳሌ በታቦት ፊት የአሪት ሊቀ ካህናት የዓመት ጸሎት ሲያቀርብ ድምፅ ከፈጣሪው ሰምቶ ምሕረት አግኝቶ ይወጣ ነበር። በአሁኑ ጊዜም በታቦት ፊት የሚቀርበው ጸሎት የሚቀርበው አስተብርኮትና ስግደት በታቦቱ ፊት ፍጹም ተቀባይነት ስለ አለው ነው። እሥራኤል ዘሥጋም ፈጣሪያቸውን ኃጢአት ሠርተው ሲበድሉት ሲያሣዝኑት፣ ሲያስቀይሙት ተመልሰውም ንስሐ ገብተው ሲያለቅሱና ሲለምኑት እግዚአብሔርም በመሐሪነቱ እየራራ የሚያነጋግራቸውና የሚገለጥላቸው በቃል ኪዳን ታቦት ነበር። እንዲያውም ታቦት የምሕረትና የደኅንነት መዝገብና መገለጫም ነው። (ዘጸ.፳፭፥፳-፳፩) ድረስ ተመልከት። እንዲያውም «ወውስተ ታቦት ትወዲ ትእዛዘ ዘእነ እሁበከ ወእትኤመር ለከ በህየ ወእትናገረከ እምላዕለ ተድባብ ማዕከለ ክልኤቱ ኪሩባን እለ ሀለው ዲበ ታቦት ዘመርጡል» ይላል።

በዚህም መሠረት ሰውና እግዚአብሔር የሚነጋገሩበት ልዩና ቅዱስ መገናኛ ነው። ታቦት በብሉይ ኪዳን ተሠርቶበት የቀረና ያከተመ ታይቶ የጠፋ አይደለም። እንዲያውም ጽላተ ሙሴ እንደ አጋጣሚ ሆኖ በፈጣሪ ፈቃድ ወደ ሌላ ክፍለ ዓለም ሳትሄድ ወደ ኢትዮጵያ ስለመጣች ሀገራችን ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት ብሉይ ኪዳንን ተቀብላ አምልኮተ እግዚአብሔርን አጽንታ ቆይታለች።

ኋላ በሐዲስ ኪዳንም የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪደንና ሥርዓቱን ተቀብላ እስከ ዘመናችን አድ ርሰዋለች። ይኸውም በትርስንት ብቻ ጠብቃ ያቈየችው አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝ መሠረት አድርጋ ነው። ለምሳሌ ጌታ በወንጌል ኦሪትና ነቢያት ሊፈጽ ማቸው እንጂ ሊሽራቸው አልመጣሁም «እውነት እውነት እላችኋለሁ ሥራዋም እንዲት፣ አቀራረጿም እንዲት የምትሆን የውጣ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከኦሪት ከነቢያት ተለይታ አታልፍም። ከእነዚህ ትእዛዛት አንዲቱን አሳንሶ የሻረ ለሰውም እንዲሁ ታንግለች ብሎ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ይሆናል።

እንዲህ የሚሠራ የሚያስተምር ግን እርሱ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይሆናል» (ማቴ.፭፥፲፯-፲፱) ብሎ ጌታ ባስተማረው መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ከብ ሉይ ኪዳን ትእዛዝ ወስዳ በተግባር ከምትሠራባቸው ንዋያተ ቅድሳት አንዱ ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት ጽላተ ኪዳን (ታቦት) ነው። ይኸውም በሰውና በእግዚአ ብሔር መካከል ጸንቶ ለሚኖረው ቃል ኪዳን ሕያው ቃሉ የተጻፈበት ዘለዓለማዊ የኪዳን ምስክር ነው።

ጥንታዊት የሆነችው የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሥርዓተ ኦሪትን ከሥርዓተ ወንጌል ጋር አጣምራ የያዘች ስለሆነ በክርስትና ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን ሥርዓቶች በክርስትና መንፈስ እየተረጎመች ትገለገልባቸዋለች።

## ታቦት (ጽላት) እንዲቀረፅ ማን ፈቀደ?

ከርዕሰ ደብር መሐሪ ኃይሉ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የስብከተ ወንጌል መምሪያ ኃላፊ

ለምሳሌ ቀደም ሲል እሥራኤላውያን ታቦተ ኪዳኑን እየያዙ በተጓዙባቸው መንገዶችና በሰፈሩባቸው መንደሮች ሁሉ ብዙ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ተአምራቶች ተሠርተዋል። ጽላቱ ሕጉን ይዘው የዘመቱባቸው የጦር መስኮች ሁሉ ድል አድርገውበታል። ኃጢአት በሠሩበት ጊዜም ረድኤተ እግዚአብሔር እየተለየቸው ድል እየሆኑ ነበር። (፩ኛ.ሳሙ.፬፥፲፩)

በሀገራችንም ታቦት የድልና የኃይል የአሸናፊነት ረቂቅ መግሪያ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን የውጪ ጠላት በተነሣባት ጊዜ ሁሉ ታቦቷን እየያዘች በግንባር ቀደም ትነት በመሰለፍ ድል ስታደርግበትና ሀገሩዋን ስትጠ ብቅበት ኖራለች። በታቦተ ሕጉ አምነው የተቀበሉት ያከበ ሩት ሁሉ የተአምራቱ በረከት ሲደርሳቸው የተዳፈሩትና ሳያምኑት የቀሩት ደግሞ ጠፍተውበታል። ተቀስፈ ውበታልም። (፩ኛሳሙ.፬፥፬-፮፤ ፮ኛሳሙ.፮፥፮-፲፩) ያከበሩት ደግሞ ተባርከዋል። (፪ኛሳሙ.፮፥፲፪-፲፰)።

ታቦት በሐዲስ ኪዳንም በቤተ ክርስቲያናችን ይሠ ራበታል። በመሠረቱ ታቦት ከሌለ ቤተ ክርስቲያን የሚባልም የለም። ማለት ይቀላል። ታቦት በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ማኅደረ እግዚአብሔር አካለ ክርስቶስ» ተብሎ ነው የሚቈጠረው ምክንያቱም ታቦተ ምሥዋዕ ታቦተ እግዚአብሔር ነው። ይኸውም እውነ ተኛው የሕይወት ምግብ የሆነው የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚቀርብበትና የሚፈተትበት የሚከብርበትም ነው። (ዕብ.፲፫፥፩) የሚከበረውን የሚሰገድለትም ለዚህ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስን ከሰይጣን ጋር አንድ የሚያደርገው ማን ነው? ምዕመናንስ ከመናፍቃን ጋር አንድ የሚያደርጋቸው ማን ነው? የእግዚአብሔር ታቦትስ በጣኦት ቤት የሚያኖር ማን ነው? በማለት አስተምሯል። (፪ኛቆር.፮፥፲፭-፲፯)።

ከዚህም ሌላ ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ «ከዚህ በኋላ በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ በመቅ ደሱም ውስጥ የእግዚአብሔር የሕጉ ታቦት ታየ» በማለት በአየው ሰማያዊ ራእይ ገልጾአል። (ራእይ ፲፩፥፲፱)።

በዚህም መሠረት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ብሉይ ኪዳን የተቀበለችውን ታቦት (ጽላተ ኪዳን) አክብራና አሊቃ በራሷ እየተሸከመች አምልኮተ እግዚአብሔር ስትፈጽም ስለ እምላክዋ ስም በአደባባይ ስትመስክር ኖራለች። ለወደ ፊትም በዚሁ ሥርዓት ትኖራለች።

ታቦት ለቤተ ክርስቲያናችን ትልቁ እምነትዋ የሥር ዓቷን መመስከሪያና መገለጫ ነው። ታቦት በስመ ሥላሴ፣ በቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም፣ በቅዱሳን መላ እክት፣ በነቢያት፣ በሐዋርያት በጻድቃን በሰማዕታት፣ ስም ይቀረጻል። ታቦት በማይገባቸው ሰዎች ቢገሠሥ፣ ቢማረክ እንደ [illegible]ና በኤጲስ ቆጶስ ልዩ ጸሎት ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ ይከብራል፣ ይቀደሳል።

ታቦት (ጽላት) እንዲቀረጽ ማን ፈቀደ?

ሊቀ ነቢያት ሙሴ እንደ መጀመሪያዎቹ ጽላቶች ያለ በፈጣሪው ፈቃድ እንደ ገና እንዲቀረጽ ቢታዘዘው መሠረት በየጊዜው ይቀረፃል፣ ይሠራል። (ዘጸ.፴፬፥፩)።

እንዴት ይሰገድለታልስ?

ስመ እግዚአብሔር ፈጣሪ (ስመ ሥላሴ) ስለ ተጻፈ በት ይሰገድለታል። ለስመ ፈጣሪ መስገድም እንደሚገባ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሳይቀር መስክሮአል። እንዲህ ሲል «ከመ ለስመ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሰግድ ኵሉ ብሩክ ዘበሰማያት ወዘበምድር ወዘበቀላያት ወለእለ ታሕተ ምድር» (ፊልጵ.፪፥፲፤ የሐዋ.ሥ.፰፥፳፫፤ ራእ.፰፥፲፫፤ ኢሳ.፵፭፥፳፫ ተመልከት)። በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓትም ታቦት ከማይ ነቅዝ ዕፀ ወይም ዕብነ በረድ ከወርቅና ከዕንቍ ኢያ ይሆናል ከብረት ማዕድን ግን በፍጹም አይሆንም፣ አይፈቀድምም። የአቀራረፁ ትእዛዝም መጠኑም በኦሪት (ዘጸ.፴፮፥፩) ላይ የተጠቀሰውን እንዳለ ሆኖ በውስጡ ስመ እግዚአብሔር በ፱ ገጽ ይጻፍበታል።

ሥዕለ ኪሩብም ይቀረጽበታል። በመካከልም ሥዕለ ሥላሴ ይሳልበታል በኤጲስ ቆጶስ ተባርኮ ይቀደሳል፣ በሜሮን ቅባት ይከብራል። ከዚያም በመንበሩ ላይ ይሰየ ማል ጽላት (ታቦት) በማይኖርበት (በሌለበት) ቤተ ክርስቲ ያን በምንም ተአምር ሥርዓተ ቅዳሴ አይደረገም ስጊድም አይፈጸምም። ታቦትንም ለመያዝና ለመዳሰስ ለመሸከም የሚችሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ጳጳሳትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው እንዲህ ከሆነ ታቦት ወደ አገራችንስ መቼ መጣ?

በብሉይ ዘመን በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ጊዜ የመጣ ለመሆኑ ታሪክ ይናገራል ብዙ የታሪክ መዝጋቢዎችም በየ ድርሰታቸው መስክረዋል።

በሐዲስ ኪዳንስ ከመቼ ጀምሮ አገራችን ተቀበለችው?

እንደ የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ/ ሊቃውንት አባባል በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ዘመን ክህነትና የሐዲስ ኪዳን መሠረት የሆነው ክርስትና ከእስክንድርያ ወደ አገራችን ሲገባ ሦስት ታቦታት አብረው እንደ መጡ ይነገራል። እነሱም:-

፩. ታቦተ ኢየሱስ ክርስቶስ
፪. ታቦተ እግዝእትነ ማርያም
፫. ታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ተብለው ተሰይመው ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገቡ ሊቃውንት በአጽ ንኦት ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም ሐምሌ ፲ ቀን የሚነ በበው ገድለ ሐዋርያት የተባለው የታሪክ መጽሐፍ በሰ ፊው ያብራራል።

በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ታቦት በየዓመቱ ከጥር ፲ ቀን ጀምሮ ታቦታት ከየመንበረ ክብ ራቸው ተነሥተው በምዕመናን ሆታና እልልታ እጀቢነት በውዳሴና በማኅሌት ወደየ ምጥማቃት እንዲወርዱ ታደር ጋለች። ይህም ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ታሪኮች በመያዝ ነው። እነሱም:-

፩ኛ. በነቢዩ ኢያሱ ዘመን የሕዝበ እሥራኤል ከመ ጠን በላይ ሞልቶ የነበረውን የዮርዳኖስ ወንዝ ለመሻገር እንዲችሉ በመጀመሪያ ታቦተ ኪዳንን የተሸከሙ ካህናት የዮርዳኖስ ወራጅ ውኃን በተረገጡና እግሮቻቸውም በውኃ ውስጥ በጠለቁ ጊዜ እጅግ ከመጠን በላይ ሞልቶ የነበረውን የዮርዳኖስ ውኃ ያለፈው አልፎ ተከታዩ ወራጅ ውኃ እንደክምር ከላይቶመ ታቦተ ኪዳንን የተሸከሙ ካህናት የዮርዳኖስን ወንዝ በደረቅ ተሻገሩ እንኳን ውኃ ሊያገኙ ርጥበትም አልገጠማቸውም። በታቦቱ አማካይነት እሥራኤላውያን በሙሉ በደረቅ ተሻገሩ። (ኢያሱ ፫፥፲፬-፲፯)። አንደኛው በዚሁ መነሻነት ሲሆን ፪ኛ. ደግሞ እግዚአ ፍጥረታት ኢየሱስ ክርስቶስ ትህትናን ለማስተማር ወደዚህ የመጣበትን ውጤት ለማሳየት ጌታ ሲሆን ወደባሪያው፣ ፈጣሪ ሲሆን ወደ ፍጡሩ ተጕዞ በነቢዩ በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ያደረገውን ትሕትና የተሞላበት አምላካዊ ጕዞ ለማስታወስ ነው። ታቦት ተይዞ በየወንዝ ዳር የሚታደረውና ልዩ ክብር የሚደረገው በዚህ መነሻነት ነው።

በቀጣዩ እትም ላይ ፩ኛ. ታቦት በጻድቃን በሰማ ዕታት ስም፣ ፪ኛ. በቅዱሳን መላእክት ስም እየተሰየመ እን ዲጠራና ታቦት በብሉይ ኪዳን ነበር እንጂ በሐዲስ ኪዳን ታቦት የለም ለሚሉ ላልታደሉ ሰዎች ሰፊ ምላሽና ሌላም በዚሁ ዙሪያ የሚነገሩ መንፈሳውያን ጉዳዮች እክስን የምናቀርብ መሆኑን እየገለጽን ለዛሬው ግን በአንደኛው ክፍል ስለ ታቦት ክብር ከብዙ በጥቂቱ ያቀረብን መሆኑን በማክበር እየገለጽን በታቦት ላይ አድሮ የሚመሰገነው እግዚአ ኃያላን ፈጣሪያችን ጸጋውን በረከቱን እንዲ ያድ ለን እንለምናለን። አሜን። ✣

## እስትጉቡእ...

ከሽፋኑ የውስጥ ገጽ የዞረ

ጾም የሥጋ እና የመንፈስ ጠላቶ ቻችንን የምናሸንፍበት ስለሆነ እንጾማለን።

«ይህ ዓይነት ግን ከጸሎት እና ከጾም በስተቀር አይወጣም አላቸው» (ማቴ.፲፯፥፳፩)።

መድኅን ክርስቶስ በመብል የገባ ሰይጣንን ድል የነሣው በጾም ነው (ማቴ.፬፥፲)።

አስቴር እና ቤተሰቦቿ ጠላቶቻ ቸውን ድል ያደረጉት በጾም ነው (አስ ቴር ፬፥፲፯)።

ጾም ራሳችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛበት መንገድ ስለሆነ እንጾ ማለን (መዝ.፴፭፥፲፤ ፩ሳሙ.፯፥፯)።

የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግ ኘት መጾም ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። (ዘጸ.፴፬፥፳፰)። ጾማችን ከሥጋዊ መብል እና መጠጥ ብቻ ሳይሆን ከክፉ ሥራም ሊሆን ይገባል። ይህ ካልሆነ ጾማችን እውነተኛ ጾም ሳይሆን የረሃብ አድማ ወይንም ትርፉ የቤት ወጭን ለመቀነስ ቁጠባ ብቻ ነው የሚሆነው (ኢሳ.፶፰፥፫)።

ጾማችን ያለ ከንቱ ውዳሴ ሊሆን ይገባል (ማቴ.፮፥፲፯)።

የጾማችን መጨረሻ (ፋሲካ) የእኛን ሰባት ሥጋ ብቻ ሳይሆን የዓለምን ኃጢአት ያስወገደው የቀራንዮው በግ የመድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ሥጋ እና ደም ሊሆን ይገባል (ዮሐ.፮፥፳፱)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወወላ ዲቱ ድንግል ለዓለመ ዓለም አሜን።

## ዘመነ ቅበላ

ከመሪጌታ ምናሴ ወ/ሐና

### ዘመነ ቅበላ ምንድን ነው?

ዘመነ ቅበላ ወይም ዘመነ መርዓዊ የሚለው ኃይለ ቃል ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ በትውፊታዊ ወይም በትብብል መልክ ሲነገር መኖሩ የሚታወቅ ነው። ሆኖም ይህ በልማድ የሚነገር ብቻ ሳይሆን ስያሜው ከየት መጣ? ለምን መጣ? በማን መጣ? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ማግኘት የሚያስፈልገውና በውል መታወቅ እንዳለበት አጠያያቂ አይሆንም።

ከላይ በርእሱ እንደ ተጠቀሰው ዘመነ ቅበላ ወይም ዘመነ መርዓዊ የሚለው ስያሜ በልማድ የመጣ ሳይሆን ሰፊ የሆኑ ምሥጢራትና ምሳሌዎች አሉት።

ይኼውም ነገርን ከሥሩ ወኃን ከጥሩ እንዲሉ አበው ምሳሌው ዘመነ መርዓዊ የሠርግ፣ የደስታ፣ የመ ታደስ፣ የመልበስ የማስጌጥ ወራት (ወቅት) ማለት ሠርግ በሚደረግበት ጊዜ የቅርብ የሩቅ ዘመድ አዝማድ ወዳጅ ወገን በሙሉ ይጠራል፤ ጥሪ ውን የተቀበለ ዘመድ፣ አዝማድ፣ ወዳጅ፣ ወገንም ለሠርጉ ቅድመ ዝግ ጅት ያደርጋል። ማለትም ያለው አዲስ ልብስ ገዝቶ፣ የሌለው የነበ ረውን አጥቦና አጽድቶ፣ የደስታው ተካፋይ ይሆናል ማለት ነው።

ምሥጢሩ እንደ ምንድን ቢሉ? አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን ፈጣሪያቸው «አታድርጉ» ብሎ ያዘዛቸውን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው ምክንያት ተድላ ደስታ፣ ከተሞላች ገነት ወጥተው፣ ምድረ ፍዳ ወር ደው፣ ከነልጅ ልጆቻቸው ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት ያህል በፍዳ በመከራ ከነበሩ በኋላ ምንም እንኳ አዳም እና ሔዋን መከራውንና (ፍዳውን) በራሳቸው ስህተት ያመ ጡት ቢሆንም መሐሪውና ይቅር ባይ አምላክ በከኃሊነቱ ስለ ራራላቸው፣ «በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ» ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በመልእልተ መስቀል ተሰቅዬ፣ ሞቼ አድንኃለሁ። ብሎ ልዑለ ባሕርይ አምላክ በማይታበል ቃሉ ለአዳም ሲነግረው ከአዳም ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የልጅ ልጆቹንም ጭምር እንደሚ ያድን ነው ቃል የገባው። መርዓዊ (ሙሽራው) ወልደ እግዚአብሔር ነው። ዘፍጥረት ፲፪፥፫ ሙሽራ በመጣ ጊዜ ከሩቅም ከቅርብም የመጣ ዘመድ አዝማድ ባንድነት በደስታ እንዲቀበሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ዓለምን ለማዳን የመጣው ከአም ስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ወዲህ ያሉትን ለማዳን ብቻ የመጣ አለመሆኑን፣ ይህም ሲባል ብዙ ደጋግ ነቢያት ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን እንደሚመጣ ሱባዔ ቆጥረዋል፤ ትንቢት ተናግረዋል። ከነዚህም መካ ከል በ፰ኛው መቶ ዓመተ ዓለም ዋዜማ የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ ከተና ገረው ወስዶ ቅዱስ ያሬድ በድጓው «ትወጽእ በትር እምስርወ እሴይ ወጽጌ ዘወጽአ እምኔሃ እምላክ ለወልድ» በማለት ከዳዊት ዘር ሐረግ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደምትወለድና ጌታችን መድኃኒታችንም ከእመቤታችን እንደሚወለድ ያስረዳል። (ኢሳይያስ ፯፥፲፬፤ ፱፥፯፤ ፲፩፥፲፩፤ ሰቆቃወ ኤርምያስ ፲፩፥፵፪፤ ትንቢተ ሚክያስ ፭፥፪)። የክርስቶስን መምጣት ኃብተ ትንቢት የተሰጣቸው ደጋግ ነቢያት ብቻ ሳይሆኑ በሀብተ መርገም ስጦ ታው የታወቀው በልአም ሳይቀር ትን ቢት መናገሩን ቅዱስ ያሬድ በድጓው «ይሠርቅ ኮከብ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምእስራኤል» ከያዕቆብ ወገን ኮከብ ይወጣል፤ መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ይወለዳል። የእስራ ኤልንም ኃጢአት ያስወግዳል። በማለት ገልጾታል። ከዚሁም በመቀ ጠል ቅዱስ ያሬድ በድጓው እንደሚ ገልጸው «እምርሁቅ ርእዩዋ ወተአምኑዋ ወአእመሩ ከመ ሀገርሙ ይእቲ» ይህም ማለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትወልደውና በእርስዋም ምክንያት መንግሥተ ሰማያት ሀገራ ቸው መሆኗን ነቢያት ለረጅም ዘመን ትንቢት መናገራቸውን ለመግለጽ ነው። የዚህ ጽሑፍ ማሠሪያ ኃይለ ቃሉ ቅበላ ሙሽራን ለመድኃኒተ ዓለም የመጣውን ወልደ እግዚአ ብሔርን መቀበል፣ ማለት ብሉይን ትተን ሐዲስን መቀበል። የሩቅ ዘመድ አዝማድ መሠራት (ለሠርግ) የተነገ ረውን ትንቢት፣ የተቈጠረውን ሱባኤ፣ ከሐዲስ በፊት አምነው በተስፋ ይጠብቁ የነበሩትን የሚያ መለክት ሲሆን የቅርብ ዘመድ አዝማድ እንደ መጥራት ከልደቱ በኋላ ያሉትን (በሐዲስ ያሉትን) የሚያ መለክት ነው። ወደ ሠርግ የታደ ሙትና ሙሽራውን ለመቀበል የሚዘ ጋጁት ልብሳቸውን ማንጻት እንዳ ገባቸው፣ በንስሐ መታጠብ የሚገባ መሆኑን ምሳሌውንና ምሥጢሩን (ማቴዎስ ፳፫፥፲፱) በሰፊው መገንዘብ ይቻላል።

ስለዚህ የቅበላ ወይም ዘመነ መርዓዊ ምሳሌና ምሥጢሩ ከረጅሙ ባጭሩ ይህንን ይመስላል።

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ። ✣



www.ethiopianorthodox.org

የጀርባ ፎቶ በግርማ ኤልያስ